# ፍካሬ

በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

ታትሞ የሚወጣ ሩባዊ

ጥናታዊ የትንተና መጽሄት

ቅጽ 15 ቁጥር 1 ህዳር 2000 ዓ.ም.

# ስለ ፍካሬ ልታውቋቸው የሚገቡ ጉዳዮች

1. በፍካሬ የሚወጡ ጽሁፎች ሁሉ የፓርቲ አባላት የጻፏቸው ጽሁፎች ወይም የፓርቲው አቋሞች አይደሉም። የፓርቲውን አቋም የሚመለከት ጽሁፍ ሲወጣ ይህንን ያስታውቃል።

2. የሚላኩ ጽሁፎች በአማርኛ የተዘጋጁ ቢሆኑ ይመረጣል።

3. የአመት ደንበኞች ለመሆን የሚሹ ሁሉ አመታዊ ክፍያው ለአራት ዕትሞች 16.00 አይሮ ወይንም ደግሞ ተመጣጣኝ ምንዛሬ ይሆናል። ይህንኑ በፖስታ ሳጥን ቁጥራችን መላክ ይቻላል። የሚከፈለው በቼክ ወይም በመኒ ኦርደር ለኢሕአፓ ነው።

4. ፍካሬ በአመት አራት ጊዜ ትወጣለች።

5. ጽሁፎች መላክ የሚፈልጉ በሀገራዊና አለም አቀፋዊ የፖለቲካና የኤኮኖሚ ጉዳዮች፤ ሥነ ጽሁፎችና ፓርቲ ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ ሊላክልን ይቻላል። በተቻለ መጠን ጸሃፊዎቹ ስማቸውን አለዚያም የብዕር ስማቸውን ሊነግሩን ይገባል። የብዕር ስም የሚጠቀሙ ከሕጋዊ እርምጃዎች አንጻር አግባብ ስላለው ለአዘጋጆቹ ብቻ ስማቸውንና አድራሻቸውን መግለጽ ይኖርባቸዋል።

6. ጽሁፎች እስከተቻለ ድረስ በጣም ባይረዝሙ (ከ 5-7 ገጽ) ባይበልጡ ይመረጣል። ለጥራትና ለመጠን ሲባል ጽሁፎች እርማት ሊደረግባቸው ይችላል።

7. የሚደርሱንን ደብዳቤዎች በየጊዜው እናወጣለን። ደብዳቤ የሚጽፉ ስማቸውንና አድራሻቸውን ከነስልክ ቁጥራቸው በትክክል እንዲያሰፍሩ እንጠይቃለን።

8. ርዕሰ አንቀጾቹ ከዝግጅቱ ክፍል የሚቀርቡ ናቸው።

ዋና አዘጋጅ ዶ/ር ዘነበ ተሾመ

ምክትል ዋና አዘጋጅ ሀይሉ ወንዴ

መጽሄቷን ለሚመለከቱ ግንኙነቶች በሚከተለው አድራሻ ይጠቀሙ።

FIKARE
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A

# ፍካሬ

በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ

ታትሞ የሚወጣ

ሩባዊ መጽሄት

# ማውጫ


1. ርዕሰ አንቀጽ (ከዝግጅት ክፍላችን) ገጽ 1

2. የግሎባላይዜሽን ክስተት ገጽ 3

3. ጠላት ምንጊዜም ጠላት ነው ገጽ 13

4. Book Review

   By Lemma Tesfaye ገጽ 23

5. ስለ ሰብአዊ መብት ስናወጋ

   ከ ቶንጂት ተስፋዬ ገጽ 26

6. ከሃይማኖት ነጻ የሆነ ፖለቲካ ገጽ 37

   ከ ታቶ ደቼሳ

7. *የኢትዮጵያ ሴቶች* ገጽ 40


*የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማምጣት በሚደረገው ትግል ውስጥ መሳተፍ አስፈላጊና ወሳኝ ነው።*

## *ከዝግጅት ክፍላችን*

ባለፉት ሁለት አመታት በድርጅታችን ውስጥ በተከሰተው አንጃኝነትና በታኝነት ባስከተሉት ውስጣዊ ችግሮች የተነሳ የፍካሬ መጽሄትን ጊዜውን ጠብቀን ለንባብ ማብቃት አልተቻለንም ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን የአንጃው ቡድን ከንግሳንግሱ ተነቅሎ በመውጣቱ በግልጽም ሆነ በስውር ያካሄድ የነበረው ችግርም በመወገዱ ፍካሬ እንደቀድሞው የውድ አንባቢያንን ፍላጎት ለማሟላት በአዲስ መንፈስ ጥረት በማድረግ ይኸው የመጀመሪያውን እትም አቅርበናል። በበኩላችን እኛን የሚያሳስበን፡ የሚያስጨንቀንና እንቅልፍ የሚያሳጣን ጉዳይ የሀገራችን ሉአላዊነት ተጠብቆ መኖር፡ የወያኔ አምባገነን አገዛዝ በትግላችን ገርስስን በምትኩ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በመመስረት፤ ሰላምንና ማህበራዊ መረጋጋትን፤ የሕግ የበላይነት፤ እኩልነትን በማስፈን ለእድገትና ብልጽግና ጥረት ማድረግን ነው። በመሆኑም ለአንባቢያን ለመግለጽ የምንወደው ቀድሞውንም ስኬታማ ለማድረግ የተደራጀንበትንና ባነገብነው ዋና አላማ ላይ ትኩረትን ሰጥቶ መታገልን፤ ለዚህም ሕዝብን በመቀስቀስ፤ በማደራጀት፤ ታግሎ በማታገል የበኩላችንን አስተዋጽዖ ማበርከት ነው። ስለዚህም "እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል" የሚለውን የአባቶች ብሂል በመጠቀም ድርጅታችንን ጥሎ ለወጣ አናሳ ቡድንና ለሚያካሂደው መሰሪ ተንኮል ጊዜያችንና ውድ የመጽሔታችን ገጾች በእሰጥ እገባ ለማጣበብ ጨርሶ ፍላጎት የለንም። አይኖረንምም። የፉካሬ ዋና ተልዕኮ በአገራችን በኢትዮጵያ የፖለቲካ፤ የኤኮኖሚና የሶሻል መስክ ውስጥ ለተከሰቱ ችግሮችና እነዚህን ለማስወገድ በሚቀርቡ የመፍትሔ ሀሳቦች ዙሪያ አንባቢያንን በማወያየት የንቃተ ህሊና ጥራት ላይ የተመሰረተ መግባባት ለማስገኘት መድረክ ሆኖ ማገልገል ነው። በዚህ መርህ ላይ በመመስረት ወድ አንባቢያን የመጽሄታችንን ዝርዝር ይዘት በንባባችሁ ሂደት የምታጣጥሙት ቢሆንም ይህ እትም የአዕምሮ ምግብ ይሆናሉ ያልናቸውን የተለያዩ ሀተታዎችን ያዘሉ ጽሁፎችን ይዘን ቀርበንላችኋል።

የሀገር መሪዎች ሀገራዊና ሕዝባዊ የሆነ ራዕይ ሳይኖራቸው፤ የፍትሃዊነት መንገድ ሳይከተሉና የጎሳ ፖለቲካ ሳይወገድ ብዙሃኑን ሕዝብ ሊያረካ የሚችል ልማትም ሆነ ሰላምም የማይታሰቡ መሆናቸው ግልጽ ነው። በአገዛዙ ባለሥልጣናት በኩል የ ኤኮኖሚ እድገትና ስለኑሮ ውድነት አስመልክቶ ባለፉት ጥቂት ጊዜያት ያልተነገረ ውሸት፤ ያልታጠፈ ስታቲስቲክ፤ ሕዝብ እየተጎዳ ቀድሞውኑም ቢሆን በባዕዳን ከፍተኛ ድጋፍ ያለ ኤኮኖሚ ተናግቶ ባለበት፤ የኑሮ ውድነቱ ሁሉንም በተለይም ደግሞ በከተማና በገጠር ኗሪ የሆነውንና ዝቅተኛ ገቢ ያለውን በርካታ ሕዝብን አጣብቂኝ ውስጥ ከትቶ እያለ ምኞት በምኞት ላይ ነው ተብሎ ሲነገር ታዝበናል። ተጨባጩ ሁኔታ የሚያሳየው ሥዕል ግን ሌላ ነው። የዋጋ ግሽበትን የሚያበረታቱ ፖሊሲዎች ተግባራዊ መሆን፤ የማዳበሪያ ዋጋ መናሩ፤ የትራንስፖርት ክፍያ መጨመሩ፤ ደሞዝተኛ ተዳዳሪ የሆነው በኑሮ ውድነት የተነሳ በላይ ላይ እየተጫነበት

ያለውን ሽክም መሸከም አልቻለም። በአራቱም ማዕዘን ስለሚኖረው ገበሬ ተጨባጭና አሳማኝ የሆነ የስታቲስቲክ መረጃዎችን ሳይቀርብ በደፈናው የገበሬው በኤኮኖሚው ማደግ ለኑሮ ውድነቱ አስተዋጽኦ ምክንያት ሆኗል የሚለው ገለጻ ስለ ኤኮኖም እውቀት ማነስን የሚያመልክት ብቻ ሳይሆን ለዘብ ባለ አነጋገር ሕዝብን ማወናበድ ከመሆን የሚያልፍ አይደለም። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን አስቸኳይ የምግብ እርዳታ ያስፈልጋቸዋል የሚል ዜና መወራት ከጀመረ መሰንበቱ የሚያመልክተው የሁናቴውን አሳሳቢነት እንጂ ሌላ አይደለም። ድህነት እየቀነሰ ሳይሆን እየጨመረ መሆኑ በግልጽ የሚታይ ነው። በሀገራችን የፖለቲካና ማህበራዊ ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያሳድር ከሚችለው ውስጥ አንዱ በግሎባላይዜሽን ሥም የሚታወቀው አለም አቀፋዊ ክስተት ነው። ይህንን አስመልክቶ ይህ የተባለው ግሎባላይዜሽን ታሪካዊ አመጣጡንና በሀገራችን የፖለቲካ ማህበራዊና ኤኮኖሚያው ሁኔታዎች ላይ ስለሚኖረው አሉታዊና አዎንታዊ አንደምታ በሰፋት የሚዘረዝርና በቂ ግንዛቤን የሚያስጨብጥ ነውና ተመለከቱት።

በትግል ሂደት ውስጥ ድልን ለመጎናጸፍ የሚሻ ማንኛውም ሀገር ወዳድ ታጋይ በሙሉ ጠላቱንና ወዳጁን በሚገባ ለይቶ መገንዘብና መረዳት መሰረታዊ የሆነ የመጀመሪያው እርምጃ ብቻ ሳይሆን የሰከነ ትግል ለማካሄድ፤ በተቻለ መጠን ከስህተት በመዳን የጠራና የተስተካከለ ሂደትን ለመጓዝ በጣም ወሳኝ ነው። ይህንን ሃሳብ ከግንዛቤ ባለማስገባት ባለፉት ጊዜያት የተለያዩ ምክንያቶችን እየደረደሩ ሕዝብን እያሰቃየ ካለ የአገዛዝ ቡድን ጋር ባደረጉት መተቃቀፍ የተነሳ በሕዝቡም ሆነ በራሳቸው ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከተለ መሆኑ ባለፉት የትግል አመታት ውስጥ በበቂ የታየ ክስተትና በቁጭትም የምናስታውሰው ነው። ይህ አልበቃ ብሎ በአሁኑ ወቅትም ከዚህ ሁኔታ ተመክሮ ባለመወሰድ ተመሳሳይ ስህተት ለመፈጸም ዳዴ የሚሉ ይገኛሉ። ሌባ ሰርቶ ሲያዝም ሰርቄያለሁ ብሎ የሚናገር እንዳልሆነ ይታወቃል። በሌላ አነጋገር ዛሬም ሸማ በየፈርጁ የሚለበስ መሆኑ የሚያስገነዝበን ሁኔታ እየተከሰተ ነውና የትግል ሂደትን ለማስተካከል ይረዳ ዘንድ ከፍኖተ ዴሞክራሲ የተገኘ “ጠላት ምንጊዜም ጠላት ነው።” በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ሀተታ ይዘንላችሁ ቀርበናል።

የሴቶችን ጥያቄ አስመልክቶ ስለሚደርስባቸው የተለያዩ ድርብርብ ጭቆናዎችና በደሎች በሁለንተናዊ መልኩ በመተንተን በሶሻል ዴሞክራሲ መርህ ከሚመሩ ሀገራት የተገኙ ተመክሮዎችን ጭምር በመዳሰስ ሴቶች ነጻነታቸውን እንዲጎናጸፉ መካሄድ ስለሚገባውም የትግል ስልት በተለይም ሴቶች በጾታቸው መደራጀታቸው ወሳኝ መሆኑ አጽንኦት ሰጥቶ የሚተነትንና የሚጠቁም መጣጥፍ አለና ተመልክቶ ማዳበሩም የሁሉም ፈንታ ይሆናል። የሴቶች መበት በሁለመናው መልኩ የማይረጋገጥበት ሥርአት ዴሞክራሲያዊ ነው ለማለት የሚያስቸግር መሆኑ ግንዛቤ ያስጨብጣል። ሁላችንንም የግል አቋማችንን እንድንመረምርም የሚጋብዝ ነው።

በመንግስትና በሀይማኖት መካከል ስለሚኖረው ግንኙነት በተለይም እንደ ኢትዮጵያ በርካታ እምነቶች ጎን ለጎን በሚገኙበት ሁኔታ የፖለቲካ ድርጅቶች ሚናቸውን አስመልክቶም ሆነ መከተል ስለሚገባቸው መርህና ማንጸባረቅ ስለሚኖርባቸው አርቆ አስተዋይነት የተሞላበት አርአያነት የሚዳስስ ጽሁፍ ታቶ ደቻሳ ያቀረቡልን መጣጥፍ አለን።

ቀንጂት ተስፋዬ የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ የተመሰረተበትን 13ኛ አመቱን በቅርቡ ማክበሩን ምክንያት በማድረግ ስለ ሰብአዊ መብቶች ይዘትና ምንነት አስመልክቶ በስፋት የዘረዘረበትን መጣጥፍ አቅርባልናለች።

በመጨረሻም በቅርብ ጊዜ በእንግሊዝኛ ታትሞ ለንባብ የቀረበን መጽሐፍ SEEDS FOR DEMOCRATIZATION IN ETHIOPIA፡ WHY UNITY OF PURPOSE MATTERS አጠር ባለ መልክ በለማ ተስፋዬ የተገመገመበትም ቀርቧል።

መልካም ንባብ።

# የግሎባላይዜሽን ክስተት

ግሎባላይዜሽን እንደ ክስተት ብቅ ያለው የዛሬ ሰላሣ አመት ገደማ የአሜሪካን ፕሬዚዳንት ኒክስንና የቀድሞዋ ሶቪየት ህብረት ፕሬዚዳንት ብሬዥኔቭ በ1970ዎቹ "ተቻችሎ መኖር" (détente) የሚል ስምምነት ካደረጉ በኋላ ነው። ስለሂደቱና እድገቱም የምዕራብዊያን ጋዜጠኞች ማለት የሚዲያ ሰዎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግሎባላይዜሽን ያስገኘውን ውጤትና ወደፊትም ሊያመጣ የሚችለውን ጠቀሜታ በተመለከተ ትንቢታቸውን እያስደመጡን ነው። እንደትንቢታቸው እንከን የለሽ "ማርና ወተት" ቢሆን ኖሮ ምንኛ መልካም ነበር። ግን የተባለው "ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ" ስለሆነ የሶሻል ሳይንስ ጠበብቶችና ፖለቲከኞች እንዲሁም የዓለም ህብረተሰብ የግሎባላይዜሽን አሉታዊና አወንታዊ ሂደትና ውጤት እስከአሁንና ወደፊት ሊያስከትል የሚችለውን እንደምታ በጥልቀት በማጥናት የአሳብ ፍጭቶት በማድረግ ላይ ናቸው።

የኒዮሊብራል (neo-liberal) ተከታዮች በተለይም የኮርፐሬሽን ጠበብቶች (corporate elites) ግሎባላይዜሽን በዓለም ላይ ላሉት ችግሮች በሙሉ እንዲሁም ወደፊት ለሚከሰቱት መፍትሔ ሰጪ ርዕዮት ነው ብለው ለማሳመን እየጣሩ ነው። በተቃራኒው ተራማጅ ጠበብቶች ጉዳቱ ከአሁኑ በጠዋቱ ካልታረመና በዘፈቀደ እንዲቀጥል ከተደረገ በዓለም ላይ በተለይም በቴክኖሎጂ ወደኋላ በቀሩት ደሃ አገሮች እንዲሁም በበለጸጉ አገሮች ውስጥ በሠራተኛው ክፍልና ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ላይ ብዙ ጉዳት ያመጣል/ያደርሳል በማለት ጩኸታቸውን እያሰሙ ናቸው። ለስጋታቸውም እንደዋቢነት ከሚያቀርቡአቸው መካከል የግሎባላይዘሽን አንዱ ዋና አካል የሆነው የዓለም አቀፍ ኮርፐሬሽን (transnational corporations) ነው። በአሁኑ ጊዜ በብዙ አገሮች/ቦታዎች ውስጥ የአካባቢ ብክለት፣ የአየር መለዋወጥና፣ ረሃብና ድህነት እንዲስፋፋ፣ እንዲሁም ኢፍትሃዊ ሥርዓት እንዲሰፍን በማድረግ መሆኑን ነው። ሌላው የሚያነሱት ፍራቻና ስጋት የግሎባላይዜሽን ሂደት አሁን በጊዜው ካልታረመና ቁጥጥር ካልተደረገበት ምናልባትም ለብዙ አገሮች ብሄራዊ አንድነታቸውን ማለት ልዑላአዊነታቸውን የሚያጡበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል የሚል ነው።

የግሎባላይዜሽን ሂደትና ማንነት በጥልቀት ለመተንተን ከመሞከራችን በፊት፤ ግሎባላይዜሽን በፅንሰ አሳብ

ደረጃ ምን ማለት እንደሆነና በጥንቱና በአሁኑ ዓለም አቀፍ ግንኙነት መካከል ያለውን ልዩነትና አንድነት እንድናብራራ ይፈቀድልን።

## የጥንቱ አለም አቀፍነትና አዲሱ ግሎባላይዜሽን

### የጥንቱ ዓለም አቀፍ ግንኙነት

የሰው ልጅ ከጥንት ዘመን ጀምሮ በተናጠልና በብድን በመሆን ከአገር ወደ አገር በተለያዩ ምክንያቶች በመፍለስና በመሰደድ እንዲሁም በንግድ ከቦታ ቦታ በመዘዋወር አዳዲስ አሳቦችን፣ የአሰራር ዘዴዎችን፣ የእውቀት ግኝቶችን፣ እንዲሁም እምነቶችን በፈቃደኝነትና በእኩልነት ያለፓስፖርትና የቪዛ ፈቃድ ልውውጥ ሲያደግ ነበር። የግንኙነቱ ሂደትና ክንዋኔ በጣም አዝጋሚ ማለት ብዙ ሺ አመታት የፈጀ ነበር። የእውቀት ልውውጡም በቀጥታ በቅጅ/ኮፒ በማድረግ ሳይሆን አዳዲስ ግኝቶችንና አስተሳሰቦችን ከየአገራቸው ሁኔታ ጋር በማዋሃድ ሥልጣኔያቸውን ያዳብሩበት ነበር። ጎጅውንም ነገሮች በአገራቸው ውስጥ እንዳይስፋፉ ይከላከሉ ነበር። የአሁን መጤው ግሎባላይዜሽን የጥንቱ የነፃ ግንኙትና አሰራር እንዲቀየር አድርጎታል።

### ግሎባላይዜሽን

ግሎባላይዜሽን ከጥንቱ አለም አቀፍ ግንኙነት ጋር በዋናነት የሚለይበት ሂደቱ በጣም ፈጣን ማለት ቦታና ጊዜ (time and space) የማይገድበው እንዲሁም ሃያላን በደካሞች አገሮች ላይ ጫና የሚያደርጉበት መሣሪይ መሆኑ ነው። የቴክኖሎጂን አመርታ በሞኖፖል በመያዝና የእድገቱ መሰረት በማድረግ በአዲስ አይዲዮሎጂ የዓለምን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የሶሻል ሥርዓቶች አንድ ወጥ አድርጎ ለመቆጣጠርና ለመግዛት ጥረት እያደረገ ያለ ሃይል ነው። እዚህ ደረጃ ከአደረሱት የቴክኖሎጂ እድገቶች መካከል ዋና ዋናዎቹን እንድንጠቅ ይፈቀድልን። እነሱም የጄት አውሮፕላን መፈጠር፣ የቴሌፎን አገልግሎት ዋጋ እርካሽ ማድረግ መቻሉ፣ ኢሜልና ኮምፒተር እንዲሁም የቴሌና ቪድዮ ስብሰባ/ኮንፍራንስና ቲቪ እንዲሁም ፓልቶክ ከተለያዩ አገሮችና አህጉሮች ጋር በአነስተኛ ወጭ ግንኙነት መደረግ መቻሉ፤ እንዲሁም ገንዘብ ማለት የፍይናንስ ስምምነትና ልውውጥ በቀላሉ በጥቂት ሰኮንዶዎች መለዋዋጥ/መላክ መቻሉ ናቸው።

የግሎባለይዘሽን ፕሮፓጋንዲስቶች የምስራች ሲያበስሩ እንዲህ ይላሉ "ከእንግዲህ ዓለም አንድ መንደር (global village) ሆናለች፣ አንዱ አገር ከሌላው አገር ጋር የተዛመደና የተሳሰረ (interdependent) ነው። አንድ አገር በተናጠል ብቻውን መኖር አይችልም። የዚህን የግሎባላይዜሽን ሂደት ማንም ምድራዊ ሀይል ሊያቆመው አይችልም።" በአጭሩ መልዕክታቸው "ስልፋችሁን ከግሎባላይዜሽን ጋር አስተካክሉ አለበለዚያ ብዙ ችግሮች ይደርስባችሁና በመጨረሻም ትጠፋላችሁ" ነው። እንደተባለውም ሂደቱ እንደ ልጓም የለሽ ፈረስ

ከተለቀቀ የሚያስከትለው ጉዳቶች አልቆመሳፍርት ሊሆኑ ይችላሉ።

እስቲ እስከአሁን ድረስ ያስከተለው አንዳንድ ጉዳቶች ለአብነት ያህል ጥቂቶቹን እንመልከት። የተለያዩ አገሮች ብሄራዊ ኩባንያዎቻችውና ፋብሪካዎቻችው አርጅተዋል በመባል እንዲዘጉና ቦታቸውን ለትራንስ ናሽናል ኮርፖሬሽን (transnational corporations) እንዲለቁ በመደረጉ በሰራተኛ ክፍል ላይ ጉዳት እያደረሰ ነው። የፋብሪካ ጥሬ እቃዎችና ምርቶች በቀላሉ የብሄራዊ ድንበር ሳያግዳቸው በዓለም ገበያ እንደልባቸው እያንቀሳቀሱ ናቸው። በመሆኑም የደሃ አገር ገበሬዎች በዓለም ገበያ ተወዳድረው ለምርታቸው ጥሩ ክፍያ ማግኘት አልቻሉም። ከዚህ በተጨማሪ ይህን ሂደት የበለጠ ለማፋጠን በዓለም አቀፍ ደረጃ የነበሩት መዋቅሮች እንዲጠናከሩና አዳዲስ ተቋማት እንዲፈጠሩ መደረጉ ነው። ማለት የሕግ፣ የንግድ ልውውጦች ደንብ፣ የኤኮኖሚና የሶሻል እንዲሁም የፖለቲካን እንቅስቃሴዎችን የሚቆጣጠሩና የሚገድዱ ድርጅቶች ማለትም የዓለም ባንክ፣ አይ.ኤም.ኤፍ. የዓለም የጤና ጥበቃ፣ የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታ ጥበቃ ካውንስል እንዲሁም ወንጀለኞች የሚዳኙበት ፍርድ ቤት የመሳሰሉትን በአዲስ መልክ እንዲዋቀሩና እንዲጠናከሩ መደረጉ ነው።

ሌላው አሉታዊ ክስተቱ የአገሮች መንግሥታት ተጠያቂነታቸው ወይም ታዛዥነታችው ለአገራቸው ማለትም በተለይም የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በተመሰረተበት ተጠሪነታቸው ለመረጣቸው ሕዝብ ብቻ መሆን ሲገባው ለኮርፖሬሽን እንዲሆን ጫና የተደረገባቸው መሆኑን ነው። የኮርፖራሽን ጠበብቶች (corporate elites) እንዲሁም የገደብ የለሽ ነፃ ገበያ (free market) አራማጅ ምሁሮች ግሎባላይዜሽን ግቡን እንዲመታ ጠንክረው በመስራት ላይ ናቸው። በአንጻሩ ደግሞ ተቃዋሚዎች ማለትም የግራ ዝንባሌ ያላቸው ምሁራን የግሎባላይዜሽን ሂደት ለማረም አማራጭ መንገድ በመሻት ላይ ናቸው። የዚህ የተራማጅ ስብስብ አጋር የሆኑ የሠራተኛው፣ የሴቶች መብት ተከራካሪዎችና የአካባቢ ብክለትን የሚቃወሙ እንዲሁም የድሃ አገሮች ተቆርቋሪ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ሌሎችን የሚያጠቃልል በዓለም አቅፍ ደረጃ የፍትሃዊ እንቅስቃሴ (global social justice movement) እንዲሁም አለም አቀፍ ስብሰብ (World Forum) አማካኝነት ጠንካራ ትግል በማድረግ ላይ ናቸው። ስብስቦቹ ገንዘባቸውንና ሃይላቸውን በማስተባበር የዓለምን ሕብረተስብ ንቃተህሊና እንዲጨምር ስብሰባና ጥናት እንዲሁም የተቃውሞ ትዕይንተ ሕዝብ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። የዚህ ተራማጅ ክፍል ከአላማቸው አንዱ ትኩረት የዓለም ሕዝቦች ከለመዱትና ከሚያውቁት የአኗኗር ዘዴና ባህላቸው እንዳይጠፋ ለመከላከልና፣ ስብዓዊ መብታቸው እንዲከበር እንዲሁም ተፈጥሮአዊ ባልሆኑ መንገድ ማለት በኢሞራላዊ ማዳቀል ጥበብ (genetic modified crops and animals)

ምክንያት የሰው ልጅ በረጅም ጊዜ ተመክሮው ያዳበራቸውን ተፈጥሮአዊ አዝርዕትና እንስሳት እንዳይጠፉ ለመከላከል ነው። በአጭሩ በአሁኑ ጊዜ የግሎባላይዜሽን ሂደትና እንደምታ በጭፍን በሚደግፉና ጎጂውን በሚቃወሙ መካከል ትልቅ የሀሳብ ፍጭቶችና ትግል በመካሄድ ላይ ነው። ስለሆነም ለደሀ አገሮች የሚበጃቸው በተገኘው መልካም ግኝታ እየተጠቀሙ፤ ጉዳት ያመጣል ተብሎ የሚታመንበት ላይ በጋራ ከተራማጆች በተለይም ከበለፀጉ አገሮች ተቃዋሚዎች ጋር በመተባበር ለሙብታቸውና ህልውናቸው መታገል ይጠበቅባቸዋል።

## የግሎባላይዜሽን ክስተት

የግሎባላይዜሽን ክስተቶችና እንደምታ ላይ ከመተቸታን በፊት የአሁኖቹ የበለፀጉ አገሮች በተለይም በአብላጫው አሜሪካን ለምንና እንዴት የግሎባላይዜሽን ተጠቃሚዎች ለመሆን ቻሉ? እንዴትስ አሁን ያሉበት የእድገት ደረጃ ደረሱ? የሚለውን ለመመለስ በአጭሩ የእድገት ታሪካቸውን እንመልከት።

## የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት

እንግሊዝና ፈረንሣይ የጦርነቱ አሸናፊ በመሆን የሰሜን አህጉር በደቡብ አህጉር (North vs. South) ሕዝቦች ላይ የበላይነት እንዲቀዳጁ ሆነ። በቬርሳሊስ ውል መሰረት በጦርነት የተገኙ ድሎች ማለት ሃብትና አገሮችን በቅኝ ግዛትነት ለመከፋፈል በቁ። በተገኘው የነፃ ጥሬ እቃዎችና ማዕደናት እንዲሁም የሰው ጉልብት ዝርፊያ እንዱስትሪዎቻቸው በቀላሉ ለማሳደግ ቻሉ። በእድገታቸው ዘመን እያንዳንዱ አገር የየራሱን ጥቅም ለማስከብርና ለመከላከል (protectionism) የሌላ አገር የሸቀጥ ማራገፊያ መሆንን አይፈቅድም ነበር ማለት በቅኝ ግዛታቸው ውስጥ ካለነሱ ማንም ድርሽ አይልም ነበር። በአለም ላይ ሌላ ጦርነት እንዳይነሳ በመፍራትና ሀይለኛው ደካማውን አገር እንዳያጠቃ የሚከላከል በቻርተር የዓለም ማህበር ማለት ሊግ ኦፍ ኔሽን አቋቋሙ። ብዙም ሳይቆይ ማህበሩ ፈይዳቢስነቱን ያስመሰከረው የድርጅቱ አባል የሆነችውን ኢትዮጵያን ሃያሏ ኢጣሊያ ስትወረር ማንም የማህበሩ አባል ሳይደርስላት በመቅረቱ ነበር። ለማጠቃለል የበለፀጉ አገሮች የእድገት ታሪካቸው እንዲህ ሆኖሳለ ታዳጊ ደሀ አገሮች በምን ተዓምር በእኩልነት በነፃ ገበይ ከበለፀጉ አገሮች መወዳደር ይችላሉ? የበለፀጉ አገሮች እንዲያድጉ የተጠቀሙበት አንዱ ዘዴ የብሄራዊ ከበርቴዎቻቸው እንዲጎለብት በመርዳት፣ ለገበሬዎቻቸው ድጎማ በመስጠትና ፋብሪካዎቻቸው እንዲጠናከሩ፣ በማበረታት እንዲሁም ዋናዎቹን የብሄራዊ ሀብት ማለት ማዕደናት፣ ቴሌኮሚኬሽንና፣ ፓርክ እንዲሁም ሌሎችን በመንግሥት ቁጥጥር ስር በማድረግ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የሕዝባቸውን መሰርታዊ ፍላጎት በፈቃዳቸው ባይሆንም በሠራተኛው ትግል ካሚሉ በኋላ ነው

አሁን ስለገደብ የለሽ የነፃ ገበያ የሚሰብኩት።

## *የሁለተኛው አለም ጦርነት*

በአብዛኛው ጦርነቱ የተካሄደው በአውሮፓ ምድር በመሆኑ አውሮፓ ብዙ ንብረትና ሕይወት ጠፋ። የአውሮፓም ኤካኖሚ በመድቀቁ፤ እንግሊዝና ፈረንሣይ ለአሸናፊ ለሆኑት ሁለት አገሮች ማለት ለአሜሪካና ለቀድሞይቱ የሶቭየት ህብረት ሀያልነቱን አስረከበ። አሸናፊዎቹም በ1945 በያልታ ስምምነት መሰረት በድሉ የተገኙትን ተከፋፈሉ። ሁለቱ አገሮች አሜሪካን የካፒታልስት፤ ሶቭየት ደግሞ የሶሻሊስት ርዕዮት አራመጅ በመሆናቸው ዓለም በሁለት ጎራ ተከፈለች። የምዕራብ አውሮፓ ኤኮኖሚ በአሜሪካን ማርሻል ፕላን እርዳታ ተመልሶ እንዲሰራ ተደረገ። ጀርመንም በሁለቱ ሃያላን በሁለት እንድትከፈል ሆነ። አፍሪካ፡ እስያና ላቲን አሜሪካ አገሮችም በፀረ-ኮለንያሊስት ትግላቸው የፖለቲካ ነፃነታቸውን አገኙ። አዲሶቹም ነፃ አገሮች በሁለቱ ሀያላን መካከል ያለውን ልዩነት በመጠቀም ጠቀም ያለ እርዳታ ከሚሰጠው ጋር በመወገን የተወሰነ እርዳታ በተለይም አምባገነን መንግሥታት እንደደርግ፡ የኢራን ሻሁና የኮንጎው ሞቡቱ የመሳሰሉት ሕዝባቸውን ረግጠው እንዲገዙ አስችሎአቸው ነበር።

ሁለቱ ሃያላን አገሮች በጦር መሳሪይ ቴክኖሎጂ አሽቀድድም ማለት በኒውክርል የበላይነትን ለማግኘት ከባድ ውድድር አድርገው ነበር ማለት የቀዝቃዛው ጦርነት ተብሎ የሚታወቀውን ለማለት ነው። ትግላቸውም የሶቪየት ህብረት እስከተፈረካከሰች ድረስ ተከሄዶ ነበር። በሁለቱ መካከል ላለመጨፍለቅና ቀሰቀስ እራሳቸውን ለመቻል የምዕራብ አውሮፓ አገሮች የኤኮኖሚ ጥቅማቸውን ለማስከበር የጋራ ገበያ ማህበር አሁን ወደ አውሮፓ የአንድነት ማህበር የተለወጠውን ለማቋቋም ተገደው ነበር።

ለግሎባላይዜሽን ሂደት መፋጠንና መጠናከር ምክንያት ከሆኑት መካከል በ1980ዎቹ ፈጣን ለውጦች መካከል የሶቪየት መፈረካከስና አዳዲስ አገሮች መፈጠር፤ ነባር አገሮችም እንደ ኢትዮጵያ፡ ቸኮዝላቪያና ዩጎዝላቪያ እንዲከፋፈሉ መደረጉ እንዲሁም አሜሪካ በቴክኖሎጂ የጦር መሣሪይ አማካኝነት የገልፍ ዘይት አምራች አገሮችን ሽያጭና ስርጭት ለመቆጣጠር መቻሉ በመጨረሻም ብቸኛ ልዕለ ሃያል መንግሥት ለመሆኑ መብቃቷ ነው።

## *የግሎባላይዜሽ እንድምታ*

ግሎባላይዜሽ በዓለም ላይ እያደረሰ ያለውንና ወደፊት ሊያደርስ የሚችለውን የፓለታካ፡ የኤኮኖሚና የሶሻል ጠንቆች በተለይም በደሃ አገሮች ላይ ያስከተለውን እንደምታዎች እንመልከት። በአጠቃላይ ግሎባላይዜሽን የሚቀጣጣረው ዘርፎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ (1) የዜናና የመረጃ ማስራጫ

ተክኖሎጂ፡ (2) የሳይንስ ምርምርና አዳዲስ ግኝቶችንና (3) የዓለም ሕዝቦችን ባህል ልምድና አመለካከት እንዲሁም የአኗኗር ዘይቤ በአንድ ወጥነት ለመቆጣጠር ማለት የአሜሪካን አዲሱን ርዕዮትና ባህል ተከታይ ማድረግ ናቸው።

*የፖለቲካ እንደምታው*

የፖለቲካ እንደምታው በብዙ ቅራኔዎች የተወሳሰበና የተወጠረ ነው። በበለፀጉ አገሮች መካከል ያለው ቅራኔ ከልዕለ ሃያሏ ከአሜሪካን የሚመጣውን የንግድ ፉክክርና ጫና በጋራ ለመቋቋም ለምሳሌ የአውሮፓ ህብረት በአንድ ህገ-መንግሥት እንተዳደር የሚለው አንቀፅ መቀበሉ ላይ ገና እያመነቱ ነው። ዋናው ምክንያት አብዛኛው የህብረቱ አባል አገሮች ልዑላዊነታቸውን ለማስረከብ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ነው። በአህጉራችን በአፍሪካ በኩል ያለው ጥረት የአምባገነን መንግሥታት ጨጨታ ማለት የአሁኑ አዲስ አበባ የአፍሪካ መሪዎች ጉባዔ ዓይነት ማለት ተፈጻሚነት የሌለው ውሳኔዎች አሳልፎ መለያየት ነው።

የዜናና የመረጃ ማሰራጫ ተክኖሎጂ ማለት በኢንተርኔት 88% በእንግሊዝኛ፡ 9% በጀርመንኛ፡ 2% በፈረንሣዊኛ እንዲሁም ቀሪው 1% በተለያዩ አገሮች ቋንቋ ነው። የዓለም አቀፍን የዜና አውታረ በሞኖፖል የያዙት የአሜሪካው አሶስየት ፕሬስ፡ የእንግሊዙ ሪዮትርና የፈረንሣዩ አግያንስ ፍራንሴ ናቸው። ስለሆነም የፈለጉትን ያስተላልፋሉ፤ ያልፈለጉትንም ያፍናሉ። እንደአልጂራ ያሉት ለመፎካከር በእንግሊዝኛና በአረብኛ እየሞከሩ ነው።

ሁሉንም የበለፀጉ አገሮች የሚያስማመውና አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ቢኖር በደሃ አገሮች ውስጥ በሚገኙ የለውጥ ፈላጊ ብድኖች/ድርጅቶች ላይ ያላቸው አመለካከት ነው። የምዕራብ አገሮች በተለይም አሜሪካን ስለዴሞክራሲ፡ መልካም አስተዳደር፡ የሰብአዊ መብት መከበር ብዙ ያውራሉ፤ ግን በተጨባጭ የሚረዱት ለውጥ ፈላጊዎቹን ሳይሆን አምባገነን መንግሥታትን እነሱ ያሉአቸውን ለሚፈጽሙት ማለት የግሎባላይዜሽን ሂደት ተባባሪነታቸውን ለአስመሰከሩት ነው። አምባገነኖች ተጠሪነታቸው ለግሎባላይዜሽ ድርጅቶች ማለት የዓለም ባንክና አይ. ኤም. ኤፍ ነው። አምባገነኖች ሕዝባቸው ቢራብ ቢጠማም ቢደኽይም እነሱና ደጋፊዎቻቸው ከርሳቸው ከሞላ ምንም ደንታ የላቸውም። የበለፀጉ አገሮችየብሄራዊ ጥቅም በሚል ሽፋን ከአንድ ትልቅ አገር ጋር ከመደራደር ይልቅ ከትንንሽ ደካማ አገሮች ጋር መደራደሩን ይመርጣሉ። በመሆኑም እንደ ኢትዮጵያ ያለች ባለብዙ የተፈጥሮ ሀብትና ማዕደናት አገር ዴሞክራሲያዊና የተጠናከረች እንድትሆን አይፈልጉም። ለዚህም ለጊዜው ቢሆን ፍቱን ሆኖ ያገኙት ዘዴ እንደ ወያኔ ያሉትን አምባገነን መንግሥታት የሚያራምዱትን የጎሳ

ፖለቲካን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋር መንገድ መደገፍ ነው።

የዴሞክራሲና የግሎባላይዜሽን ሥርዓት በጭራሽ ማይጣጣሙ የተለያዩ ርዕዮቶች ናቸው። የግሎባላይዜሽን የፖለቲካ እንደምታ እንኳን ለደሃ አገሮች ይቅርና ለግሎባላይዜሽን ርዕዮት አራማጇ ለሆነችው ለአሜሪካን እንኳን ብዙ የማይጥማት ጉዳዮችን የያዘ ነው። ለምሳሌ አሜሪካን በዓለም አቀፉ የአስቃቂ ወንጀለኞች ፍርድ ቤት ለመዳኘትና የኪዮቶን የአየር ብክላ የመቀነስ ውል ለመፈረም ለማክበር ፈቃደኛ አይደለችም።

*የኤኮኖሚ እንደምታው*

አዳዲስ ግኝቶችንና የሳይንስ መርምሩን የሚቆጣጠሩ አገሮች ማለት በግንባር ቀደምትነት አሜሪካ፣ በመለጠቅም የአውሮፓ ህብረትና ጃፓን ናቸው። እነዚህ ሦስት አገሮች ለምሳሌ በ1992 በዓለም ለምርምርና ለእድገት ከተደረገው ወጪ $25 ቢልየን የአሜሪካ ብር ውስጥ 82.6% ወስደዋል። ማለት በዝርዝር ሲታይ አሜሪካ 38.5% የአውሮፓ ህብረት 28.6% ጃፓን 15.8% እስያና ራሻ 4% ላቲን አሜሪካን ከአንድ ፐርስንት በታች እንዲሁም አፍሪካ 0.2% ነበር። በመሆኑም የድሃ አገሮችን የኤኮኖሚ መርህ ግብር አዛዥና አድራጊ ፈጣሪው የግሎባላይዜሽን ዋና አካል የሆኑት የአለም ባንክና አይ. ኤም. ኤፍ ናቸው። የድርጅቶቹም ትኩረት ደሃ አገሮች የተበደሩትን የብድር ወለድ (interest) በጊዜ እንዲከፍሉ ማድረግ/ማስገደድ ነው። በመሆኑም ተበዳሪ ደሃ አገሮች ለሶሻል አገልግሎት ማለት ለጤና፣ ለትምህርት፣ ለምግብ በአጠቃላይ ለኑሮ አስፈላጊ ለሆኑት ባጀታቸው እንዲቀነስ ማስደረግ፣ እንዲሁም በአምራቹ ገበሬ ላይ ታክስ መጨመር ከዚያም አልፎ ብዙ ተመክሮ ያካበቱን በሕዝብ ገንዘብ የተማሩትን የመንግሥት ሰራተኞችን ማባረር (structural adjustment) ያካተተ ነው። ይህን የአበዳሪዎች ቀጭን ትዕዛዝ ያለማቅማማት የሚፈጽሙ ለሕዝባቸው ተጠሪነት የሌላቸው አምባገነን መንግሥታትን ለምሳሌ እንደወያኔ ያሉት ናቸው። ለወሮታቸው የሚደረግላቸው እደገት በአገራቸው ውስጥ ሳይኖር እንደአድጉ ተደርጎ የቁጥር ጋጋታ በመደርደርና ምስክርነታቸውንና አጋርነታቸውን ለአምባገነኖች ይለግሳቸዋል።

የግሎባላይዜሽን የኤኮኖሚ ተጠቃሚዎች እንኳን ለደሀ አገሮች ማስብ ቀርቶ ለራሳቸውም የአዋቂነት የፈጠራ ባለቤትነት መጻሕፍት፣ ዘፈኖች፣ እንዲሁም ሌላ ፈጠራዎች ባለቤትነት በብቸኛነት ለማረጋገጥ በውዝግብ ላይ ናቸው። የሚገርመው አገሮች ጥቅማቸውን ለማስከብር በአለም ገበያ ትግል በሚያደርጉበት ጊዜ ደንታቢሱ ወያኔ የኢትዮጵያን የጤፍ ተፈጥሮ ባለቤትነቷን ለሆላንድ አሳልፎ መስጠቱ ነው።

*የሶሻል እንደምታው*

የዓለም ሕዝቦችን ባህል፣ ልምድና አመለካከት እንዲሁም የአኗኗር ዝይቤ

አንድ ወጥነት ለማድረግ በግሎባላይዜሽን የሚደረገው የባህል ወረራ ማለት የአሜሪካንን ባህል ተከታይ ለማደረግ በሲኒማና በቪዲዮ እንዲሁም በቴሌቪዥን በእንግሊዝኛ ቋንቋ ማስታወቂያንና ሌሎችን በመጨመር ይጠቀማሉ። ለምሳሌ በእንግሊዝ አገር ከሚታዩት ሲኒማዎች 80% በፈረንሣይ 60% እንዲሁም የቀድሞዎቹ የምስራቅ አውሮፓ አገሮች ማለትም የቼክ ሪፓብሊክ፣ ፓላንድና ሃንጋሪ 90% የሽያጭ ገቢ የሚሆነው ለአሜሪካ ሆሊውድ ሲነማ አምራቾች ነው። በጥቅሉ የአሜሪካን የሲኒማ ምርት ከ60% በ1944 ወደ 80% በ2000 አድጓል። በአጠቃላይ የአለም ሕዝቦች ባህላቸውን፣ ቋንቋቸው፣ ሃይማኖቻቸውና የአኗኗር ዘዴዎቻቸውን ከባህል ወረራ ለመከላከል በትግል ላይ ናቸው።

*ማጠቃለያ*

በቴክኖሎጂ ወደኋላ ለቀሩ አገሮች እንደ አገራችን ኢትዮጵያ ያሉት ገና የዴሞክራሲያ ሥርዓት ለመመስረትና ለጥሬ እቃዎቻቸው ፍትሃዊ ዋጋ/ክፍያ ለማግኘት እንዲሁም የሕዝቦቻቸውን መሰረታዊ ፍላጎት ለማሟላት ለሚታገሉት በተለይም ለለውጥ ፈላጊዎች ግሎባላይዜሽን ያንያህል ለትግላቸው የሚያበረክተው አስትዋጽኦ የለም ማለት ይቻላል። ያምሆኖ አገራችን ኢትዮጵያም የዓለም ህብረተሰብ አካል እንደመሆኗ መጠን የግሎባላይዜሽን ሂደትና እንደምታ ስለሚመለከታት ሁሉንም ማጥናትና መከታተል ለትግላችን ይተርፋል።

በአሁኑ ሰዓት ቦግ እልም ይበል እንጂ በአንድነትና የዴሞክራሲዊ ሥርዓት ፈላጊዎችና በፀረ አንድነት የግሎባላይዜሽን ጭፍን ተከታዮች መካከል የሞትና የሽረት ትግል አይቀሬ ጉዳይ ነው። ፀረ አንድነት ጎራ ያሉት ወይም ለመሆን የሚዳዳቸው "ወያኔ ጠንካራ ነው፤ የሃያላን መንግሥታት በተለይም የአሜሪካን ድጋፍ አለው፤ ስለዚህ ወያኔን በጠላትነት መፈረጅ አቁመን አብረን እንስራ ማለት በሚመጣው በ2010 የወያኔ ምርጫ እንካፈል" ነው የሚሉት። ምኞታቸውንም ስኬታማ ለማድረግ ውጅንብር መንዛት ላይ ናቸው። ሁለቱ አሻሚና ተቃራኒ የሆኑ ፅንሰ-አሳቦችና የቃላትን አዘውትረው መጠቀም፤ ለምሳሌ የዴሞክራሲንና የግሎባላይዜሽን ሂደትና ሥርዓት እንዲሁም ሥልጣኔና ዘመናዊነት የተለያዩ ፅንሰ አሳቦች ሆነው ሳለ እንድ ዓይነት እንደሆኑ አድርገው ያቀርባሉ። ስለዴሞክራሲና ግሎባላይዜሽን በስፋት ስለተተቸበት፤ ዘመናዊነትና ሥልጣኔ የሚለውን እንድናብራራ ይፈቀድልን። ዘመናዊነት የሚያመለክተው አንድ አገር በቴክኖሎጂን እድገት የደረሰበት ደረጃ የሚያመላክት ሲሆን ሥልጣኔ ግን በሁለንተናዊ መልኩ የሚገልጸው የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚ እንዲሁም የሶሻል ሥርዓቶችን ያካተተ ማለት አስተዳደርን፣ ባህልን፣ ቋንቋን፣ ሥነፅሁፍና ኪነትን፣ ሳይንስ እንዲሁም እምነትን ሌሎችንም በረጅም ጊዜ ታሪክና ተመክሮ የተገነባ መሆኑን ነው። የውጅምብሩን በግንባር ቀደምት ተዋዕኒዎች ሆድ አደር ግለሰቦቹና

ቡድኖቹ ማለት ለወያኔ የሥልጣን ፍርፋሪ ለማጎብደድ ፈላጊዎች የሆኑ የዚህ የዚያ ተቃዋሚ ድርጅት አባል ወይም ደጋፊ ነን በማለት የአገራችንን ሥልጣኔና ታሪክ በመናቅ የዘመናዊ ትምህርት ቤት የፈረንጁን ትምህርት በመማራቸው ብቻ እራሳቸውን ሁሉን ነገር አዋቂ አድርገው የሚቀርቡት ናቸው። ኢትዮጵያን ባህል፣ ታሪክ፣ መልክአ ምድሩን እንዲሁም ችግሮች መንስዔ በቅጡ ሳያውቁና ሳያጤኑ፤ አገራችን ከገባችበት ቀውስ ለመውጣት በሚደረገው መፍትሔ ፍለጋ የሚያቀርቡት አሳቦች እንደ የፈረንሣዊቷ ንግሥት "የተራቡ ሰዎች ጩኸት አይታ ለምን ኬክ አይበሉም" እንዳለችው የሚመስል ዓይነት ነው።

በእርግጥ አገራችን በተለያዩ ምክንያቶች በቴክኖሎጂ ወደኋላ የቀረች መሆኗ አሌ የማይባል ሃቅ ነው። ግን ከዚህ በመነሳት ሥልጣኔ የላትም ማለት ስህተትና ክህደት ነው። እንደው ለነገሩ ነው እንጂ አጉል አዋቂዎችና ጨለምተኞች ይሁነኝ ብለው በአሁኑ ወሳኝ ትግል ጊዜ "እውነቱን እንደውሸት እንዲሁም ውሸቱን እንደእውነትን" አድርገው ውዥንብር ቢነዙ ብዙም አያስገርምም። ይብላኝ ለእነሱ እንጂ "ወያኔ ወዳጅ ነው አብረን ተቻችለን እንስራ" ለሚሉት፤ በከንቱ ለሚደክሙትና ትዝብት ውስጥ ለሚገቡት፤ ሕዝባችን እንደሆን ወዳጁንና ጠላቱን ጠንቅቆ ያውቃል። የኢትዮጵያ ሕዝብ አገሩን የሚወድና ለአንድነቱና ለባህሉ ቀናዊ የሆነና የተፈጥሮ እውቀትና አስተዋይነትን የተላበሰ ነው። ለዚህ አባባላችን ዋቢ ማቅረብ ካለብን በዘመናዊ የጦር መሳሪያ ታጥቆ የመጣውን ጠላት ሕዝባችንን ከዳር እስከ ዳር በመንቀሳቀስና በመተባበር፤ በጀግንነትና በቆራጥነት፣ ጠላትን ድል መተዋል። ሕዝባችንም ብልሃተኛ፣ የጦር አመራርና ስልት ማለት የሽምጥ ውጊይ የሚያውቅ መሆኑን በተግባር ያስመስከረ ነው። ለጠላት በውስጥ አርበኝነት ለሚሰሩ አንጃ ግራንጃ ስልጣኔንና ዘመናዊነትን እንዲሁም ዴሞክራሲንና ግሎባልይዜሽን አንድ እንደሆኑ አድርጎ ማቀረብ ማንንም አያታልልም።

አገራችን በነበራት ሥልጣኔና የጥንት ፌደራላዊ አስተዳደር የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች እንዲሁም ሃይማኖቶች አቅፋ እንዲሁም የተለያዩ ወራሪዎችን በመከላከል ለብዙ ሺ አመታት ለመኖር የበቃችው እንደው በደመነፍስ ወይም በአጋጣሚ ሳይሆን በአባቶቻችንና በእናቶቻች አዋቂነትና አርቆ የማስብ ችሎታ እንዲሁም በከፈሉት መስዋዕትነትና ተጋድሎ ነው። ይህን ሀቅ መካድ ከእውነት ጋር መጣላት ነው። በእኛ በኩል ነፍሱን ይማረውና ሎሬት ፀጋዬ እንዳለው ታሪካችን "ለኢትዮጵያ አንድነት፣ ለዴሞክራሲ፣ ለኩልነትና ለፍትህ" መስዋዕትነት መክፈል ነው። ስለዚህ ባደረግነውና ብምናደርገው የምንኮራበት እንጂ የምንፀፀትበትና የምንሸማቀቅበት ምንም ነገር የለም። የፈለገውን ጊዜ ይፍጅ እንጂ ያለጥርጥር ኢትዮጵያ በታጋይ ልጆቿ የትብብር ትግልና መስዋዕትነት

**አንድነቷን የጠበቀች ዴሞክራሲያዊ ፌደራላዊ ሪፓብሊክ ትሆናለች። እናቸንፋለን!!!**

<u>*ዋቢዎች*</u>


- Herman, Edward, "The Threat of Globalization", New Politics, vol.7. no.2 (new series), whole no.26 Winter 1999.
- Dallmayr, Fred (1998), *Alternative Visions: Paths in the Global Village* (Lanham, Md.: Rowman & Littlefield).
- Giddens, Anthony (1990), *The Consequences of Modernity* (Stanford: Stanford University Press).
- Eriksen, Thomas Hylland (2001), *Tyranny of the Moment: Fast and Slow Time in the Information Age* (London: Pluto Press).
- Falk, Richard (1999), *Predatory Globalization* (Cambridge, UK: Polity Press).
- C. Rangarajan (2006), Responding To Globalization: India's Answer (New Delhi, India)






## ጠላት ምንጊዜም ጠላት ነው
## መጠንቀቅ የሚያሸው ከጉያ ወጥቶ
## ወደ ጠላት ሰፈር ለመግባት የሚያሰፍሰውን ወሰላታን ነው!!

1. በሀገራችን ተከስቶ የሚገኘውን የፖለቲካ፤ ማህበራዊና የኤኮኖሚ ቀውስ ለማስወገድና ፍትህ፤ እኩልነት፤ እድገትና ብልጽግና፤ ሰላምና ማህበራዊ መረጋጋት የሚገኝበት የተቻለ ሥርአት ለመገንባት ትግልን የግዴታ ማለቱ የፖለቲካ ሳይንስ አልፋና ኦሜጋ ከመሆኑ ሌላ ሀገር ወዳዶች ሊያልፉት የማይችሉት ሀገራዊ ግዴታቸው ነው ቢባልም አግባብነት ያለው ይሆናል። ይህ ትግል ውስብስብ፤ ከፍተኛ ውጣ ውረድና እልህ አስጨራሽ በመሆኑም ስኬታማ ለማድረግ መስዋዕትነት መክፈልን ጠያቂ መሆኑ በሁሉም ዘንድ ባይሆንም ቢያንስ ለኛ ግልጽ ነው። ሁለቱን ሥርአት በማስወገድ ሶስተኛውንም ደግሞ ወደ ታሪካዊ መቃብሩ እንደአመጣጡ ለመሸኘት የእድሜ ባለጸጋ ሆነውና በትግል ላይ ከሚገኙት አምባ፤ ትግሉም ሆነ መስዋዕት ክፍያው በተግባር እየታዩ ስለመሆናቸው አሌ ሊባል የሚችል አይደለም። ምንም እንኳ በተወሰነ የታሪክ ወቅትና የትግል ሂደት ስውር አላማቸውን በአደባባይና ግልጽ በሆነ ውይይት ተግባራዊ ማድረግ የማይቻላቸው፤ ለማድረግም አቅሙና እውቀቱ የሌላቸው በተለይም ደግሞ የሥልጣን ጥምና ባልሰሩት ተግባር ልታወቅ ባይነት የሚያጠቃቸው ጥቂት ግለሰቦች በአንጃነት ተቧድነው የተወሰነ ጊዜያዊ ችግር ሊፈጥሩ ቢችልም የጀመርነውን ትግል ግን የቀድሞዎቹ ሊያጨናግፉት እንዳላቻሉ ሁሉ የዘንድሮዎችም ሊያኮላሹት ስለማይችሉ፤ በአሸናፊነት እንደምንወጣው ቅንጣት ታህል ብዥታ የለንም። በአሁኑ ጊዜ ከማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሚጠበቀው የመለስ አገዛዝ አፋኝ ሥርአትን አስወግዶ በምትኩ ዴሞክራሲያዊ ሥርአትን ለመመስረት በሚደረገው ሁለገብና ሀገራዊ ትግል የየበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም። ከዚህ በተለየ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ እየታዘብን እንዳለው ለትግሉ ስኬታማ መሆን ባላቸው አቅም መስዋዕት እየከፈሉ ትግል የሚያደርጉትን ድርጅቶችና መሪዎቻቸውን አባላቶቻቸውንም ጭምር ማጥላላትና ተጨባጭ ሁኔታዎችን በማጣመም እየተደረገ ያለው የውንጀላ ተግባር ከተንኮለኝነት የመነጨ አሳፋሪና አፍራሽ ተግባር መሆኑ ከጥርጣሬ የሚገባ አይደለም። ይህ ደግሞ በተጨባጭ ሲታይ ኢትዮጵያን ከወያኔያዊና ከአጋሮቻቸው የጥፋት ተግባርና የዘረኞች ተውሳክ ለማላቀቅ እየተደረገ ላለው ትግል በዋና እንቅፋትነት ተፈጥሞ ያለውን የመለስ አሽባሪ አምባገነን አገዛዝ የሚጠቅም መሆኑን

የተገነዘቡ ቁጥራቸው ከጊዜ ወደጊዜ እየተበራከተ በመሄድ ላይ ይገኛል። ይህም ያለ ምክንያት አይደለም። ድርጊታቸው ከእርምት ትችት፣ ከገንቢ አስተያየት፣ ለትግሉ ግንባር ቀደም አስተዋጽኦ ከማድረግ ጋር ፈጽሞ የተጣላ በመሆኑ ከመቼውም ጊዜ ግልጽ እየሆነ በመምጣቱ ነው። ውግዘትን፣ ወጊዱልን መባልን እያስከተለባቸው በመሆኑ እርቃነ ስጋቸውን እየቀሩ በመምጣት ላይም መሆናቸው ከየቦታው የሚደርሱን ዜናዎች ያረጋግጣሉ። የሕዝብ ወዳጅ ለመምሰል በተለያዩ መድረኮች እያደረጉ ያሉት ጥራት ውስጣዊ ይዘቱ ከመለስ አገዛዝ ጋር ለመተቃቀፍ የታሰበ እጅ መንሻ መሆኑ ስለተጋለጠባቸው ውርደትን በመከናነብ በቀቢሰ ተስፋነት ውር ውር ሲሉ ይገኛሉ። ፈረንሳዮች ውርደት ከየትኛውም መሳሪያ የበለጠ ይግደላል የሚሉት ያለምክንያት አልነበረም። የጠቀረ ምሽት የቀኑን ውበት ያሳያል እንደሚባለው በነሱ መሰሪ ተንኮል የኢሕአፓን ማንነት፣ ውስጠ ባህሪዩን ጭምር ከመቼውም በበለጠ ለሕዝባቸው ቀናኢ አስተሳሰብ ላላቸው ለብዙሃኑ ግልጽ ሊሆን ችሏል ቢባል ሀቁን መናገር እንጂ ሌላ አይሆንብንም። እነዚህ ሀገር ወዳድ የሆኑ ማህበርሰብ ክፍሎች የመለስ አገዛዝን ለማስወገድ የሚደረገው ትግል ጥንካሬና ስኬታማ ይሆን ዘንዳም መልካም የሆነ ምክራቸውን ለግሰዋል። ከቀና ድርጅቶች ጉያ ወጥተው ትግሉን ለማሰናከል የሚጥሩትን ክፍሎች እንዳመጣጣቸው ቾል ሳይባሉ በቁርጠኛነት በመታገል አገዛዙን ለማስወገድ ግን የሀገር ወዳዱና በሕዝቦቿ እኩልነት ላይ የተመሰረተ በኢትዮጵያ ሀገራዊ አንድነት ላይ የሚያምኑ ታጋዮችን ለማስተባበር የራስን እንቅስቃሴ በማያደናቅፍ መልኩ የተጀመሩትን ጥረት አሁንም እንደቀድሞው በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀጠልበት እያሳሰቡ ይገኛሉ። ይህንን ሀላፊነት የተሞላበት ጥሪ ማድረጋቸው የሚደገፍ ነውና በሱ ዙሪያ የሚነሱትን አንዳንድ ነጥቦችን ማንሳቱና ግልጽ ማድረጉ ተገቢነት ያለው ነውና እነሆ እንላለን።

2. ባለፉት ጊዜያት ለመገንዘብ እንደተቻለው ከተግባር ይልቅ ማውራቱ ጎልቶ በመገኘቱ "ተባበሩ ወይንም ደግሞ ተሰባበሩ" የሚለው መፈክር ለሰሚ ጆሮ እስኪሰለች ድረስ ለመነገር ምክንያት ሆኖ የነበረ መሆኑ የሚታወስ ነው። እንዲያውም ይህንኑ መፈክር በተለይ ከትግሉ ዳር ቆሞ ተመልካች በሆነው ዘንድ እንደተፈለገ የተወረወረ ብቻ ሳይሆን ይሁነን ተብሎ ከመለስ አገዛዝ ባልተናነሰ መልኩ የተወሰኑ የፖለቲካ ቡድኖችን በተለይም ደግሞ የተለየ የትግል ሥልት ያላቸውን ለማጥቃት ስውር መጠቀሚያ ለማድረግ እንደተቻለ የሚታወስ ነው። ምክንያቱ ደግሞ ግልጽ ነበር። እነዚህ የተለየ የትግል ሥልት ያላቸውን ተቃዋሚ ክፍሎች በተለይም ኢሕአፓ ላለፉት አስረተ አመታት ሕዝባችንን አንቀው የያዙትን ችግሮች አመቺ መስሎ በታያቸውና ትግሉ በጠየቀውና ግዴታ ባለበት ለማስወገድ የራሳቸውን አስተዋጽኦ ያበረከቱና እያበረከቱ ያሉ፣ ብዙ የታገሉና ከፍተኛ መስዋዕትነትም የከፈሉ፣ በዚህም ተስፋ ባለመቁረጥ አሁንም እየተንቀሳቀሱ ያሉ በአርአያነታቸውም

ሆነ በሕዝብ አለኝታነታቸው አኩሪ ታሪክ ያላቸው በመሆናቸው ነው። በሀገር አንድነትና በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ ከቶምና መቼም አልደራደርም የሚለው ኢ.ሕአፓ አሁንም በትግሉ አውድማ መገኘት ለብዙዎች አሎሎ እሳት ሆኖባቸው ያለ በመሆኑም ጭምር ነው።

3. የመተባበሩ ጉዳይ ሁሉም በሚመኘው ደረጃ አለመሳካቱ፤ በድርጅቶች መካከል ንትርክ መኖሩ ወይንም ደግሞ መከፋፈልም ሆነ አንጃ መፈጠሩ ብዙውን የሚያሳዝን ቢሆንም ላለመሳካቱ ከአንዳንዶች የሚሰጠው ምክንያት ግን "ከመፈላለግ ይልቅ መጠላለፍ አለ" በሚል ማቅረቡ ስህተት ብቻ ሳይሆን የነገሩን ጭብጥ ለማሳሳት ከሚደረግ ሙከራ ሊያልፍ አይችልም። ትግልን ወደኋላ ጎታች እንጂ ቅንጣት ታክል ወደፊት የሚያራምድ፤ ለሁኔታውም ጥራትና መልካም ግንዛቤ የሚያስገኝ ሊሆን አይችልም። በአሁኑ ወቅት ሕዝብም ሆነ ታጋዩ ክፍል ባለፉት ጊዜያት ከተደረጉት የመተባበር ጥረቶች በርካታ ተመክሮዎችን ቀስሟል ብለን እናምናለን። ማን ለሕዝቡ እንደቆመና ማን ደግሞ በአስመሳይነት እየተንቀሳቀሰ እንዳለ በሚገባ የሚያውቀው ነው። ቀን ተቃዋሚ ሲመሽ ደግሞ ከአገዛዙ ቱባ ቱባ ባለሥልጣናት ጋር አሸሼ ገዳዎ ከሚሉ አስመሳይ ታጋዮችና እንመራዋለን ከሚሉት ቡድን ጋር በምንም አይነት ተአምር የትግል መተማመን ሊፈጠር እንደማይቻል ሳይታለም የተፈታ ነው። እነዚህ ሰልፋቸው ከጠላት ጎን እንጂ በምንም አይነት በተቃዋሚነት ስም ከሕዝቡ ጎን እንዳይደሉ ተግባራቸው በበቂ የመሰከረው ነው። ይህ ተመክሮ ሁሌም ከግንዛቤ መግባቱ ጠቃሚነቱ የጎላ ነው። ስለሆነም አስመሳዩ ከታጋዩ ተለይቶ እንዳይቀመጥ ሁኔታውን ለማድበስበስ ካልተፈለገ በስተቀር በነዚሁ ሁለቱ መካከል ሕብረትና ትብብር ማግኘት እንደማይቻል ግልጽ መሆኑ ከሕዝብ ግንዛቤ ውስጥ ከገባ አመታትን አስቆጥሯል ቢባል ከስህተት የሚጥል አይደለም። የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረትን ለመመስረት በተደረገው ሂደት በግልጽ የታየ በመሆኑ ምስክር መጥራት የሚያሻ አይሆንም። የመለስ ቡድን "ጠላታችን አይደለም ወይንም ተቃራኒ ሳንሆን የተለየ አቋም ያለን ነን"፤ "ከኢሕአደግ ጠብ የለንም" ተብሎ ሲስተገባ የነበረውና አሁንም በአንጃነት ብቅ ባሉት ክፍሎች አማካኝነት ቀደም ብሎ ውስጥ ውስጡን ተብላልቶና አሁን በግላጭ ሊወጣ እንደቻለው ከወያኔ ለመጠጋት ዳዴ ከሚሉ ጋር ተመልሶ በአንድነት ለመሥራት እንደሚያስቸግር መገንዘቡ አዳጋች አይሆንም። በአንጃኛነት የተከሰቱ ጥቂት ግለሰቦች ስህተታቸውን ተገንዝበው ወደ እናት ድርጅታቸው ተመልሰው እንዲቀላቀሉ ለማስቻል ግፊት የሚያደርግ ማንኛውም ግለሰብም ሆነ ቡድን በተለይም ደግሞ በአስታራቂነት የሚሰማራ በአገዛዙና በደጋፊዎቹ ብሎም በዳዴ ባዮች ላይ እየቀረበ ያለውን የመረረ ትችትና ብሎም ከሌላው ነጥሎ ለማስቀረት የሚደረገውን ትግል ለማኮላሸት የሚደረግ ስምሪት እንጂ በሌላ በምንም ሊፈረጅ አይችልም። ይህ ደግሞ የኋላ ኋላ ሀገር ወዳዱን

በአገዛዙ ለመጥለፍ በመስለቢያነት ሊያገለግል ይችላልና ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል አይሆንም። የዚህ አይነት እንቅስቃሴ ሕዝብን ለመረማመጃ ታጋይን ለአጋዥነት ድግስ ማሰናዳት ነው። ለወሳኝ ትግል የሚያነቃቃ ሳይሆን የሚያኮራምት፤ የሚያበረታታ ሳይሆን የሚያዳሽቅና የሚያዘናጋ ነው። ከብት እንጂ ታጋይ የሆነ የሰው ፍጡር ከአራጁ ጋር እንዲውል መሞከር ከስህተትም በይቅርታ ሊታለፍ የማይችል ስህተት መሆኑ ባይረሳ መልካም ይሆናል። ኢሕአፓ ለዚህ ዝግጁ የሚሆን ሳይሆን አጥብቆ የሚታገለው መሆኑ በግልጽ ሊታወቅ ይገባል እንላለን።

3. ማንኛውም ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ሕዝባዊነትን እስከተላበሰና በብዙሃኑ ሕዝብ እስከተደገፈ ድረስ ለወቅቱ ተስማሚ የሆነ የትግል ሥልት ይኖረዋል። ማንኛውም ታጋይ ከልቡ ለትግሉ ቆርጠ ከተነሳ የትግል ሥልቱን የመምረጡ ሃላፊነት የግሉና በሚኖረው የርዕዮተ አለምና እይታ ግንዛቤ መሰረት የግድ በሚለው የሚወሰን ሲሆን በዚህ ጥያቄ ላይ እንካ ሰላንቲያ የሚገጥም አይኖርም። የስልቶቹ ትክክለኛነት መፈተኛው የትግሉ አውድማ ነውና የሁሉም ትኩረቱ በዛ ላይ ሊሆን ይገባል። ይህ በንዲህ እንዳለ በግልጽም ሆነ በስውር ከጠላት ጉያ ለመግባት የሚደረግ ሽር ጉድ ተደርጎ አላዋጣ ሲልና ተቀባይነትም እያጣ መሄዱ ተሰፋ አስቆርጠ በሌላ በተዘዋዋሪ ለሕብረት ለመታገል ራስን ለማጨት መዳዳቱ የሸሹትን በሌላ መለክ ለማጥፋት ቢያንስ ለማዳከም የሚደረግ የተንኮል ጥረት ነውና ከሀገር ወዳዱ በኩል አስፈላጊው ተቃውሞ የሚገጥመው መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ይህንንም የግል አጀንዳዎቻቸውን ስኬታማ ለማድረግ ለንደዚህ አይነት ክፍሎች ይፋም ሆነ ስውር ድጋፍ የሚያደርጉትን በምንም አይነት በቸልታ የምንመለከታቸው እንዳለሆነ ግልጽ ሊሆን ይገባል። እነዚህ ከዋናው ጠላት ባልተናነሰ ደረጃ በኢሕአፓ ላይ እየዘመቱ ያሉ ክፍሎች ቀደም ብሎ በተመሳሳይ ሁኔታ የተገለሉ አጥፊና ከፋፋይ ግለሰቦች ድጋፍ ማግኘት ተመሳሳይ ላባ ያላቸው አብረው ይበራሉንን ያስታውሰናልና ቀጥሉበት እንላለን።

4. ደጋግመን ለመግለጽ እንደሞከርነው የትግል ሥልትን ለመቀየስ ተጨባጩን ሁኔታ በሚገባ ዘርዝሮ መተንተንን፤ ከጭፍን ጥላቻ በመራቅ ሆኖም ግን ጠላትንና ወዳጅ በቅጡ መለየትን፤ የሃይል አሰላለፍን በሚገባ ማወቅን፤ የሕዝብ እንቅስቃሴዎች ድክመታቸውንና ጥንካሬያቸውን አብጠጥሮ ማወቅን፤ የፖለቲካና የኤኮኖሚ ሥልጣንን በቁጥጥሩ ሥር ያደረገውን ቡድን በተለይም ቀንደኛ ወኪሎቹን ማንነት በሚገባ መረዳትን፤ የትኛው የኤኮኖሚ አውታር በማን እጅ እንዳለ ተከታትሎ ዜና ማግኘትን፤ የታጋዮች የትግል ቅንብር በምን ደረጃ ላይ እንዳለ መገንዘብን፤ የትግሉ ራዕይ፤ ግብና ኢላማ ማወቅን፤ ለጠላት ክፍት ሆኖ አለመገኘትን፤ ሚስጢርን ለማይመለከታቸው ሁሉ አለማዝረክረክን፤ ከባዕዳን ባለሥልጣናት ጋር

የሚደረጉ ግንኙነቶች ከሕዝብ ጀርባ እንዳይሆኑ መታገልን የነሱንም እንቅስቃሴዎቻቸውን በቅጡ መከታተልን፤ የሕዝቡን ታሪክ፤ ባሕሪይ፤ ባሕልና እምነትን፤ ጥቅሙንና ፍላጎቱን በሚገባ ማወቅን ይጠይቃል። በርካታዎች ከስህተት እየወደቁ ያሉትና የኋላ ኋላ በመለስ አገዛዝ መዳፍ ሥር ወድቀው የታሪካ አተላ የሚሆኑት ይህንን የሕብረተሰብ መሰረታዊ ፍላጎትና ምኞት በቅጡ ባለመገንዘባቸው አለበለዚያም እድሜ ሲገፋ አርቆ የማሰብ ችሎታ እየጎደላቸው የተጣመመ አመለካከት ሊይዙ በመቻላቸው መሆኑ ከጥርጣሬ አይገባም።

5. በትግል ስልቶቹ ላይ ልዩነቶች መኖራቸው የሚጠበቅና መከበር የሚገባው ሲሆን ትኩረት መስጠት የሚገባው በስልቶቹ ላይ ሳይሆን በየትኛውም ቢሆን ቆርጦ በመታገሉና ሕዝብን እያደራጁ በማታገሉ ላይ ሊሆን ይገባዋል። ሕዝብ የራሴ መንግሥት የሚለውን እስኪመሰርት ድረስ ትግሉን በየደረጃው እንደሁኔታው ማካሄድ፤ ግብታዊውን ከተቀናበረው ጋር ማቀራኘት፤ የከተማውን ከገጠሩ፤ የአስተማሪውን ከተማሪው፤ የወታደሩን ከሕዝቡ፤ የነጋዴውን ከሸማቹ፤ የፖለቲካውን ከሕዝባዊ ድርጅቶችና ከእቁቦች፤ እድሮችም ሳይቀሩ እያጣመሩ የመለስ አገዛዝን በሚገባ ማስጨነቅ እንጂ የተለየ የትግል ስልት ባላቸው ላይ መሰመራቱ በተጨባጭ ሲታይ ጥቅሙ ለአገዛዙ ብቻ ነው።

6. በስጋት ደረጃ እየተባለ ሆኖም ግን የራስን ድብቅ አላማ ለማስረገጫ እንዲያገለግል እየተቀነቀነ ያለው ሀሳብ በጠመንጃ የሚደረግ ሹም ሽርን የሚመለከት ነው። ሀሳቡ በመመኘት ደረጃ መልካም ቢሆንም በወደፊቷ ኢትዮጵያ ሌላ አዲስ አምባገነን ከሥልጣን መቀናጠጥ አለመቀናጠጥ የሚወሰነው በወቅቱ የትጥቅ ትግል ስለሚካሄድ ሳይሆን የባዕዳን ጣልቃ ገብነት እንዳለ ሆኖ በመሰረቱ ባለው አገዛዝ ጠባይና በሚከተለው ፖሊሲ፤ በሚያከናውናቸው ተግባራት በአንድ በኩል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝቡ መብቱን ለማስከበርና ነጻነቱን ለመጎናጸፍ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች የመዳከምና የመጎልበት ድምር ውጤት መሆኑን የሚዘነጋ ነው። ማንም የደህንነትና በሰላም ለመታገል የሚያስችል ዋስትናና የፖለቲካ አየር ለመስጠት የሚችል የመለስ አገዛዝ ተቃዋሚ የሆነ ቡድን ሆነ ግለሰብ ሊኖር ስለማይችል ተወደደም ተጠላ መሳሪያ አንግቦ የሚታገለውን ቡድን ትጥቅህን አውርድና የወያኔን ሕገ አገዛዝ አክብረህ በሰላማዊ መንገድ ታገል ብሎ ለማለት ማንም የሞራል ሃላፊነት የለውም። የሚቀበለው ሊኖር አይችልም።

እርግጥ ነው። የፖለቲካ ሥልጣን የሚፈለገው፤ ጠለቅ ተደርጎም ለሱ ትኩረት የሚሰጠው ሰላማዊና የበለጸገች፤ በዴሞክራሲ ሥርአት የምትተዳደር እንዲት ኢትዮጵያ እውን ለማድረግ ነው። የትግላችን አላማም በዚህም ተባለ በዚያ በሕዝባዊ ምርጫ የስልጣን ሽግግር ሊኖር የሚችልበትን ሥርአት፤ የሕዝቡ የነጻነትና ሰብአዊ መብቶች ያለገደብ ሊከበሩ የሚችሉበትን ሁኔታ

ማመቻቸት ነው። ጠላ ካልተጠጣ አላማውን ስቷል የሚለው የአነጋገር ዘይቤ ይህንን መሰል ሁኔታ ለመግለጽ ነው እንጂ ለሌላ አይደለም። መብትና ግዴታን ማወቅ በአንድ በኩል፤ በሌላ በኩል ለመብት መከበር ቆርጦ መታገልና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆን የተለያዩ ናቸውና።

ስለዚህም ሀገር ወዳዱ ቡድን በሚገባ ተደራጅቶ ራሱንም አጠናክሮ ሕዝብ የቀን ተቀን ኑሮዉን እየኖረ መብትና ግዴታውን እንዲያውቅ እየቀሰቀሱ በትግሉ ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት ካልተደረገ ለአምባገነንነት ምቹ ሁኔታ መፈጠሩ የማይቀር ነው። የዚህን ጊዜም ከሕዝብ ፍላጎትና ጥቅም የተለየ ተልዕኮ ያላቸው ቡድኖች በሰላማዊ ተባለ በመሳሪያ ሀይል ከሥልጣን ለመቆናጠጥ አመቺ ሁኔታ ይፈጠርላቸዋል። የተወሰኑ ምሁራን ተበዬዎች ሕዝብን ለማደራጀት እንቅስቃሴ ሳያደርጉ ኡኡታ ብቻ በማሰማትና ወይንም በማስጠንቀቅ ብቻ ከተወሰኑ የሚፈራው ነገር መከሰቱ አይቀሬ ነው። ለነገሩ ከትግል ውጭ ማንም ቢሆን የሚፈራው የአምባገነንነት ጉዳይ ለወደፊቱ ላለመከሰቱ ወይንም ደግሞ አስተማማኝና ፍትሃዊ ሥርአት ሁሌም ከሰላማዊ ትግል ብቻ ይወለዳል የሚል የማረጋገጫ ዋስትና የሚሰጥ ሊኖር አይችልም። ማንኛውም የቀውስ ሁኔታ መሰረታዊ ለውጥን ያረገዘ ቢሆንም አይጨናገፍም ወይንም ያልተፈለገው አይወለድም ማለት አይደለም። የደርግም ሆነ የወያኔ ከሥልጣን መውጣት የሚያመለክተን አንድ ሀቅ ቢኖር ይህንኑ ነው። ባለፉት ጊዜያት የተደረጉት ጸረ ወያኔው ትግሎችም ድልን ሊቀዳጁ ሲገባቸው በመሃል ተደናቅፈው ዛሬ የተከሰተውን ክስተት ለማየት ተገደናል። የወደፊቱን አማትሮ በማየትና አርቆ አሳቢነትን መሰረት በማድረግ በዚህ ጉዳይ ላይ እሰጥ እገባ መግባቱ ከእንኪያ ሰላንቲያ በስተቀር የሚያመጣው ጥቅም የለም በሚል ዝም እየተባለ እንጂ እንነጋገር ከተባለማ የዚህ ኡኡታ ባለቤቶች ባለፈው የገማ ሥርአት ዋና አቀንቃኝ፤ አለበለዚያም ዋና ተካፋይና አገልጋይ የነበሩ ለመሆናቸው የታሪክ ማህደራቸውን ማገላበጥ ብቻ በቂ ነው። በሌለው ጠባይና ባሕርይ እንዲሁም ፍላጎት በጊዜ ሂደት ወያኔን ዴሞክራት ለማድረግ የተደረጉት ጥረቶች ውጤት አልባ መሆናቸው ባይዘነጋ ለሁሉም መልካም በሆነ ነበር። ስለሆነም በዛው በሰለቸና ውጤት አልባ በሆነ ጎዳና መጓዙ ስህተት ከመሆኑ ሌላ ከሌላው ሙከራዎቻቸው ጋር ሲደመር በተጨባጭ አገዛዙን ማገዝ ስለሆነ አሁንም እንደወትሮው ታረሙ የሚል ምክር በመስጠት ብቻ እንድንወሰን ያለንበት ሁኔታ እንደማይፈቅድልን ቀዩ መስመርን ማለፋቸው የሚያስገነዝበን ነው። አንድ እርምጃ ወደፊት ተኪዶ እንደአመጣጡ መመከት የግድ የሚል ነው። ከዚሁ ጋርም ተያይዞ የኢትዮጵያ ሕልውና አደጋ ላይ ወድቋል በሚል ማጠየቂያ ከአገዛዙ ጋር ለመቆራኘት ደፋ ቀና እየተባለ የሚስተጋባውና ተግባራዊም ሆኖ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰው መተቃቀፍ ለአገዛዙ ጠቀሜታ አስገኘ እንጂ

የሚፈለገው ሰላምም ሆነ የፍትህ ሥርአት ሊወለድ አልቻለም። ከሻዕቢያ ጋር በተደረገው ጦርነት በመቶ ሺ የሚቆጠር ዜጋ ሕይወቱን ቢከፍልም የመለስ አገዛዝ የሥልጣኑን እድሜ ለማራዘም አስቻለው እንጂ መልካም አስተዳደር ሊመሰረት አልተቻለም። ከባድሜ መለስ ወደ መለስ የተባለው የማደናገሪያ መፈክር የውሃ ሽታ ሆነ ቀረ እንጂ ለሕዝብ ጠቀሜታ አልስገኘም። በሶማሌ ከፍተኛ የሕይወት ግብር እያስከፈለ ይገኛል። አሁን እንደሚታየው ደግሞ ሌላ ተጨማሪ ሕይወት ሊያስከፍል ችግሩ አቆብቁቦ ይገኛል።

7. ወያኔዎች ከምንም በላይ የሚፈሩት ስለ ሰላማዊ ሆነ ስለ ትጥቅ ትግል ማውራቱን ሳይሆን በየትኛውም የትግል ሥልት ይሁን እነሱን ቆርጦ የመታገልን ሁኔታ ነው። “ጦርነት መስራት እንችላለን” የሚለው ፉከራና ለሰሚ ጆሮ የሰለቸ የማስፈራሪያ ጩኸታቸው ሥልጣን በጅ ከገባ በኋላ እንዳታፈተልክ የሚደረግ እንጂ መስራቱ ለነሱ ብቻ በስጦታ የታደሉት እውቀት እንዳልሆነ ማንም ያውቀዋል። ሕዝብንም ለመከፋፈል ወያኔዎች ልዩ ተአምር ሰሪዎች ሆነው ሳይሆን ለጊዜው ሕዝባችንን ለንደዚህ አይነት ተግባር አመቺ ሆኖ እንዲገኝ ተለጣፊዎች በረግረግነት መጠመቀሚያ ስለሆኑ ብቻ ነው። ክብርን በነውርነት፤ ሹመትን በቅሌት ማግኘት የሚሹ መድረኩን በማጨናነቃቸው ብቻ ነው።

8. ህገራችንና ሕዝባችንን የገጠሟቸውን ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት በሚል ማጠየቂያ ከወያኔ ጋር ለመጎዳኘት ሰላማዊ ትግልን በብቸኝነት የሚያቀነቅኑት ባብዛኛው በዋቢነት እያስቀመጡ ያሉት ጋንዲን፤ የሰላም ኖቤል ተሸላሚ የሆኑትን ማንዴላን አሁን ደግሞ ውይዘሮ ሳን ሱ ኪ ቢሆንም ይህንን ስልት በልጥጡ ወደ ቀኖናዊነት እየለወጡት ይገናሉ። ፅሁፎቻቸውን ቢጠቃቅሱም ለነሱ በሚስማማቸው ደረጃ እንጂ ለጥራትና ግንዛቤ እንዲገኝ በሚመች መልኩ አይደለም። መደሻ ባለበት ቦታ ሁሉ ነገር ምስማር መስሏቸው ከሆነም ስህተት መሆኑን ማወቅ አስቸጋሪ አይደለምና ቢያስቡበት መልካም ይሆናል።

9. በበኩላችን ሰላማዊ ትግል ሁኔታው አመቺ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ ቅድሚያ የሚሰጠውና በሚገባ መጠቀምም አስፈላጊ ሲሆን ሁኔታው አላመች ካለ ደግሞ አማራጭ የትግል ሥልትን መጠቀሙ ተገቢም ህገራዊ ግዴታ ነው ብለን እናምናለን። ደጋግመን በተለያዩ መጣጥፎቻችን ለመግለጽ እንደሞከረነው ሰላማዊ ትግል በዋናና በመርህ ደረጃ ፖለቲካዊ ይዘት ያለው አመጽ ማለት ነው። እምቢኝ፤ አልገዛም፤ በቃኝ አሻፈረኝ ማለት እንጂ ከአገዛዙ ጋር በመተቃቀፍ በመቻችል እየተበደሉና እየተረገጡ መኖር ማለት አይደለም። የአገዛዙን ሕጎች አላከብርም ብሎ እንቅስቃሴ ማድረግ ነው። የነጋንዲ፤ ሊተር ኪንግ፤ የፓሌስቲና፤ የሶዌቶ እንዳሉ ሆነው ከራሳችን በ1966 ዓ.ም. ሰኔ 1997 ዓ.ም. ያሳዩን ይህንኑ ነው። የመለስ አገዛዝን ሕግ ተከትሎና አክብሮ ለመብትና ለነጻነት መገኘት ሊካሄድ የሚችል ትግል የለም። ሊኖርም አይችልም። በሕቡዕ መታገል ዛሬም ቀጣይ ሆኖ የተገኘው

በዚህ መልክ መንቀሳቀሱ ለትግል ቀና ሆኖ ወይም ተመርጦ ሳይሆን አገዛዙ ሰላማዊ ትግልን ስለማይፈቅድ ብቻ ነው። ሰላማዊ ትግልን ወያኔ እምቢ አለ ተብሎ ደግሞ ትግሉ መቆም ስለሌለበት በማንኛውም መንገድ መቀጠሉ ከአግባብም አግባነት ያለው መሆኑ ቀናኢ ሕዝብ የሚመኘውና የሚደግፈው ነው። የተወሰኑ ጥቂት ግለሰቦች ከኢሕአፓ ጉያ ወጥተው ወያኔን ወያኔ ማለት ስላልፈለጉ፤ የሚያወግዙበት አንጀትም በማጣታቸውና በየቦታው እየዞሩ የአዞ እንባ እያፈሰሱ ከመለስ አገዛዝ ለመተቃቀፍ ወይንም ተቻችለው ለመኖር ሲሉ ለዘመናዊ የትግል እሳት አጥፊነት ራሳቸውን ስለዳረጉ ይፋ ወጥተን በተራና ደም በጠማቸው የወያኔ ካድሬ እንደ ቆሎ እንድንታፈስ የምንፈልግ አለመሆናችንን አለማወቃቸው ከስህተት ቢጥላቸው ተጠያቂ የሚሆኑት ራሳቸው እንጂ ሌላ ማንም ከቶ ሊሆን አይችልም። ወያኔን በእምቢተኛነቱ፤ ሰላምን አሻፈረኝ ማለቱን ሊያወግዙት፤ ወያኔን ወያኔ ሊሉት አለመፈለጋቸው ምስጢሩ ይኸው እንጂ ሌላ አይደለም። የደቡብ አፍሪካ የሰላም ኖቤል ተሸላሚ የሆኑት ማንዴላ ወደ ነጻነት የተደረገ ረዥም ጉዞ በተሰኘ መጽሃፋቸው "በ 1969ን ዓ.ም. የሰላም ትግሉ ቀናት አከተመ። ወደ ትጥቅ ትግሉ ከመሰማራት ሌላ ምንም ምርጫ አልነበረንም"" በማለት በገለጹበት ወቅት በማጠየቂያነትም የተጠቀሙት "የጫካ እንስሳ ሊያጠቃ ሲነሳ በባዶ እጅ ራስን መከላከል አይቻልም" የሚለውን የአፍሪካ የአነጋገር ዘይቤን ነበር። ይህንን ሃሳባቸውን ከትግል አጋሮቻቸው ከሆኑት ውስጥ አንዳንዶቹ "የሰላማዊ ትግል የማይናወጽ መርህ እንጂ ጥቅም የለሽ ሲሆን እንደተፈለገ የሚተው በታክቲክ ደረጃ የሚታይ አይደለም" በማለት ተቃውሟቸውን ባቀረቡበት ወቅት የመለሱት "የኔ ሃሳብ በተቃራኒው ነው። ሰላማዊ ትግል ወደፊት የማያስኬድ ሆኖ ሲገኝ የሚተው ታክቲክ ነበር። ሕዝባችንን ምንም አይነት አማራጭ ሳናቀርብለት ለመንግሥት የመሳሪያ ጥቃት ማጋለጡ ስህተትና ወንጀልም ነው" የሚል ነበር። በዚህ መልክ ማንዴላ የገጠማቸውን ተቃውሞ በወቅቱ ሊያለዝቡ ችለው ነበር። ማንዴላ ግን ቀኖናዊና ግትር ስላልነበሩ ሁኔታው ለሰላማዊ ትግል አመቺ ሆኖ ሲገኝ ትግላቸውን በሰላማዊ መንገድ ቀጥለው ድርጅታቸው ለሥልጣን ሊበቃ ቻለ። ሕዝባቸውም የፖለቲካ ነጻነቱን ሊጎናጸፍ በቃ። ሥልጣን ከጨበጡ በኋላ ደግሞ በሜይ 7 ቀን 2000 ዓ.ም. በአሶሲየትድ ፕሬስ እንደተገለጸው ሕጻናቶች ሲራቡ በሙስና የተበከሉና ብዙ ሀብት ያካበቱ መንግሥታቶችን ለማስወገድ መሳሪያ እንዲያነሱ ጠይቀው እንደነበርም ሊጠቀስ ይችላል።

10. ማንዴላ የተናገሩትን በማንዴላነቱ እናስቀምጠውና ወደኛዎቹ ስንመለስ ግን በሰላሙ የትግል ስልት መደረግ የሚገባውን ማድረግ ሳይሆን የተለየ በአማራጭነትና በአጋዥነት የሚቀርበውን መኮነን ነው የተያያዙት። አንዳዶቹማ ከአፋኝ ሥርአት ወኪሎች ጋር ግብግብ ከመግጠም ይልቅ የእማሬ ጣታቸውን ያነጣጠሩት ለሕዝባችን እኩልነትና መብት መገኘት በሚታገሉት ላይ ነው። የመለስ አገዛዝን አጥብቆ በመታገል ፈንታ እሱን

የሚታገሉትን ሀገር ወዳዶችን በዘመናዊ ፖለቲካ በሚል አፍ ማሟሻ መዝለፍ እንደ ከፍተኛ ሞያ ተያይዘውታል። በግልጽም ሆነ በስውር ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ጠቅለል ብሎ ሲቀርብ ሀገር ወዳዱን ታጋይ ከመለስ አገዛዝ ቱባ ቱባ ባለሥልጣናት ጋር በወረቀትና በቃላት ጋጋታ እየተጎነታተሉ መኖርን እንደ ትግል አድርጎ እንዲወስድ፤ እሱ በቀደደላቸው ቦይ ብቻ እንዲሟልሉላቸው ነው። ይህ ደግሞ በፍጹም ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል እንዳልሆነ እነሱም ያጡታል ብሎ ማሰብ የሚቻለን አይደለም። አይ ካሉና በሚያስቡት ጎዳና ከቀጠሉ የታረደች በግ እስክትሞት ድረስ ትንፈራገጣለች ነውና ነገሩ መንገዱንም ሆነ ስለቱን ማቅረቡ የሚገደን እንዳልሆነ ግን ሊያውቁት ይገባል እንላለን።

11. ለማንኛውም ጠላት ምን ቢደልሉት ወዳጅ አይሆንምና እስቲ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እናቅርብና የዛሬ መጣጥፋችንን በዚሁ እንቋጨው።

ሀ. የኢትዮጵያ ሕዝብ ከምንም በላይ ከበሬታና ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጣቸውን የተፈጥሮ ነጻነትና ሰብአዊ መብት በማን አህሎኝነት እየረገጠና በሕዝብ ላይ በደል የሚያደርስ የመለስ አገዛዝ በጠላትነት ካልተመደበ በምን ሊፈረጅ ይችላል? የሱ አጨፋሪዎችንስ ከየት ጎራ መመደብ ይቻላል?

ለ. በእብሪታቸውና በሕገወጥ ድርጊታቸው፤ በሙስና ተግባራቸው የተጋለጡ የአገዛዙ ከፍተኛ አባላትን በሕግ እንዳይጠየቁ የሚያደርግ አገዛዝ ምን ስያሜ ይሰጠዋል?

ሐ. የሚደርስባቸው እስራት፤ ግድያ፤ ስደትና ጉስቁልና፤ በሰውነት ላይ የሚደረግ እንግልት ሳያስበረግጋቸው ሕዝብ ከድል ጎዳና የሚያደርሰውን ሂደት አብሮ በመምከር፤ ችግርህ ችግሬ፤ ጉዳትህ ጉዳቴ፤ መከፋትህ ክፋቴ፤ ጉስቁልናህ ጉስቁልናዬ፤ ደስታህ ደስታዬ እያሉ በመታገላቸው ከፍተኛ መፈቀርንና መከበርን እንዲሁም ታማኝነትን ያተረፉ ብርቅዬ ዜጎቻችንን በአደባባይ የሚረሽን፤ ደብዛቸውን የሚያጠፋ፤ ገድሎ በተቃዋሚ ተገደለ እያለ አብሮ የውሸት ለቅሶ በሚያለቅስና በሚሳለቅስ በምን ይፈረጃል?

መ. አለአግባብ ዜጋ ከሰራውም ሆነ ከቀዬው የሚያፈናቅል፤ በሀሰትና መሰረተቢስ በሆነ ክስ የሚወነጅልና ለፍርድ አቅርቦ ፍርድ አስጥቶ ዘብጢያ አውርዶ በእስር የሚያንገላታ የፍትህ አልባ ዳኛ በምን ይፈረጃል?

ሰ. ሕዝብን ለጭቆናና ለችግር የሚዳርግ ሥርአተ አልበኛ በምን ሥሙ ይጠራ?

ረ. ለአቤቱታ አፈና፤ ለሰላማዊ ሰልፍ ጥይት፤ ለፖለቲካ ተቃውሞ ፍጅትን በምላሽነት የሚሰጥስ?

ሠ. የኢትዮጵያን ምንነትና ማንነት የካደና ያዋረደ፤ አካሏን ያስገነጠለ፤ ለቀጣይ ግንጠላም ሆን ብሎ በግንባር ቀደምትነት የሚንቀሳቀስ፤ መለያ ባንዲራዋን ጨርቅ ነው በማለት ያንቋሸሸ?

ሸ.. በቀል ባዘለ አመራር የተመረዙ በሕዝብ ጫንቃ ላይ በግዴታ የተቆናጠጡ በሥልጣን ዋልጌነት አድሏዊ አሰራርና ከፋፍዬ ድርጊት የሚሰሩ ይሁነኝ ብለውም በተጣመመ አመለካከት ተነስተው ሽብርን የሚያካሂዱ?

ቀ. ሀገርና ሕዝብ እንዲታመስ፤ ልዩነት እንዲነግስ፤ መከፋፈል እንዲፈጠር፤ አንድነት እንዲጠፋ ሌት ተቀን የሚኳትን በምን ይፈረጃል?

በ. ለባዕዳን በሎሌነት በማደር በቅጥረኝነት በመሰለፍ በጎረቤት የውስጥ ጉዳይ በጦር ሀይል ጣልቃ በመግባት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዘላለማዊ እንኳ ባይሆን ለረጅም ጊዜያት የሚሆን ጠላት የሚያፈራ፤ ከነሱ በተቃረነ መልክ ለሕዝቡ የተለየ ሃሳብና ራዕይ ያለውን የመነተሩ፤ በተራበ ሕዝብ የነገዱ፤ በንጹሃን ሕይወት ሕልፈት የከበሩ ይህንን ሲያደርጉም ተሳስተው ሳይሆን ይሁነኝ ብለው የተሰማሩ በምን ይገለጡ? ወዘተ፤ ወዘተ........

ለነዚህና መሰል ጥያቄዎች በሚገባና በማያሻማ መንገድ መልስ ካልተሰጣቸው እንዴትስ ቀርጠ መታግል ይቻላል? ሕዝብንስ በቀራጥነት የሚያታግል ስልትስ እንዴት መንደፍ ይቻላል? በምን መመዘኛ ተለክቶ ነው ካለፉት አገዛዞች ሁሉ የበለጠ ጸረ እኩልነት፤ ጸረ ዴሞክራሲ፤ ጸረ አንድነት ጠባይ ያሳየው የመለስ አገዛዝ መሆኑን መሳት የሚቻለው? የሕዝብን ጠላትና ወዳጅ በሚገባ መለየት ካቃተን፤ የዚህም መንገዱና ዘዴው ከጠፋን እንዴትስ በትግሉ ሂደት ላይ የጠራ አስተያየት ሊኖረን ይችላል? የሀገር ወዳድነት ካባ ለመልበስ የሚፈልግ ለሰላም ጽኑ ፍላጎት ያለው ሁሉ ሰላማዊነቱን የሚያረጋግጠው የመለስን ሕገ አገዛዝ አሜን ብሎ ተቀብሎ ማክበር ሳይሆን ለአገዛዙ አልገዛም አልታዘዝም አሻፈረኝ በማለት በማመጽና አዲስ ሥርአት ለመመስረት እየተጋለ ሕዝብን ሲያታግል ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ ሌላው ሁሉ ትርፍ ነው። የትም አያስኬድም። ትግል ሲሉ ትግል ይባላልና ሰላም ሲሉ

የምንረዳው የምንገነዘበው ለየቅል ነውና እንቅስቃሴያችንም በዘው መቃኘቱ አይቀርምና የግዴታ ልዩነት መከሰቱ አይቀሬ ነው። መፍትሄውም የግዴታ በሕዝባዊ ትግልና በሕዝቡ አሸናፊነት ለመገኘቱ እምነታችን የጸና ነው። ለዚህ ግን ጠላት ወዳጅ ላይሆን መለመኑ ያብቃ እንላለን። ቢመክሩት የማይሰማን፤ ቢለምኑት ለማይራራ ለጨካኝና ጸረ ሕዝብ ሀይል ለመስገድ መሯሯጡ አብቅቶ ለሚመረው፤ ለሚጎመዝዘው ትግል ፊታችንን እናዙር። ያልደፈረሰ አይጠራምና በትግል እስከ ድል ጸንተን እንገኝ እንላለን። እስከዛው ድረስ መልካሙን እንመኝላችኋለን።

**BOOK REVIEW**

***AUTHOR: TAMIRATE B.SEMEGN***

***TITLE: SEEDS FOR DEMOCRATIZATION IN ETHIOPIA- WHY UNITY OF PURPOSE MATTERS***

***PUBLISHED BY AUTHORHOUSE, 2007, 255 PAGES***

**In the foreword of this valuable book we find the following quote: "A young man's dilemma: "How does one co-exist and live with a clear conscience in comfort in the midst of poverty?" It casts light on Tamirate himself who wrote this book with a conscience that says no to the bad governance and missed opportunities. He puts it clearly: "The debate about governance is, ultimately, about the coming generation of Ethiopians and their abilities to deter/prevent poverty that afflicts the vast majority". Tamirate attempts and succeeds to delve deep into the real causes of the existing poverty and its political and economic reasons.**

**This book, that should be read by all Ethiopians (an Amharic translation is on the way) is divided into eight chapters: political governance /the missing link/; failed leadership and missed opportunities; revolutionary democracy/dictatorial or representative?/; endemic poverty and governance; the Ethiopian brain drain/a national crisis/;transforming mindsets, attitudes, behaviors and values; the vital role of the Diaspora. Tamirate is no distant observer of the Ethiopian scene-- from the book one gets the clear impression that he is involved in the ongoing struggle against poverty and bad governance. The book is timely in that it also deals with the CUDP and UEDF attempts to forge change peacefully and the**

ensuing repression. As an active member of the Ethiopian student movement and the struggle of the sixties for democratization Tamirate gives us informative background on the sacrifices made in the fight against feudalism and autocracy. Tamirate does not forget to focus on the most oppressed, for example women, and the effect of bad governance on their lot. Shattered expectations and moral decay are analyzed with vigor and the why of all this is addressed. How come the poverty became grinding? How come the expectations of the people get dashed time and again? How come human capital, "the key force in development", get underrated and wasted? While Tamirate does give due importance to the role of the Diaspora, especially in light of its visible support to the CUDP, it is my opinion that he gives it much more importance and weight than it deserves when he argues that the Diaspora "must educate the opposition parties, civic organizations, media outlets, professional associations and intellectuals to explore the possibility of creating a well structured, coordinated and sustainable worldwide democratic umbrella organization". It is precisely this over dependence on the Diaspora and particularly on those in North America that lies at the root of the myriad problems of the opposition parties that have subsequently failed to forge close ties with their home constituencies and their basic yearnings and demands. The author's assertion that the USA is "a country that is truly a laboratory of current knowledge and thinking that lives and breathes democracy at all level of civic and social life" and by implication that the Ethiopian Diaspora in America is also beneficiary of this is more than debatable on all premises. In fact, the elitist approach to opposition politics has not borne fruit and the opposition parties should realize that it is high time they guided the Diaspora to be politically useful and supportive without assuming the role of "guide' and educator.

Tamirate's book is perhaps the most extensive critic of the failed leadership of the CUDP and on the damages of the disarray and acrimony that ensued (pp.206-238). Still, the place he gives to the CUDP and the role of the Diaspora leaves me uneasy. One shares the author's anger at what he calls selfish and partisan interests standing in the way of unity and opening the way to fragmentation but his reference to taking the 'higher road", mutual trust, truthfulness and honesty, and the like comes out as a panacea from Dr. Deepak Chopra (quoted by the author on page 215) and not a political analysis of the failures. The CUDP crisis is basically political, the inability of the hastily patched up Kinjit to be political and not just a conglomeration of wild expectations and blurred visions. The CUDP failed in the first test of "know your enemy and know yourself", it harbored illusions as regards the EPRDF and had a high opinion of itself without even setting up a solid organization other than a poorly guided mass movement of protest it wanted to label the tsunami. The role of the Diaspora in the evolution of the CUDP was not all positive as the Diaspora is made up of exiles of various political shades (it is no secret that many activists of the fallen

regime rallied to the CUDP tent) and divisive influences stamped on the path taken by the CUDP leaders who were in the first place forced out of the UEDF by the 'advice' of Diaspora members. An organization without due structure (not just leadership top heavy but membership level down to the kebelle and wereda) and contingency plan based on the clear realization of the nature of the ruling group was bound to falter and fall victim to the more organized force holding power. In other words, there was now ay in which the CUDP would prevail over the EPRDF.

Tamirate adequately explains the financial and resource monopolistic control of the TPLF while at the same time putting the vital nationalities question into proper perspective and insisting that as before revolutionaries should emphasize the primacy of the class struggle. Obviously, this question ahs been narrowly subverted be it by the TPLF, Shabia or OLF but the reverse side of the coin that it epitomized by the opposition that seems to yearn for the "good old days" of chauvinist supremacy needs also to be castigated. Tamirate's apt criticism of Tecola Hagos and the Eritrean Jordan Gebremedhin needs to be read even if it is brief. No one can argue against Tamirate's firm assertion that the foundation for a strong, peaceful, democratic, prosperous and unified Ethiopia should be unwavering commitment to unity in diversity, a commitment that the ruling party leaders lack so glaringly.

Let me end with a relevant quote from the author:

"There is no doubt that the absence of a culture of dialogue and cooperation among opposition groups has adversely affected the possibility of positive transformation in Ethiopia. A major flaw within the camp of the opposition has been and continues to be the lack of a culture of perceiving and accepting minor disagreements as acceptable norms of behavior. In order to contribute to the democratization process, and in order to save our country from the balkanization process that is in the making, <u>opposition parties, civic organizations, opinion leaders, civic societies, associations and intellectuals need to place the national interests of the Ethiopian people above narrow, partisan and individual interests. It is the national agenda of democratic change and freedom</u> that should govern our individual and group behaviors, relationships and actions. There is no shortcut to achieve democracy and freedom" (emphasis mine- LT),p.252.

Tamirate, an obvious optimist, concludes his book by stating that "we can now use the freedom of the CUDP leaders as a break through to reinvigorate the support of the Diaspora" (p.252). Alas, the division has only increased and deepened. All the more for all of us to read this book by Tamirate .

Seeds for Democratization in Ethiopia is must read book and I advise on all to get a copy, to read and discuss it.

A copy can be ordered from www.authorhouse.com, price US$20

Review by: Lemma Tesfaye

# ስለ ሰብአዊ መብት ሰናወጋ

ቆንጂት ተሰፋዬ

## ማስታወሻ

ይህ ጽሁፍ የተዘጋጀው የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ከተመሰረተ 13ኛ አመቱን በቅርቡ ያከበረበትን አጋጣሚውን ምክንያት በማድረግ ነው። የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ እስካሁን ድረስ ያደረጋቸውን እንቅስቃሴዎች በሚመለከትም ሆነ በቅርቡ ያወጣውን መግለጫና ሌሎች እሱን ነክ በሆኑ ርዕሶች በጽሁፉ ማገባደጃ በምንጠቅሰው የድርጅቱን ድረገጽ ውስጥ መመለከቱ ጠቃሚ መሆኑን እንገልጻለን። በበርካታ የኤኮኖሚም ሆነ የሰብአዊ መብት ጠበብቶች እንደሚታመነው የሰብአዊ መብቶች መከበር ለእድገት ዋና መሰረት እንደሆኑ ነው። ሰብአዊ መብቶች በሚጣሱበት ሀገር የሰው ፍጡርን እምብርት ያደረገ እድገት ለማግኘት አይቻልም። ስለዚህም የእድገት መብት መኖር የማይገሰስ ሰብአዊ መብት ነውና ለነዚህ ሁሌም ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀሱ ለሕዝቡ ቀናኢ የሆነ የማንም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሃላፊነትና ግዳጅ ነው። የሕዝብን ሰብአዊ መብቶችን በማፈን ወይንም ደግሞ በመገደብ የኤኮኖሚ እድገት ይገኛል ብሎ ማውራት ቀልድ ነው የሚሆነው። እድገት፤ ብልጽግና ማህበራዊ መረጋጋት በአንድ ሕብረተሰብ ውስጥ እንዲገኙ ለማድረግ መሰረት የሚሆነው ደግሞ ስለ ሰብአዊ መብቶች፤ ይዘትና ምንነት በማወቅ ተግባራዊ የሚሆኑበትን ፖሊሲዎች ቀይሶ በትኩረት ከሕዝቡ ጋር በአንድነት ልብ ለልብ ተገናኝተውሲተገበሩ ብቻ ነው። በሁለቱ መካከል ያለውን ግንኙነት ያወቀና የተገነዘበ ማንኛውም የፖለቲካ ኃይል ፖሊሲውን ለሕዝብ ለማስረዳት የሚቸግረው አይሆንም። ተቀባይነት የማግኘቱ እድል በጣም ሰፊ ነው። እድሉን አግኝቶ የፖለቲካ ሥልጣኑን በሕዝብ ይሁንታነት አግኝቶ የቀረጻቸውን ፖሊሲዎች ተግባራዊ በሚያደርግበት ወቅት የሚያስገኘው እድገት ትክክለኛነቱን ስለሚያረጋግጡለት የሕዝብ አለኝታ መሆኑን የሚመሰክርለት ይሆናል። በመሆኑም ለግንዛቤና ጥራት ያመች ዘንድ ስለ ሰብአዊ መብቶች አጠር ባለ መልክ የሚከተለውን ለአንባቢ ማቅረቡ ጠቃሚ ነውና እነሆ እንላለን።



# ስለ ሰብአዊ መብት ስናወጋ

በናቶ የምዕራቡ የጦር ቃልኪዳንና በዋርሶው የሶሻሊስት ሀገሮች የጦር ክፍል መካከል የነበረው ቀዝቃዛው ጦርነት ተብሎ የሚታወቀው ፍጥጫና ሽኩቻ የፖለቲካ አየር ሙቀቱ ክፉኛ በበረዶ ተዳፍኖ በአንደኛው አሸናፊነት ከተደመደመ በኋላ ሰብአዊ መብት ያልተጠበቀ የፖለቲካ ድሎችን በየቦታው ይጎናጸፋል ተብሎ በብዙዎች ሰላም ወዳድ ልብ ውስጥ ታምኖበትና ተስፋም አሳደሮ እንደነበረ የሚታወስ ነው። ለዚህም የራሱ በርካታ ምክንያቶች ነበሩት።

1ኛ. በርካታ ሕዝብ ሊካፈልበት የቻለበት በምስራቅ አውሮፓ በሶሺያሊስት አምባገነን አገዛዝ ሥር የነበሩት ሀገራት ቀስ በቀስ የተካሄደው የለውጥ ትግልና ሕዝባዊ እንቅስቃሴ፤

2ኛ. የላቲን አሜሪካ ሀገሮች ሕዝቦች ለወታደርና ለሲቪል አምባገነን አገዛዞች አሻፈረን ማለታቸውና፤

3ኛ. በአፍሪካ የነበሩት የአንድ ፓርቲ አገዛዞች ቀስ በቀስ በመንኮታኮት የደረሰባቸው ኪሳራዎችና ለመድበለ ፓርቲ ሥርአት የመገንባት ሂደት ማቆጥቆጥ በርግጥም የዴሞክራሲ ሥርአት ግንባታ ሂደትና የሰብአዊ መብቶች መከበር የወደፊቷ የአለም ገጽታዎች ይሆናሉ የሚለውን ስሜትና ተስፋ በከፍተኛ አሳድጎ ነበር። በተለይም የአንዳንድ ሀገሮች መንግስታት ሰብአዊ መብት መከበርን አስመልክቶ ከአለም አቀፍ ተቋማት

ጋር ለመተባበር ዝግጁነታቸውን መግለጽ በውነትም በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ በጥሞና ወደኋላ ዘወር ብሎ ለሚያስታወሰውና ለተመለከተው ቁጥራቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ ጨምሮ እንደነበር ይገነዘባል። ከዚህ ውጭ ከሌላ ድምዳሜ ለመድረስ በርግጥም ወቅቱና ሁናቴው የሚያስችል አልነበረም።

ነገር ግን እየዋለ እያደር በሰላም ወዳዱ ማህበረሰብ መካከል ሰፍኖ የነበረው የእድገት ተስፋ ተግባራዊ ሆኖ ሊታይ አልቻለም። ሰብአዊ መብቶች በሁሉም በተለይም በታዳጊ ሀገራት ውስጥ የመንግሥቶቻቸው ፖለቲካዊ ሂደት በመመሪያነት ሊገለገሉበት ቀርቶ ከምዕራቡ ሃያላን ሀገራት ገንዘብ መለመኛና የፕሮፓጋንዳ ፍጆታ መጠቀሚያ ከመሆን አላለፉም። ሰብአዊ መብቶች አለም አቀፍነት ይዘት ያላቸው በመሆናቸው ሁሉም ይህንን እውቅናን ሰጥቶና ሕጋዊነታቸውን ተቀብሎ ሊገለገልባቸው ይገባል የሚለው አስተሳሰብ አሁንም ድረስ እያጨቃጨቀ ይገኛል። ይህ ብቻ አይደለም። ሰብአዊ መብቶች ክፉኛ ጸረ ዴሞክራሲ በሆኑ አገዛዞች

እየተጣሱ በሕዝቡ ላይ ሊደርስ የሚችለው የረሃብ እልቂት፤ የርስ በርስ ጦርነት፤ መንግሥት አልባነት፤ መሰረታዊ የሆኑ ማህበራዊ አገልግሎቶች መጓደል፤ የፖሊስ፤ የትምህርት፤ የጤንነት የፍርድ፤ ለሰውነት ተስማሚ የሆነ የምግብና ንጹህ ውሃ የማግኘት፤ የኤሌክትሪክ መብራት ለመጠቀም ሌሎችም ወዘተ አገልግሎት መጥፋት በሚከሰቱባቸው ሀገራት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም ሆነ በሌላ አለም አቀፋዊና አህጉራዊ ተቋማት አማካኝነት ጣልቃ ገብቶ ማርገብና ማህበራዊ መረጋጋትን ማስገኘት ይገባል/አይገባም የሚለው ሃሳብ ከሰብአዊነት አንጻር በበጎ የሚመለከቱት ባይጠፉም አሁንም በጣም የሚያነታርክ ሆኗል። ይህ በተለይ ተግባራዊ እንዲሆን የታሰበው በጣም ደካማ በሆኑና በታዳጊ ሀገሮች ውስጥ መሆኑ ደግሞ ነገሩን ይበልጥ አስቸጋሪ አድርጎታል። በሰብአዊ መብቶችና በሀገራዊ ሉዐላዊነት መርሆዎች መካከል የሚኖረው ግንኙነትም ሆነ መደጋገፍ በሁሉም ዘንድ ተመሳሳይ አመለካከት አለመኖሩ ብቻ ሳይሆን በተቃራኒነት የሚያሰቀምጧቸው የፖለቲካ ኃይሎች ቁጥራቸው በቀላሉ የሚገመት አይደለም። በሶማሌ ከጥቂት አመታት በፊት የተሞከረው ጣልቃ ገብነትና ያስገኘው ውጤት በአሉታዊ ምሳሌነቱ አሁንም ድረስ እያነጋገረ ያለ ነው። ጸረ ሽብርተኝነትን በአለም አቀፍ ደረጃ ለመቋቋም በአሜሪካ የበላይነትና መሪነት የሚደረገው እንቅስቃሴ በበኩሉ ለዚህ አስተዋጽኦ ማድረጉ በስፋት የሚነገር ነው። በሕዝባቸው አመኔታ የሌላቸው በሥልጣን የተቀመጡ አገዛዞች ይህንን ሁናቴ በሚገባ ለራሳቸው የሥልጣን ማራዘሚያ ያልጠበቁት መልካም አጋጣሚ ሆኖ መገኘቱ ደግሞ ድብቅ አይደለም። ስለሆነም በአሁኑ ወቅት ሰብአዊ መብቶች በሁሉም ሀገራት በተለይም በታዳጊ ሀገራት ለብዙሃኑ ሕዝብ ጠቀሜታ እያስገኙ ናቸው ለማለት የሚያስደፍር አይደለም። እንዲያውም ጥሰቶቹ እየጨመሩ መሆናቸውን ለመገንዘብ አዳጋች አይደለም። የመለስ አገዛዝ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ለመሆኑ ምስክር መጥራትና ማስረጃ አቅርቡ ብሎ የሚሞግተን ሊኖር አይችልም። የአስተዳዳአሩና የሥርአቱ ተቃዋሚ የሆኑ ዜጎቻቸውን እንዳሻ ማሰር፤ የጸጥታ ክፍሎቻቸው ገዶብ የለሽ ሥልጣን መስጠትና አሰቃቂና ከሰብአዊነት ውጭ የሚያደርጓቸው ተግባራት፤ በቁጥጥር ሥር በዋሉ ዜጎች ላይ እንግልት ማካሄድ፤ የፖለቲካዊ ይዘት ያለው በተለይም በፓራሚሊቴሪ ተቋማት አማካኝነት የሚደረጉ ግድያዎች፤ የሕግ የበላይነት ግደባ፤ የታሰሩ ዜጎችን ደብዛቸውን ማጥፋት፤ መንግሥታዊ ያልሆኑ እንደ ሰራተኛ፤ አስተማሪ ወጣቶች፤ በተለያዩ የእድገትና ሰናይ አቅራቢ ድርጅቶች እንቅስቃሴዎቻቸውን መግታት ወይንም መከልከል ለሰብአዊ መብት ጥሰት በምሳሌነት የሚታዩ ናቸው። እነዚህ ሁሉ ደግሞ በጥቂት ግለሰቦች መዳፍ ውስጥ የፖለቲካና የኤኮኖሚ ሥልጣን ይዞ ለማቆያ የሚያገለግሉ ናቸው። ለጥሰት ምክንያት የሚሆኑትም በዚሁ የተነሳ ነው። ሰብአዊ መብቶች በተለይ

የሚጣሉት በሥልጣን ላይ የተቀናጠጡ ክፍሎች ጨምድደው ለያዙት የፖለቲካ ሥልጣናቸው እንደ የመለስ አገዛዝ የመሰሉ ሕጋዊ መሰረት ጨርሶ የሌላቸው ወይንም ደግሞ በጣም ደካማ በሆኑበት ሁኔታ መሆኑ ደግሞ ሁኔታውን ይበልጥ አሳሳቢና ትኩረት ሰጥቶ ማየትና መመርመር የሚጠይቁ ናቸው።

የታሪክ ሂደት ባለበት ረግቶ የሚቆም አይደለምና ሰብአዊ መብቶች የመከበራቸው ጉዳይና የፖለቲካዊ ሂደታቸውን አስመልክቶ በመንግሥታት፤ ለርዕሱ ቅርበት ባላቸው ክፍሎችና ለሰብአዊ መበት መጠበቅ በሚንቀሳቀሱ ባለሙያዎች መካከል የሚደረጉ ውይይቶች መልካቸውን እየቀየሩ መሆናቸውን ለመገንዘብ አዳጋች አይደለም። ሰብአዊ መብቶች ምንም እንኳ ለተግባራዊነታቸው በርካታ እክሎች ቢያጋጥማቸውም ለሀገራዊም ሆነ ለአለም አቀፍ ተቋማት የውይይት መነሻና መድረሻ እምብርት እየሆኑ መገኘታቸው ግን አልተቋረጠም። የፖለቲካ ውሳኔዎች እየተመዘኑ የሚገኙት ከሰብአዊ መብቶች መጠበቅ አንጻር እንዲሆን የሚደረገው ግፊት እየጨመረ ብቻ ሳይሆን ለፖለቲካ ሂደቱም ዋና መለኪያ እየሆኑ ናቸው። ሰብአዊ መብቶች ውስጣዊ ይዘታቸውን በመተርጎም እንዲሁም በሕብረተሰቡ ውስጥ በሚከሰቱት የእሴት እድገቶችና ለውጦች የተነሳም ሰብአዊ መብቶች ሁሌም አዳዲስ ይዘትን እያገኙ መሄዳችውም ይታያል። ስለሆነም በዚህ አጠር ባለ መጣጥፍ ከትርጉምና ውስጣዊ ይዘታቸውን አንስቶ አለም አቀፋዊ መሰረታቸውን በሚመለከት በርዕሱ በቂ ተመክሮ ካካበቱ የተለያዩ በተለይም የኤኮኖሚና የሰብአዊ መብት ባለሙያዎች ከዘገቧቸው መጣጥፎች ውስጥ ጥቂቶችን በመንደርደሪያነት በመመርኮዝ ለግንዛቤ በሚረዳ መልክ አጠናቅረን ለማቅረብ እንሞክራለን።

## *ትርጉም*

ሰብአዊ መብቶች ማንኛውም ሰው ከተፈጥሮው ጋር የሚጎናጸፋቸው፤ በሕብረተሰቡ ውስጥ በሚኖረው ቦታ፤ ዜግነት፤ እምነት፤ ወይም ጾታ ጥገኛ ያልሆኑ የማይሻሩና የማይለወጡ፤ የማይገሰሱ መሰረታዊ የነጻነትና የመብት እሴቶች ሲሆኑ ከዜጎች መብቶች በተለየ ለሁሉም ሰው የሚያገለግሉ ናቸው።

ሀ. *"ከተፈጥሮው ጋር"* የሚለው ሰብአዊ መብቶች በመንግሥት በችሮታ መልክ የሚሰጡ አለመሆናቸውን እንዲያውም መንግሥት እንዲከበሩ ለማድረግ ዋና ተግባሩ መሆኑን የሚያመለክት ነው።

ለ. *"ለሁሉም ሰው"* የሚለው ለሰብአዊ መበት መከበር ብቸኛ መመዘኛው ሰው ሆኖ መፈጠር ብቻ መሆኑን የሚያጠናክር ነው።

ሐ. የመከበራቸው ጥያቄ የሚቀርብላቸው ተደራጅተው ለሚገኙ ማናቸውም ክፍሎች በተለይም ለመንግሥት፤ ለእምነት፤ ለቤተሰብ፤ ለኤኮኖሚ ተቋማት፤ የርስ በርስ ግጭት ለሚያካሂዱ አማጺያን ክፍሎች ናቸው።

የትኞቹ ሰብአዊ መብቶች በተናጠል የማይለወጡ ናቸው የሚለው ጥያቄ በጣም የሚያከራክር ነጥብ መሆኑ ድብቅ አይደለም። እንዲያውም ይህ ሁናቴ ጥራት ለማግኛ እየረዳ መሆኑ ይታያል። በሰብአዊ መብቶች ሥር ተዘርዝረው የሚገኙት እሴቶች ከብዛታቸው የተነሳ በአንዳንዱ መካከል ችግር ሊከሰት ይችላል የሚል መከራከሪያ ነጥብን በአግባቡ ፊር ለማስያዝ ይቻል ዘንድም ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። ሰብአዊ መብቶችን የተለያዩ ደረጃዎችን ለመስጠት ሙከራዎች የተደረጉ መሆናቸውንና ወደፊትም ሊደረጉ እንደሚችሉ ታሳቢ ውስጥ በማስገባትና መሰል ሙከራዎችን ለመቋቋም ይቻል ዘንድ *"ሰብአዊ መብቶች የሚከፋፈሉና የተለያዩ ደረጃ ያላቸው ሳይሆኑ እንዲያውም እርስ በርስ የሚደጋገፋ ናቸው"* የሚለው ሃሳብ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት እያገኘ መሆኑ ይታያል።

መብቶቹን አስመልክቶ ግልጽነት ለመስጠት ሲባል ምሁራኖችና በርዕሱ በርካታ ተመክሮ ያካበቱ ሙያተኞች ሰብአዊ መብቶችን በሁለት ትላላቅ ርዕሶች አንደኛው ከፍልስፍና አንጻር አዎንታዊና አሉታዊ በሚል ሁለተኛው ደግሞ ከታሪክ አንጻር በሶስት ንዑስ ክፍሎች ሥር ከፍለው ይተነትኗቸዋል። ከታሪክ አንጻር የሰብአዊ መብቶችን ምንነት ለመተንተን የዚህን መጣጥፍ ገጾች በጣም የሚያሰፋውና እንደ ሁናቴው ወደፊት የምንመለስበት በመሆኑ ለጊዜው ተወት በማድረግ ከፍልስፍና አንጻር በአዎንታዊና በአሉታዊ መልክ የተቀመጡበትን ሁናቴ ለመመልከት እንሞክራለን።

## *አዎንታዊ/አሉታዊ*

ሰብአዊ መብቶች የሰው ልጅ ሰው ሆኖ በመፈጠሩ ብቻ ሰብአዊ ክቡርነትን የተጎናጸፈ ሕይወት እንዲኖረው ዋስትና ቢሰጡም ሰብአዊ ክቡርነት የሚለው ግን ግንዛቤው በጣም አስቸጋሪና አከራካሪም ስለሆነ የሰብአዊ መብቶች አላማ የሰዉን ፍጡር ነጻነቱን ከማስጠበቅ አንጻር ማየቱ መልካም ሆኖ ተገኝቷል። እነዚህ የተለያዩ የነጻነት መብቶች በሁለት የነጻነት ግንዛቤዎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። እነዚህም በባለሙያዎች አስተያየትና ገለጻ መሰረት በአዎንታዊና በአሉታዊ በሚል የሚያቀርቧቸው ናቸው።

## *አሉታዊ*

ከተለያዩ ጥናታዊ ዘገባዎች ለመገንዘብ እንደሚቻለው የነጻነት ግንዛቤ እንደ አሉታዊ ነጻነት ሲወሰድ እጥር ምጥን ባለ አኳኋን ለመግለጽ ከተፈለገ *"የአንድ ግለሰብ ዜጋ ግላዊ ነጻነቱ ገደቡ የሌላው ግለሰብ ዜጋ ነጻነት በሚጀምርበት ጊዜ ነው"* በሚለው አረፍተ ነገር ማጠቃለል የሚቻል ነው። ይህ አረፍተ ነገር የሚሰጠው ግንዛቤ የሚያመለክተው አንድ ቁም ነገር የሰው ፍጡር በአምሳያው ካለው ወገኑ የኃይል እርምጃ ሊወሰድበት አይገባም የሚለውን መሰረታዊ ሃሳብ ነው።

ይህ የነጻነት መብት ስኬታማነት ሊያገኝ የሚችለው የሕብረተሰቡ አባላት በርዕሱ ላይ ከስምምነት በመድረስ ዋስትና ሰጥተው ለተግባራዊነቱም አጥብቆ የሚንቀሳቀስ ሥር አትና አስተዳደር ሲገነቡ ነው። ሥርአቱም ሆነ አስተዳደሩ ግለሰብ እንደ ግለሰብነቱ በግል ውስጣዊ ጉዳዩ አስመልክቶ የማስከበር፤ የማስጠበቅ ግዴታ ይኖርበታል ማለት ነው። ይህንንም ዋስትና ለማስጠበቅ ይቻል ዘንድ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ መብቶች ይኖራሉ። ከነዚህ ውስጥ ግለሰቡ ከአደጋ ነጻ መሆን፤ የግል መኖሪያ ቤቱ አለመደፈር፤ ሃሳቡን በነጻ መግለጽ፤ የፕሬስ ነጻነት፤ የእምነት ነጻነት፤ የመሰብሰብ ነጻነት፤ በነጻ የመንቀሳቀስ፤ የሥራ ምርጫ ነጻነት ማግኘት፤ የመዋዋል ነጻነት መኖር፤ የግል ሀብት የመያዝ ነጻነት፤ ራስን የማበልጸግና የማሳደግ መብት መኖር በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው። በዚህም የተነሳ በአሉታዊ የነጻነት መብቶችና በዴሞክራሲ መብቶች መካከል የጠበቀ ግንኙነት ይኖራቸዋል። ስለሆነም ስለ ሰብአዊ መብቶች ተግባራዊነት በሚጠየቅበት ወቅት ከዴሞክራሲ መብቶች ጋር አቆራኝቶ መሆኑን ማወቅ የግድ ይላል። ለዚህም ነው ሰብአዊ መብት ያለ ዴሞክራሲ፤ ዴሞክራሲ ያለ ሰብአዊ መብት መከበር ጨርሶ የማይታሰብ ተብሎ አጽንዖት በመስጠት የሚነገረው።

## *አዎንታዊ*

አዎንታዊ ነጻነት የሚሰጠው ግንዛቤ ማንኛውም ግለሰብ የፈለገውን ለማድረግ የነጻነት መብቱ ሊከበርለት የሚገባ መሆኑን ነው። ይህም ማለት መብቱ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው በጣም ጠባብ በሆኑ ሁኔታዎች ነው። ለምሳሌ ለሰውነት ደህንነት እድገት የሚያስፈልጉ ምግብና መጠት አስመልክቶ የመመገብና ንጹህ መጠጥ የማግኘት መብት መቅረጽ ይቻላል። ነገር ግን ሥጋዊ ፍላጎቱን የማርካት ጉዳይ ከተነሳ የሌላኛውን ግለሰብ ግዴታ ይመለከታልና የእርካታ መብት በእሴትነት ለመቅረጽ በጣም አስቸጋሪ ይሆናል። በአሉታዊ ነጻነት አንድ ግለሰብ የተወሰኑ ድርጊቶችን ከማከናወን እንዲቆጠብ ግዴታ ሲያስገባ አዎንታዊ ነጻነት ግን በተቃራኒው ይሆናል ማለት ነው። ለምሳሌ የመመገብ መብት ተግባራዊ እንዲሆን ከተፈለገ ሌላ ሶስተኛ ወገን ምግብን የማከፋፈል ግዴታ ውስጥ ይገባል ማለት ነው። በመሰረቱ ይህ ጥያቄ የሚቀርበውና የሚመለከተው ሕብረተሰቡን ነው። በዚህም የተነሳ አዎንታዊ ነጻነት ከአንድ ሕብረተሰብ ጋር በጣም የተቆራኘ ነው። ስለሆነም ከግለሰብ አቅም በላይ የሆኑና የጋራ ጥረትን የሚጠይቁ ከሆኑት የነጻነት መብቶች የሚያልፍ በሙሉ ሕብረተሰቡ ሊወሰን ይገባል ማለትም የሕብረተሰቡ ጥያቄና ተግባራት ይሆናሉ ማለት ነው።

ለአዎንታዊ ነጻነት ወሳኙ ሃሳብ ራስን የማሳደግ ሁኔታ ነው። ይህ ራስን የማሳደግ ሃሳብ በአሉታዊ ነጻነት ካለው የራስ ስብዕናን ከማበልጸግ ጋር

እንዳይምታታ ማወቁና መጠንቀቁ ደግሞ አስፈላጊ ነው። አንድ ግለሰብ በባሕላዊ ሕይወት ውስጥ ኑሮውን እንዲመራ ከፈለገ የግዴታ የሰዎች ስብስብ የሆነ አንድ ሕብረተሰብ ያስፈልገዋል። በሕብረተሰቡ ውስጥ አብሮ በመኖር ነው የሰው ፍጡር ከፍተኛውን ግብረገባዊ ነጻነትን ሊጎናጸፍ የሚችለው።

ግዴታን በውስጡ ያዘለው አዎንታዊ ነጻነት ከአሉታዊ ነጻነት የበለጠ ለሰው ፍጡር ጉዳት በሚያስከትል ሁኔታ ለመጠቀም እምቅ ኃይል ያለው ነው። የአንድን የሕብረተሰብ ትርጉም ይዘትና ምንነት በልጥጡ በመተርጎም የማይነካ፤ የማይደፈር፤ የማይተችና ዘላለማዊነት እንዳለው በማድረግ ግለሰብን ለመጨቆኛ መጠቀሚያ መደረጉ ይታወቃል። ይህንን ሁኔታ የተለያዩ ርዕዮተ አለምን ያነገቡ አምባገነኖች ተጠቅመውበታል። ውስጣዊ ይዘቱ በስልጣን ላይ የተቆናጠጡ ክፍሎችና ደጋፊዎቻቸው ሥልጣንና ጥቅምን ማስከበር መሆኑን በመሸፋፈን የሕዝብ ጥቅምና ደህንነት ማስከበር በሚል ሳቢያ ተቀናቃኝ ሃሳብና ተናጋሪዎችን ለማስወገድ ሕይወታቸውን እስከ ማጥፋት ድረስ መጠቀሚያ ሆኗል። ደርግ በሕብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ሥም አንድን ትውልድ የመተረበት ያ አሳዛኝና አስቃቂ ድርጊት በሕዝባችን ላይ ያሳደረው የሕሊና ቁስል ገና ሳያገግምና ሳይደርቅ በላዩ ላይ የወያኔ አገዛዝ በብሄረሰብ መብት አስታኮ እያደረሳቸው ያሉ በደሎች፤ ዘግናኝ ስቃዮች አሁንም ድረስ በቀጣይነት ያሉት ከደርግ የማይተናነሱ ለመሆናቸው በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል።

ከግለሰብ ሃላፊነት ግንዛቤ ንቃተ ሕሊና እየዳበረ መምጣት፤ ተምኔታዊ ከሆነ ውጫዊ ሀይል ጥገኝነት መላቀቅ፤ ለማንኛውም የሰው ፍጡር ነጻነት ግንዛቤ የማግኘትና የመጠየቅ መሰረት ሊሆን የሚችለው የእያንዳንዱ ግለሰብ ክቡርነት አሳቤ ሊጎለብት አስችሎታል። ስለ ሕይወት፤ ነጻነትና የግል ንብረትን አስመልክቶ የተካሄደውም ግልጽነት የማግኘት ሂደት መሰረታዊ ለሆኑት መብቶች ዝርዝርና ልዩነቶቻቸው ይበልጥ ጥረት እያገኙ ሊሆዱም አስችሏቸዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ስለ ሕብረተሰብ፤ ስለ ሀገራዊ ሉዓላዊነትና ስለ ሥልጣን ክፍፍል የዜጎችን መብትና ነጻነት ለማስጠበቅ የሚያስችል መሳሪያ ለማግኘት መድረኩን አመቻችቷል።

የሰብአዊ መብቶችን አሳቤ የተላበሰ ሕጋዊነት ለአንድ መንግሥት ይሁንታነት ለመስጠት ነጻነትን እኩልነትንና ሀላፊነት የተሞላበት ተግባር እንዲኖር ጥራት የሚያደርግና የሚያስጠብቅ ሲሆን ብቻ ነው የሚለው ሃሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ ተቀባይነት ያገኘው በ1776 ዓ.ም. በቨርጂኒያ የመብት ሕጎችና በ1789 ዓ.ም. በዝርዝር ሊቀመጡ የቻሉበት በፈረንሳይ ነበር። በኋላም በተለያዩ ጊዜያት እያደጉና እየጎለበቱ አሁን የደረሱበት ደረጃ ለምሳሌ ግላዊ ነጻነት(ሕይወት፤ ዋስትና፤ እምነት፤ የግል ንብረት፤ የሕግ የበላይነት) ና

ፖለቲካዊ ነጻነት(ምርጫ፤ የሀሳብና የፕሬስ ነጻነት) በግንባር ቀደምትነት ሲጠቃለሉ በ 18ኛውና 20ኛው መቶኛ አመት የማህበራዊ መብቶች(የሥራ፤ ማህበራዊ ደህንነት፤ ትምህርት) ሊታከሉበት ችለዋል።

## የሰብአዊ መብት ፖለቲካ አለም አቀፍ መሰረቱ

የወቅቱ የሰብአዊ መብት ፖለቲካ መሰረቱ ከሁለተኛው አለም አቀፍ ጦርነትና በተለይም የጀርመንና የጣሊያን ፋሺስቶች በአውሮፓ በሰው ፍጡር ላይ ያደረሱት ተወዳዳሪ የሌለው እጅግ አሰቃቂና አሳዛኝ ድርጊቶች ናቸው። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር ራሱ ዝርዝር የሆነ የሰብአዊ መብት አንቀጾች ባይኖሩትም በውስጠ ደንቡ አንቀጽ 1 ቁ. 3 እንዲሁም አንቀስ 55 ሐ. እንደተጠቆመው ሰብአዊ ነክ በሆኑ ሁኔታዎች ሊኖረው የሚችለው ሥልጣን ተገልጿል። በዚህም መሰረት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የዘር፤ የጾታ፤ የእምነትና የቋንቋ ልዩነቶችን ሳያደርግ ሰብአዊና መሰረታዊ የነጻነት መብቶችን ለማስከበር አለም አቀፍ ትብብር በማስገኘት ማስከበር ይኖርበታል። በአንቀጽ 56 መሰረት ደግሞ ሁሉም መንግሥታት ለዚህ ስኬታማነት ተባብረው እንዲሰሩም ግዴታ ይኖርባቸዋል። የሰብአዊ መብት ውስታዊ ይዞታና ትርጉማቸው እንዲሁም ለሰብአዊ መብት ፖለቲካ የሂደት መሰረት ሊሆን የቻለው በ1948 ዓ.ም. ይፋ የሆነው ቻርተርና በ1966 ዓ.ም. ና በ1976 ዓ.ም. የጸደቁት የኤኮኖሚ፤ ባሕላዊ፤ ማህበራዊ፤ እንዲሁም የዜግነትና የፖለቲካ መብቶች ናቸው። እነዚህ በአለም አቀፍ ደረጃ ስምምነት የተደረሰባቸው በመሆናቸው እነዚህን ያጸደቁ መንግሥታት በሙሉ ተግባራዊ ሊያደርጓቸው የሚገቡ ናቸው። እስካሁን ድረስ የተደረሰባቸው የስምምነት ውሳኔዎች ከ60 በላይ ይሆናሉ።

ይህ ይሁን እንጂ አሁንም አንዳንድ መንግሥታትና የነሱ ቀንደኛ ወኪሎቻቸው በሰብአዊ መብቶች መካከል የደረጃ ልዩነት በማበጀት ለምሳሌ ሃሳብን በነጻ የመግለጽ መብትን እየተቀበሉ የማህበራዊና የኤኮኖሚ መብት አካል የሆነውን ሥራ የማግኘት መብት ግን ለመቀበል አይፈልጉም። ነገር ግን በ1993 ዓ.ም. በቪየና ከተማ የተደረገው ሁለተኛው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ጉባኤ ላይ 171 ሀገሮች ይህንን መብት እውቅና ሰጥተው በመቀበላቸው ሂደቱ ትክክለኛ አቅጣጫ እንዲይዝ ለማድረግ የሚደረገው እንቅስቃሴ ሊያጎለብተው ችሏል። በዚህ ውሳኔ መሰረት፤

- ሰብአዊ መብቶች አጠቃላይነት ያላቸው ሲሆኑ ለሁሉም በሁሉም ቦታ በማንኛውም ወቅት የሚሰሩ መሆናቸው፤
- ሰብአዊ መብቶች ውህደት ያላቸውና የማይከፋፈሉ ማለትም በሁለንተናቸው

ተግባራዊ ሲሆኑ ብቻ ነው የሰው ፍጡር ክቡርነት ዋስትና እንደሚያገኝ፤

- ሰብአዊ መብቶች እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉ ሲሆኑ የእሴትነት ይዞታቸው ሊገለጽ የሚችለውም በአጠቃላይነታቸው መሆኑን በሚገባ አስረግጠው ከስምምነት መድረሳቸው ነው።

ሰብአዊ መብቶች በሚከበሩበት ሀገር ሁሉ የእድገት መሰረት ለመሆናቸው ከጥያቄ የሚገባ አይደለም። ሃሳቦች በነጻ በማይንሸራሸሩበት ሥርአት የኤኮኖሚና ማህበራዊ እድገቶች ደግሞ ይቀጭጫሉ። ሰዎች በድህነት የሚጠቁ ከሆነ ልጆቻቸውን ትምህርት እንዲያገኙ ለማድረግ ስለማይቻላቸው ልጆቻቸው ከድህነት አረንቋ ለመውጣት ይቸግራቸዋል። በግለሰብ ደረጃ የሚደረጉ ማናቸውም የኤኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በአምባገነን ሥርአትና በማህበራዊ ጭነት እንዲቀጭጩ ከተደረጉ ኤኮኖሚው ይጎዳል። ለዚህም ነው መንግሥት ለሚቀይሰው የእድገት ፖሊሲ የሰብአዊ መብቶች መጠበቅ ወሳኝ የሚሆነው። በተለያዩ አለም አቀፍ ተቋማት ይፋ በተደረጉ የስታቲስቲክ መረጃዎች ለመገንዘብ እንደሚቻለው የሃሳብና የፕሬስ ነጻነትና ሰብአዊ መብቶች በሚከበሩበት ሀገር የኤኮኖሚ እድገቶች በአፋጣኝ ሊኖር እንደሚችል ነው። ይህ በሌለበት ሰላምና ማህበራዊ መረጋጋት አይኖርም። ሰላምና ማህበራዊ መረጋጋት በአንድ ሕብረተሰብ ውስጥ ከሌሉ እድገት ይገኛል ማለት ዘበት ነው። እድገት ሲባል ደግሞ የተዛቡና እውነተኛውን የሀገሪቷን ገጽታ የማያንጸባርቁ የስታቲስቲክ መረጃዎች ማጉረፍ ማለት አይደለም። የኤኮኖሚ እድገት በምግብ ራስን መቻል፤ በኤኮኖሚ ከዳበሩትና በቴኮኖሎጂ ከበለጸጉት ሀገራት እውቀትን ማስመጣት ብቻ አይደለም። እድገት የሰውን ፍጡር በሁሉም አቅጣጫ በሰብአዊ ክቡርነቱ፤ በመብቱ መከበርን ማዕከል ያደረገ ሊሆን ይገባል። እድገት ሲባል ስለ ሰው ልጅ እድገት ነውና የራሱን ችሎታ ማዳበር፤ የመፍጠር ችሎታ ማካበት፤ በሚኖርበት ተፈጥሮአዊና ማህበራዊ አካባቢ የመወሰንና ሃላፊነት የመውሰድ፤ የአማራጭ ነጻነት ማግኘትን ያጠቃልላል። ተመክሮ ማካበት፤ ተምሮ እውቀት እያካበተ ችሎታውን እንደገና ማወቅ፤ ማጠናከርና መገንዘብ ይህንንም ለመጠቀም መቻል ለሕብረተሰቡ ዋና ሞተር ነው።

## ሰብአዊ መብቶች የማይነጣጠሉ/የማይከፋፈሉ ስለመሆናቸው

ሰብአዊ መብቶች ከአጠቃላይነታቸው ሌላ የማይነጣጠሉ ስለመሆናቸው አሁንም በአንዳንድ አካባቢዎች የልዩነት መንስኤዎች ናቸው። የልዩነት ፍሬ ነገር ተጨምቆ ሲቀርብ የኤኮኖሚ፤ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች ከፖለቲካዊና ከዜግነት መብቶች ጋር በእኩልነት ደረጃ

ይታያሉ ወይ? ወይንም ያላቸው ዋጋ/ክብደት እኩል ነወይ? የሚለውን ጥያቄ የሚመለከት ነው።

ለብዙዎች የሰብአዊ መብቶች ዋና እምብርት የሆኑት የፖለቲካና የዜግነት መብቶች ብቻ ናቸው በማለት ይከራከራሉ። ለዚህ ማጠየቂያቸው እነዚህ መብቶች ግለሰብ ዜጋን ከመንግሥት ጥቃት(ለምሳሌ ከእንግልት ዳርጎት መጠበቅ) የሚከላከሉ በመሆናቸው የሚል ነው። ነገር ግን በአዎንታዊ ነጻነት የሚታዩት የኤኮኖሚ፤ ማህበራዊና ባሕላዊ መብቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ ከመነግሥት ከፍተኛ ጥረት ማድረግን የሚጠይቁ ናቸው። በዚህም የተነሳ እነዚህ መብቶች በአብዛኛ ሕጋዊ ግዴታ የማያስገቡ የፖለቲካ እሴቶችን ገላጮች ናቸው። በዚህም የተነሳ መንግሥት ስኬታማ እንዲሆኑ ጥረት ማድረግ እንጂ አላማዎቹን ስኬታማ እንዲያደርግ አይጠበቅበትም። በሌላ በኩል ደግሞ ሰብአዊ መብቶች የማይነጣጠሉ ናቸው በማለት የሚከራከሩት ወገኖች ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑና እውቅና ካገኙት ዝቅተኛ ዋስትና መኖር ከፖለቲካ ነጻነት ያነሰ ሊሆን አይችሉም። መንግሥት የኤኮኖሚ፤ ማህበራዊና ባሕላዊ መብቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ የሚኖረው ግዴታ የፖለቲካና የዜግነት መብቶች ተግባራዊ በማድረግ ካለበት ግዴታ የሚለይ አይሆንም በማለት ሃሳቡን ክፉኛ ይቃወሙታል። እነዚህ ግዴታዎች የሚገለጹትም፤

ሀ. ሰብአዊ መብቶች የሚከበሩበት የኑሮ ደረጃ ሊጠበቅ ይገባል።

ለ. በሶስተኛ ኃይል እንዳይጣሱ ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል።

ሐ. እነዚህ በማይኖሩበት ሁናቴ ማናቸውንም አስፈላጊ የሆኑ ኃይሎችን ተጠቅሞ ስኬታማ ሊደረጉ ይገባል።

ስለሆነም የዜግነትና የፖለቲካ መብቶች ሁሉ የኤኮኖሚና ማህበራዊ እንዲሁም ባሕላዊ መብቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ መንግሥት የተወሰኑ የጣልቃ ገብ እንቅስቃሴውን ሊያቆም የግድ የሚለው ብቻ ሳይሆን የተወሰኑ ቁሳቁሶችንም ማቅረብ ይኖርበታል። እነዚህ መብቶች ስኬታማ እንዲሆኑ ለምሳሌ ፍትሃዊ የሆነ የፍርድ ሂደት እንዲኖር ከተፈለገ በቅድሚያ መንግሥት ፍርድ ቤቶች ከአስተዳደሩ ጣልቃ ሳይኖርባቸው ነጻነታቸው ተጠብቆ የመስራት ዋስትና ማስገኘትና ለዚህም መረጋገጥ የሚያስፈልገውን ሁናቴዎችን ሁሉ ለፍርድ ተቋሙ ማሟላት ይጠበቅበታል። ከዚህ በተጨማሪ እንግልት ማድረግ ጉዳይ በባሕል ሊስታከክ፤ ድህነት እንደ እድል ጉዳይ ሊወሰድ ጨርሶ አይቻልም። እንግልትም ሆነ ረሃብና ድህነት ምንጫቸው ፖለቲካዊ ነውና። ለዚህም ነው የተለያዩ ምክንያት ይሰጠው ባለፉት ጊዜያት በታዳጊ ሀገራት በተለይ የአንድ ፓርቲ አምባገነን ሥርአት ባደረሰው የኤኮኖሚ ውድቀቶች ምክንያት፤ የመልካም አስተዳደር የመገንባት፤ ግልጸነት፤ ፍትህነት፤ በውሳኔ አወሳሰድ

ሂደት ተካፋይ የመሆን ጥሪ ክብደት እያገኙ ሊመጡ የቻሉትና ለኤኮኖሚ እድገት መገኘት መሰረት ናቸው ተብለው በዋናነት እየቀረቡ የሚገኙት። በመሆኑም የኤኮኖሚ፤ ማሕበራዊና ባህላዊ መብቶችን ችላ ማለት ከረጅሙ አንጻር በሕብረተሰቡ መረጋጋት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል። የፖለቲካ መብቶችን ማፈንም ውጤታቸው እንዲሁ ከዚሁ የተለየ አይደለም።

## *መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች*

ሰብአዊ መብቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ ወሳኙ መንግሥት በጽሁፍ በሕገ መንግሥት ለነዚህ መብቶች ዋስትና መስጠቱ ብቻ ሳይሆን ከዚህ በበለጠ የመንግሥት ባለስልጣናትዴሞክራሲያዊ ቁጥጥር ሊደረግባቸው ሲቻል ነው። ለዚህ ደግሞ ነቅቶ በአንክሮ የሚከታተል ዜጋ በሀገርም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ ያስፈልጋል። ከነጻ ፕሬስ በተጨማሪ መንግስታዊ ያልሆኑ ሕዝባዊ ድርጅቶች ከፍተና ሚና ይጫወታሉ።

መንግሥታዊ ያልሆኑ ሕዝባዊ ድርጅቶች የአንድ ሕብረተሰብ ዋና ካፒታሉ ናቸው። ሕዝባዊ ድርጅቶች በሚያደርጓቸው ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎች አማካኝነት፤ የፖለቲካ ሁናቴዎችን ለሕዝብ ይፋ በማድረግ ድጋፍ ለማግኘት የሚያከናዉናቸው ተግባራት ለአንድ ፖለቲካ ችግር የሕዝቡን ትኩረት እንዲስብና ንቃተ ሕሊናው እንዲዳብር ለማድረግ ሚናቸው በጣም ከፍተኛ ነው። ሕዝባዊ ድርጅቶች ለሕዝቡ ቅርበት ያላቸው በመሆናቸው ያካበቱትን እውቀት በማካፈል የሚያገለግሉ ናቸው። የራስ አነሳሽነትን ለማጠናከር፤ አባላትም ሆነ ደጋፊ በማሰባሰብ በተለይም ለተጎዱ፤ በደል ለደረሰባቸው ማህበራዊ ክፍሎች እርዳታ ማቅረብ ብቻ ሳይሆን እንደ ቃል አቀባይና ችግሮቻቸው፤ ብሶታቸው እንዲደመጥ ያደርጋሉ። በዚህ በኩል እንደ ሌሎቹ ህዝባዊ ድርጅቶች ሁሉ የሰብአዊ መብት ጠባቂ ድርጅቶች በመልካም ምሳሌነታቸው የሚጠቀሱ ናቸው። ያለመታከት ለሕሊና እስረኞች፤ ደብዛቸው ለጠፋ፤ መብታቸው ለተረገጡባቸው፤ እድገታቸው እንዲቀጭጭ ለተደረጉባቸው ማህበራዊ ክፍሎች በአጠቃላይ ለሕብረተሰቡ ሰብአዊ መበት መከበር ይንቀሳቀሳሉ። ሰብአዊ መብቶችን አስመልክቶ የሕዝቡ የፖለቲካ ንቃት ከፍ እንዲል የተለያዩ ሴሚናሮችን በማዘጋጀትና በርዕሱ በርካታ ተመክሮን ያካበቱ ምሁራንን በመጋበዝ በደል ከደሰረሰባቸው ዜጎች ጭምር በማገናኘት መፍትሄ በጋራ የሚያፈላልጉ ናቸው። እንቅስቃሴያቸው በዚህ ብቻ አያቆምም። የሕሊና እስረኞች ዘመዶቻቸውን መርዳት አንስቶ በደል የደረሰባቸውን ሁሉ ባላቸው አቅም ሕጋዊ መከታ ለመሆንም ጥራት ያደርጋሉ። መብታቸው በፍርድ ቤት እንዲከበርላቸው ይጥራሉ። ያልነቃ ያልተደራጀ ማንኛውም ዘጋ መብቱን ለማስከበር በጣም የሚያዳግተው መሆኑን በተጨባጭ ያቀርባሉ። ንቃተ ሕሊናው ዳብሮም ከአምሳያው ጋር አብሮ የሚደርስበትን የመብት ጥሰትም

ሆነ ጥቃቱን ለመቋቋም ካልጣረ የትም እንደማይደረስም ያስተምራሉ። ሰብ አዊ መብቶችና የሕግ የበላይነት የሕዝብ ጥቅም ምሶሶን የሚገነቡ ናቸው። ሰላምና ነጻ ሕሊና ኖረው እድገትን የማይቀይ ክስተት ለማድረግ ይቻል ዘንድ ዴሞክራሲን ማስፈንና ሰብአዊ መብቶችን ማስከበር ሊያልፉት የማይችሉት ሀገራዊ ግዴታ ነው።

ከዚህ አንጻር የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ በርካታ እንቅስቃሴዎችን ከሚያከናውኑ ሀገር በቀል መሰል ሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ አንዱ ነው። ይህ ድርጅት በሀገራችን የሰብአዊ መብቶች እንዲከበሩ፤ በሌሎች የተረሱና ደብዛቸው የጠፋትን ኢትዮጵያዊያን ፍትህ እንዲያገኙ ለማድረግ የሚያከናውናቸው እንቅስቃሴዎቹን ይበልጥ እንዲያጠናክር የሁሉም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ድጋፍና ትብብር የሚያስፈልገው ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። ድርጅታዊ ነጻነቱን ጠብቆ የሚንቀሳቀስ፤ የማንም የፖለቲካ ድርጅት ተቀጥያያ ተጠያቂነቱ ለኢትዮጵያ ሕብዝ ብቻ መሆኑን በተግባር እያረጋገጠ ያለ በመሆኑ በዚህ አጋጣሚ የዚህ መጣጥፍ አንባቢያን የድርጅቱን ድርገጽ WWW.SOCEPP.DE እንዲያዩ እየጋበዝን እርዳታ ለማድረግ የሚፈልጉ ኢትዮጵያን ደግሞ የሚከተለውን የባንክ አድራሻ እንዲጠቀሙ እንጋብዛለን።

SOCEPP
COMERZBANK AG
Bank account Number
128 1468 — 90
BLZ 370 400 44
Hohenzollernring 71 —
7350762 Koeln
Germany

ዋቢዎች

1. The role of National Human rights Institutions in the UN-Treaty Body process.
2. The UN-Human Rights System in the 21st Century

ከሃይማኖት ነጻ የሆነ ፖለቲካ
ታቶ ደቼሳ

መንግሥታን ሃይማኖት፤ ፖለቲካና ሃይማኖት መለየት አለባቸው የሚለው መርህ(ሴኩላሪዝም ወይም በትክክለኛው ላይሲቴ የሚባለው) የዴሞክራሲና የሬፑብሊካዊ አስተሳሰብ ማገር ምሶሶ ነው። በአጼ ሃይለ ሥላሴ ዘመን ሀገር የጋራ ናት፤ ሃይማኖት የግል ነው ሲባል የነበረው በመሰረቱ ይህንን መንፈስ ያንጸባርቅ ነበር ማለትም ይቻላል። በአሁኑ ጊዜ የዚህ መሰረታዊ መርህ ይዘትና ጠቀሜታ የተዘነጋ ነው ቢባል የተሳሳተ አይሆንም። በድህረገጾችም ሆነ መወያያ መድረኮች ሃይማኖት በፖለቲካው ውስጥ ጣልቃ እየገባ

ይታያል። ፖለቲካና ሃይማኖትን መለየት ጥፋት የመሰላቸው ክፍሎች በርከት ብለዋል። ይህ ግን መሰልጠን ሳይሆን ወደኋላ መሄድ መሆኑን ማወቅ ይገባል።

በአሁኑ ጊዜ በአለም አቀፍ ደረጃ የሃይማኖት ማክረር አቋምና እርምጃ ተስፋፍቶ ይታያል። ፖለቲካና ሃይማኖትን አናደባልቅም የሚለው አሜሪካ ለምሳሌ በአክራሪ ክርስቲያኖች ጣልቃ ገብነትና ፖለቲካም መያዙን በጆርጅ ቡሽ ዘመን በተለይ ታይቷል። ቫቲካን ራሱን የቻለ ነው ቢባልም በጣሊያን ፖለቲካ ተጽዕኖው ቀላል አይደለም። እስላም አክራሪዎች ፖለቲካ በሻሪያ ህግ ይገዛ የሚሉ ናቸው። በአፍጋኒስታንና በሳውዲ አረቢያ ሃይማኖት መቀየር በሞት ያስቀጣል። መቻቻልን ያጠፋው ይህ ፖለቲካና ሃይማኖትን የመደባለቁ አቋም መዘዙ ብዙ ሊሆን እንደሚችል የታየ ነውና ከመቼውም በበለጠ ሃይማኖትና ፖለቲካ/መንግሥት መለየት አለባቸው የሚለው መርህ ክብደትን ይዞ ይገኛል።

ላይሲቴ የተባለው ጽንሰ ሃሳብ ማለትም ፖለቲካ ሀይማኖትን መለየት ይገባል የሚለው ደሞክራሲያዊ አቋም ጸረ ሃይማኖት አይደለም። ሀይማኖቶች በፖለቲካው ጣልቃ አይግቡ ወይም ፖለቲካ በሀይማኖት ጣልቃ አይግባ ሲባል በአንድ በኩል በአንድ የተወሰነ ሀገር ልዩ ልዩ ሃይማኖቶች መኖራቸውንና መቻቻል እንደሚገባቸው ሲያመለክት(የአንድ ሃይማኖት የበላይነት ሰፍኖ የሚከተለው አድልዖ ያበጣብጣልና) በሌላ በኩል ደግሞ የእምነት ነጻነትን መብት መረጋገጥን ያመለክታል።

የሃይማኖት ተቋሞች በራሳቸው ትምህርት ቤቶች ስለ ዕምነታቸው መስበክ፤ ማስተማር ሲችሉ በመንግሥት/ሕዝብ ትምህርት ቤት ግን ሃይማኖት ጣልቃ ሊገባ አይገባውም። ተማሪዎች በሆነ ሃይማኖት ጸሎት ግዴታ ሳይገቡ የሀገርን ሰንደቅ ዓላማና መዝሙር ማክበራቸው ይመረጣል። ሬፑብሊካዊ ስርአት እንዲሁ ከሃይማኖት ነጻ መሆነ አለበት። የዳኝነቱም ስርአት እንዲሁ ከሃይማኖት ነጻ መሆን አለበት። የመግሥት የሚባልም ሃይማኖት አይኖርም። በሀገር ደረጃ የሚከበሩ በአላትም ለዚህ ለዚያ ሃይማኖት ያደሉ መሆን የለባቸውም። የሁሉንም ዋን ዋና በአላት በእኩል ማስተናገድ ይገባል ማለት ነው።

የግል ኑሮና የሕዝብ ወይም ህብረተሰባዊው መስክ የተለያዩ ናቸው። በግል ኑሮ መስክ ሃይማኖት ወይም ማንኛውም ዕምነት ቦታ አለው። በህብረተሰቡ መስክ ደግሞ ሁሉም ዜጋ እኩል ሆኖ ከብሄረሰብና ጾታና ሃይማኖት መለያዎቹ ተላቆ በዜግነቱ የሚታይበት ነው። ስለዚህም መንግሥት ጸረ ሃይማኖት ይሆናል ማለት ሳይሆን በሃይማኖቶች ጣልቃ አይገባም ማለት ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ ሃይማኖቶች ወይም የሃይማኖር ድርጅቶች በመግሥት ጉዳይ ያልቃ አይገቡም ማለት ነው።፡ ይህ ደግሞ

ከሙብትና ዴሞክራሲ፤ ከመቻቻልና ሬፑብሊኩን ከመጠበቅ አንጻር፤ የሃይማኖት ጽንፈኝነትን ለመከላከል፤ የመንግሥት በሃይማኖት የመጠቀም ፍላጎት ከማገድ አንጻር ጠቃሚና አስፈላጊ ነው።

በአሁኑ አለም በሃይማኖት የተነሳ ፍጹም አክራሪነት ተከስቶ እያደረሰ ያለው ጉዳት ለሁሉም ገሃድ ነው። የአሜሪካ አክራሪና ቀኝ ክርስቲያን የተባሉ ሃብታም ተቋሞች በፖለቲካው ጣልቃ ገብተው ይታያሉ። በኢራን የአያቶላው ሥልጣን መያዝ፤ በአፍጋኒስታን በጸረ ሕዝብ ደረጃ ሊፈረጅ የሚገባው የታሊባን አክራሪዎች ለሥልጣን መብቃት፤ በሃይማኖት የተነሳ የተስፋፋው ብጥብጥ ሁሉ የሚያመከክቱት ሃይማኖትና ፖለቲካ ሲደባለቅ መዘዙ አስከፊ መሆኑን ነው። መንግሥት ወይም የፖለቲካ ሃይሎች በማንም ሃይማኖት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያደርጉ፤ አድልዎ ሊያሳዩ አይገባም ማለት ነው። ይህ መርህ በመሰረቱ የመንግሥት ሃይማኖት የሚለውን ጽንሰ ሃሳብና አቋም የሚቃወም ነው። መንግሥት በፖለቲካው መስክ በሕዝብ ምርጫ ሁሉንም ሕዝብ ለማገልገል የሚቆም መሆን ያለበት ስለሆነ በሃይማኖት መሰረት ልዩነት ተደርጎ አንድ ሃይማኖት መንግሥት ከተባለ ግልጽ የሙብት ረገጣ መፈጸሙ የሚታወቅ ነው። መንግሥትና ሃይማኖት አንድ በሆኑባቸው ሀገሮች ሁሉ በደሎች መፈጸማቸውና ልዩነትና አድልዖ መደረጉ በግልጽ የሚታይ ነው። የመንግሥቱ እንዳለ ሆኖ በተቃዋሚ ድርጅቶች ደረጃም በዚህ ጥያቄ ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። በደርግ ዘመን ቢያንስ በእስልምናና በክርስትና መሃል አድልዎ ላለማድረግ የተወሰኑ እርምጃዎችን ወስዷል። ወያኔ በበኩሉ በሃይማኖት እኩልነት አምናለሁ ቢልም በእምነት ደረጃ ሕዝብን እያለያየ ሲያጋጭና ሲያዳማ ዛሬ እየታየ ነው። ሀይማኖት የግል እምነት ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን በዚሁ ደረጃ መያዝ አለበት። የሃይማኖት ተቋሞችም በአማኞቻቸው እየተደገፉ መንቀሳቀስ መቻል አለባቸው። በአንጻሩ መንግሥት ደግሞ የሕዝብና የሁሉ እንደመሆኑ መጠን ለአንዱ ወገንተኛ ወይም የሚያዳላ መሆን አይችልም።

የዴሞክራሲና መሰረታዊ የሕዝብ ሬፑብሊክ ስርአትን ስንደግፍ ሃይማኖትና መንግሥት/ፖለቲካ መለያየታቸውን የግድ ይሆናል። የሙብት መከበር ጥያቄ ነውና። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገሮች ደግሞ ልዩ ልዩ ሃይማኖቶች ያሉ ናቸውና ሁሉም በ እኩልነት ሆነው ግን ወደፖለቲካው መስክ ሳይገቡ መቆየታቸው በጣም አስፈላጊ ነው። የመለስ አገዛዝ በሀይማኖት ጣልቃ ገብቶ በአባ ገብረ መድህን/ጳውሎስ/ ና በ እነ ሼክራድዋን አማካይነት ችግር እየፈጠረ ነው። ከዚህም የተነሳ ሃይማኖት ልዩነትን ምክንያት ያደረጉ ግጭቶችም ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል። ይህ ደግሞ ከቀጠለ አብሮ በሰላም ይኖር የነበረውን ሕዝብ የሚያዳማና ሀገሪቷንም ለአደጋ የሚያጋልጣት መሆኑ ግልጽ ነው። በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተነሳም

ሀገራችን ውስጥ ብጥብጥ መኖሩን ለሚፈልጉ የአካባቢ ሀገሮችም በር ይከፍታል። ስለዚህም በዚህ ጥያቄ ላይ ተገቢውን ግንዛቤ መያዝና ሃይማኖትና ፖለቲካን አለማዛነቁ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው። ይህን በተመለከተ ተቃዋሚ ድርጅቶች አርአያ መሆን አለባቸው እንጂ ወያኔ በቀደደው ቦይ በመፍሰስ በሀይማኖት ጥያቄ ልዩነት የሚደረግበትን ሁኔታ መፍጠር የለባቸውም። ሃይማኖት የግል ነው፤ ሀገር የጋራ ናት። ሀይማኖት የእምነትና የግል ጉዳይ ሲሆን ፖለቲካና መንግሥት ደግሞ በሌላ መስክ ያሉ የጋራ ጉዳዮች ናቸው።

ሀይማኖትና መንግሥት የተለያዩ ናቸው/ይሆናሉ የሚለውን በፕሮግራሙ ያላሰፈረን ድርጅት ዴሞክራሲያዊ ነው ማለት ያስቸግራል። የመንግሥት ሃይማኖት ሊኖር እንደማይችልና እንደማይገባም ግልጽ መሆን አለበት።

## *የኢትዮጵያ ሴቶች የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማምጣት በሚደረገው ትግል ውስጥ መሳተፍ አስፈላጊና ወሳኝ ነው።*

*ይህች ፅሁፍ በአራት ኪሎ በከፍተኛ 14 በእስር ቤት ውስጥ በደርግ ብችሎች ክብረ ንጽህናቸውን ለተደፈሩ፥ ለተገረፉና በነፃ እርምጃና በቀይ ሽብር ለተሰውቱ ጓዲቶች፤ እንዲሁም የሕዝብ ድምፅ ይከበር ስለአሉ ብቻ በዘረኛው የወያኔ ካድሬዎችና በአጋዚ ነፍሰ ገዳዮች ለተንገላቱ፥ ለታሰሩ፥ ለተፈናቀሉ፥ ለተሰደዱና፥ ለተገደሉ እናቶችና እህቶች በመታሰቢይ ትሁን።*

የኢትዮጵያ ሴቶች በአለፉት ሥርዓቶች ውስጥ በግንባር ቀደምትነት ለቤተሰባቸው፥ ለህብረተሰባቸውና ለአገራቸው ግንባታና እድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርገዋል። ኢትዮጵያዊት ወገኖቻችን ምንም እንኳን የሚገባቸውን ያህል እውቅና፥ ምስጋናና ከበሬታ ባይሰጣቸውም ያለባቸውን ድብርብርብ ጭቆና እንደተሸከሙ የሚቻላቸውን ሁሉ ከማበርከት ወደኋላ ያሉበት ጊዜ የለም። በባህላችን ውስጥ በአንዳንድ ኋላቀርና ጎጂ አስተሳሰብ አማካኝነት ለሴቶች አስተሳሰብ፥ ጠባይና ምግባር ብዙ አሉታዊ ነገሮች ሲነገር ኖሮአል አሁንም ይሰማል። ሃቁ ግን በተቃራኒው ሴቶች በተፈጥሮአቸው አዋቂ፥ ደግ፥ አርቆአሳቢ፥ ብልህ፥ ብርቱና በራሳቸው የሚተማመኑ ናቸው። ይህንም ለማሳወቅ ብዙ እርቀን ሳንሄድ በእኛ እድሜ ክልል ያሉትን ስንገመግም ብዙ ሴቶች ከባሎቻቸው የተፋቱ እንዲሁም የሞቱባቸው ከሰው ቤት በግርድና በመቀጠር፥ ቆሎና እንጀራ በመሸጥ ቤተሰባቸውን በብቃት አስተዳድረው፤ ልጆቻቸውን ያለአባት አሳድገውና አስተምረው ለቁም ነገር ያበቁ እናቶች ለምስክርነት በሕይወት በህብረተሰባችን ውስጥ ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪ

በአገር አቀፍ ደረጃ ብዙ ሴቶች አገራቸው በጠላት ስትደፈር በጀግንነት በመዋጋት እንዲሁም የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት ክቡር ሕይወታቸውን ለትግሉ ሰጥተው አልፈዋል።

በጥንት ዘመን ማለት ከፊውዳል ሥርዓት ማህበር ማለት የግል ሀብት ማካበት ከመጀመሩ በፊት ሴቶች በሕብረተሰብ ውስጥ ከበሬታና ተሰሚነት ነበራቸው። ያም ዘመን የእናቶች ዘመን ይባል ነበር ማለትም የዘር ግንድ የሚታወቀውና የሚቆጠረው በእናት ስም ነበር። ወንድና ሴት ልጆች የሚታወቁትና የሚጠሩት በእናታቸው ስም ነበር። በዚያን ዘመን የወንዶች ሥራ ለምግብ የሚሆን አራዊት ማደን ሲሆን የሴቶች ሥራ ደግሞ ቤተሰብንና አካባቢን መንከባከና ማስተዳደር ነበር። ከጊዜ በኋላም የነበረው የዱር አራዊት ቁጥር እየቀነሰና እየተመናመነ በመምጣቱ ወንዶች ለረጅም ጊዜ ከቤተሰብ ተለይተው እሩቅ ወደሆነ አካባቢ በአደን ሥራ ላይ ይቆዩ ነበር። ሴቶችም ቀያቸውን ሳይለቁ አካባቢውንና ቤተሰባቸውን መጠበቅና ማስተዳደር ማለት ልጆቹን መመገብ፣ ማሳደግና፣ ማስተማር ነበር። አዳኞችም ከረጅም ጉዞ በኋላ ምግብ ይዘው እስኪመጡ ድረስ ቤተሰባቸው በረሃብ እንዳይልቅባቸው በመፍራትና በመጨነቅ ብልሆቹ ሴቶች በአካባቢያቸው የሚገኙትን አዝርዕቶችና ፍራፍሬዎችን ለመጀመሪያ ጊዜ የሚበሉትና የማይበሉት ለይትው በማወቅ የእርሻ ሥራን የጀመሩት እነሱ እንደሆኑ ታሪክ ይናገራል።

የግል ሀብት ማከማቸት ከተጀመረ በኋላ ወንዶች ቀስብቀስ ሀብት፣ ጉልበትና ሥልጣን እያገኙ መጥተው ሴቶችን በቁጥጥራቸው ሥር ማለት የእነሱ ጥገኛ በማድረግ የወንዶችን ዓለም ለመፍጠር ቻሉ። ባገኙትም የበላይነት በመጠቀም ልጆች በእናት የዘር ግንድ መታወቃቸው እንዲቀርና በአባት የዘር ግንድ እንዲተካ አደረጉ። ሴትም ደካማና ሁልጊዜ ያለወንድ እርዳታ በእራሷ መኖር የማትችል ምስኪን ፍጡር ናት የሚል የተሳሳተ አስተሳስብ እንደ ጥሩ ባህላችን ተደርጎ እንዲወስድ ለማስደረግ ቻሉ። በሴትም የዘር ግንድ መጠራት እንደነውርና እንደስድብ እንዲቆጠር እንዲሁም የሴት ሥራ በማድቤት እንዲወሰንና ሥራዋም ዋጋ ቢስ ተደርጎ እንዲታይ በተለያዩ መንግሥታዊና የሃይማኖታዊ ተቋማት አጋዥነት በሀብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ተደረገ።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ስለሴቶች ሚናና አስተዋፆ ማለት በድንጋይ፣ በብረት፣ በባሪያና በፊውዳልና በካፒታልስት ሥርዓቶች እንዴትና ምን እንደነበር በታሪክና በሀብረሰብ ጠበብቶች/አዋቂዎች ብዙ ምርምርና ጥናት ሊደረግበት የሚገባውንና ብዙ መጻሕፍት ሊጻፍበት የሚችለውን ትልቅ ጉዳይ ነው። በመሆኑም ለርዕሳችን መግቢያና መንደርደሪያ እንዲሆን በማስብ ከህብረተሰብ ጥናት (sociology) የይድረስ ይድረስ

በቁንፅል በማቅረባችን ትልቅ ይቅርታ እንጠይቃለን። የጽሁፉ ዋና ትኩረት የሴቶች ተሳትፎ በአለፈው መቶ አመታት በዓለም አቀፍ ደረጃ በበለፀጉና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በአለባቸው አገሮች ውስጥ ሴቶች በትግላቸው ያገኙትን መብቶችና ወደፊት የሚጠብቃቸውን የትግል መጠንና ዓይነት ለመቃኘት ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ያገራችን ሴቶች ከዓለም አቀፍ ሴቶች በተመክሮ ደረጃ ምን ሊማሩ ይገባል? እንዴትስ የዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ሊያከብሩ ይገባል? እንዲሁም አሁን በመካሄድ ባለው ብሄራዊ አገር የማዳንና የሥርዓት ለውጥ ትግል ውስጥ ሴቶች እንዴት የትግል ተሳትፎአቸውን ይበልጥ ያጎለብቱ? የሚሉትን ጥያቄዎችንም ይዳስ ሳል።

የሴቶች ጭቆና ዘርፈ ብዙ መሆኑን በመረዳት ማለት የፆታ፣ የሰብዓዊ መብት ረገጣ፣ የፖለቲካና የኤኮኖሚ መብቶች እጦትን ያካተተ ነው። በመሆኑም የሴቶች ጥያቄ መልስ ሊያገኝ የሚችለው በዴምክራሲያ ሥርዓት ባለበት አገር ውስጥ ብቻ ነው። ስለሆነም በአገራችን በኢትዮጵያ ስርነቀል የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማምጣት በሚደረገው ትግል ውስጥ ሴቶች የትግላቸውን ከፖለቲካና ከሲቪክ ማህብራት ጋር ማስተባበርና ማቀራኘት እንዲችሉ በትግል ላይ ያሉ ወንዶች የአስተሳሰብ ለውጥ ማድረግና የሴቶች እኩልነትን መቀበል አስፈላጊና ወሳኝ መሆኑን አንፅኦት ለመስጠት ነው። በአጠቃላይ የምንመኘውን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ያለሴቶች ተሳትሮ ማምጣት አይቻልም። የሴቶች የትግል ተጋድሎና ለወደፊትም አቅጣጫ ፍለጋ ለውይይት እንዲያመች በሁለት ከፍለን ማለት በዓለም አቀፍና በአገር አቀፍ ደረጃ ለማቅረብ እንሞክራለን።

## *<u>የሴቶች የትግል ተጋድሎ፤</u>*

### *<u>በዓለም አቀፍ ደረጃ፣</u>*

በመላው ዓለም የሚገኙ ሴቶች በፆታ፣ በፖለቲካ፣ በኤኮኖሚና በባህል የሚደርስባቸውን ጭቆናን በተለያዩ ሥርዓተ ማህበራት ውስጥ ይህ ነው የማይባል ትግልና መስዋዕትነት በመክፈል አንዳንድ የማይናቁ ድሎችን ተጎናፅፈዋል። በአለፈው መቶ አመት በአውሮፓ፣ በአሜሪካንና በአውስትራሊያ ሴቶች መብታቸውን ወዲያው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲመሰረት አላገኙም። ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ በትግላቸው የፓለቲካና የኤኮኖሚ ጥቅሞች ማለት የመምረጥና የመመረጥ መብት፣ የስራ ሰዓት መቀነስ፣ የስራ ቦታቸው ለጤንነት ተስማሚ እንዲሆን፣ ለኩል ሥራ እኩል ክፍያና ለወንዶች ብቻ የነበረውን የዳኝነት፣ የህኪምነት፣ የአስተዳደርና በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ማለት ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ መሳተፍ ማለት ተማሪም አስተማሪም የመሆን መብት ለማግኘት በቅተዋል። ለተመክሮ እንዲረዳ የዓለም አቀፍ ሴቶች በያገሮቻቸውና በህብረት ያደረጉትን አበይት ተጋድሎና ያስገኙት ድሎች በአጭሩ እንድናቀርብ ይፈቀድልን። አመተ

ምህረቶችና ቀኖችና ወሮቹ እንደአውሮፓ አቆጣጠር መሆኑን ልብ እንድትሉን በትህትና እንጠቃለን።

- በ1908 ዓ. ም. በኒዮርክ ከተማ 15 ሺ ሴቶች ለተሻለ ክፍያ፣ የስራ ሰዓት ቅነሳና የመምረጥ መብታቸው እንዲከበርላቸው ሰላማዊ ሰልፍ አደረጉ።
- በ1909 ዓ.ም. የሴቶች ብሄራዊ ቀን ፌብርዋሪ 28 ቀን ሆኖ እንዲከበር የአሜሪካን የሶሻሊስት ፓርቲ ታወጀ።
- በ1910 ዓ.ም. በኮብንሃግን ከተማ የዓለም አቀፍ ሶሻሊስት ከአስራ ሰባት አገሮች የመጡ ከመቶ በላይ የሚሆኑ ሴቶች ተካፋዮች በተገኙበት ስብሰባ ላይ ምንም እንኳን ቀኑ ባይወሰንም የሴቶች አለም አቀፍ ቀን መከበር እንዳለበት በመስረተ አሰብ ደረጃ ስምምነት ላይ ደረሱ።
- በ1911 ዓ.ም. የመጀመሪያው የሴቶች ዓለም አቀፍ ቀን በማርች 19 ቀን በአውስትሪያ፣ ዴንማርክና ጀርመን ተከብሮ ዋለ። በዚህ ቀን የሴቶችን የሰብዓዊና የእኩልነት መብት ጥያቄን በመደገፍ ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ወንዶችና ሴቶች ትዕይንተ ሕዝብ አደረጉ። በሳምንቱም በኒውዮርክ ከተማ በአስቃቂ የእሳት አደጋ ከ140 በላይ የሚሆኑ ሴቶች እጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ውስጥ መቃጠል የዓለም ሕዝብን ቀልብ የሳበ በመሆኑ በአሜሪካ ምክር ቤት የስራተኛ ህግ ማለት የስራተኛውን ሁኔታንና ደህንነት የሚመለከት ሕግ እንዲወጣ አስገደደ።
- በ1913-1914 ዓ.ም. የመጀመሪያው የአለም ጦርነት ዋዜማ የአውሮፓ ሴቶች በዓለም ላይ ሰላም እንዲሰፍን ጦርነቱን በመቃወም ትዕይንተ ሕዝብ አደረጉ። የራሻም ሴቶች ለመጀመሪያ ጊዜ የአለም አቀፍ የሴቶችን በዓል ቀን በፌብሩዋሩ 13 ቀን አክብረው ዋሉ።
- በ1917 የራሻ ሴቶች በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ውስጥ ከሁለት ሚሊዮን በላይ የአገራቸው ወታደሮች በማለቃቸው "ሰላምና ዳቦ" እንፈልጋልን በሚል መፈክር አራት ቀን የፈጀ ሰላማዊ ሰልፍ አደረጉ። በዚህ ሴቶች ተቃውሞ ሳቢያ የኦክቶር አብዮት ተቀጣጥሎ የዛር ንጉሳዊ መንግሥት እንዲያከትምና የቦልሸቪክ ፓርቲ የመንግሥት ሥልጣን እንዲይዘ ተደረገ። አዲሱም መንግሥት የሴቶች መብት የሚያስከብር አንቀፆች በሕገ መንግስት ውስጥ እንዲካተትና በተጨባጭም ለልጆች መዋዕለ ህጻንት በነፃ አገልግሎት እንዲስጥና ሴቶች በነፃ ትምህርትና የሥራ ስልጠና እንዲሰጣቸው ተደረገ። የመምረጥ መብትና

ካልተስማማቸው ባሎቻቸውን የመፍታት መብት እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ ልጅ የማስወረድ መብት ተሰጣቸው። ለሴቶችና ለልጆቻቸው መንግስት እርዳታና (welfare) እንክብካቤ እንዲያደርግላቸው በሕግ ፀድቆ በስራ ላይ ዋለ። በእስታሊን አምባገነናዊ ዘመንም የሴቶችን ጉዳይ የሚከታተለውና ጥቅማቸውን የሚያስከብረውን ተቀዋም እንዲዘጋ ተደረገ፣ ቀስ በቀስ ሴቶች በትግላቸው ያገኙትን መብቶች እንዲሸረሸሩ አስደረገ።

- በ1920 ዓ.ም. የአሜሪካን ሴቶች በትግላቸው የመምረጥና የመመረጥ መብታቸውን አገኙ።
- በ1960 የአሜሪካ ሴቶች እንደአቻቸው የአውሮፓ ሴቶች ከፋብሪካና ብዙም ገንዘብ ከማያስገኑ ሥራዎች ባሻገር ጥሩ ሥራ የሚያገኙበት የእድል በር እንዲከፈትላቸው ተንቀሳቀሱ።
- በ1963 አሜሪካዊቶች ለኩል ሥራ እኩል ክፍያ በሕግ እንዲደነገግ አስደረጉ
- በ1960-1964 ዓ.ም. የጥቁር አሜሪካኖች በዘር (በቀለማቸው)፣ በፖለቲካና በኤኮኖሚና በባህል የሚደርስባቸውን በደሎች በመቃወም በተደረገው ትግል ሴቶች ማለት ነጭና ጥቁር የአሜሪካ ሴቶች ተካፍለዋል።
- በ1964 ዓ.ም. አፍሪካ-አሜሪካና የነጭ አሜሪካ ተራማጅ ወንዶችና ሴቶች እንርብርቦሽ (Civil Right Act) የሲቪል መብት እንቀጽ በሕገ መንግሥት ውስጥ እንዲካተት ለማደረግ በቅተዋል። በአጭሩ ሕጉ የሚለው አንድ ሰው ሴትና ወንድ በዘር፣ በፆታና በሃይማኖት ልዩነት ምክንያት ከህብረትሰብ እንዳይገለል፣ ጥቃት እንዳይደርና በደል መፈጸም በሕግ የተከለከና የሚያስቀጣ ነው የሚል ነው።

እዚህ ላይ ግንዛቤያችንን በበለጠ ለማዳበር የሁለቱን ጽንስ አሳቦችን ማለት የሊብራል ዴሞክራሲንና የሶሻሊዝምን ደካማ ጎናቸውን (deficiencies) ለማራቅና የሁለቱን በጎ ንጥረ ነገሮች ያካተተ ማህበረ ዴሞክራሲ (social democracy) የሚለውን ፅንስ ሀሳብ በአማራጭነት ለማቅረብ ይፈቀድልን። ይህ ርዕስ እራሱን የቻለ ትልቅ ጥናት የሚጠይቅ በመሆኑ የሴቶች ተሳትፎና ሚና በሶሻል ዴሞክራሲ ሥርዓት በአሉባቸው አገሮች ውስጥ ማለት በምዕራብ አውሮፓ፣ በአውስትራሊያና በኒውዝላድ በሰላማዊ ትግላቻቸው አድርገው ያገኙትን ድሎችና ወደፊት የሚገጥማቸው ትግሎችን በአጭሩ ለአብነት ያህል ለመጠቃቀስ እንሞክራለን።

- የስካንድኔቪያ አገሮች ማለት ኖርዌ፣ ፊንላንድና

ሰዊዲን በማንኛውም የኢኮኖሚ ልማትና የእድገት መለኪያ እነዚህ አገሮች ከፍተኛ ቦታ ይዘው ይገኛሉ። ያንድ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ያለበት አገር ትልቅነቱ፣ ብልጽግናውና ሁለንተናዊ እድገቱ የሚለካው በአገሩ ውስጥ ያሉትን ደሃዎች፣ አዛውንት፣ ያለአባት ልጆቻቸውን ለሚያሳድጉ እናቶች፣ ለአካለስንኩላን በሚያበረክቱ ማህበራዊ አገልግሎቶች ማለት ገንዘብና የነፃ ህክምና እንዲሁም ሌሎች አገልግሎቶች ለመስጠት መቻሉ ነው። እነዚህ አገሮች ለመላው ዓለም በሶሻል ዴሞክራሲ ሥርዓት በአርአያነት ተጠቃሽ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። በአለፉት አመታት በተለይ ከ1990ቹ አመታት ጀምሮ በዓለም የገበያ ውድድር ሰበብና በግሎባላይዜሽን ክስተትና ጎጂ ገጽታው ተፅእኖ እንዲሁም በተከታታይ ወግ አጥባቂ ፓርቲዎች ሥልጣን በመያዛቸው ምክንያት በትግል የተገኙ ህብረተሰባዊ አገልግሎቶች የተቦረቦሩ ሆነው ይገኛሉ። ወደፊትም ሴቶችና ወንዶች በትግል ያገኙትን መብታቸውንና ጥቅማቸውን ለማስከበር ሌላ ዙር ትግል ይጠብቃቸዋል ማለት ነው።

- በቀረው የምዕራብ አውሮፓ አገሮች እንግሊዝ፣ ፈረንሣይና ጀርመን የተሟላ ባይሆንም ሶሻል አገልግሎቶች ይሰጣሉ። በተለይም እንግሊዝና ጀርመን እራሳቸውን እንደ ሶሻል ዴሞክራቲክ አገር አድርገው ይቆጥራሉ። በአለፉት አመታት የወግ አጥባቂ ፓርቲዎች ለሥልጣን መብቃትና በወሰዱት የፓሊሲ እርምጃዎች ቀስ በቀስ ሶሻል አገልግሎቶችን ቦርብረው ቀፎአቸው ብቻ እንዲቀር አድርገዋል። በምዕራብ አውሮፓ የሚገኙት የዓለም አቀፍ የሴቶች ማህበር አባሎች ብዙ የትግል ተመክሮ ያላቸውና በትግል የተፈተኑ ጠንካሮች በመሆናቸው ለጥቅማቸውና ለመብታቸው ተግራሪ የሆነውን ዓለም አቀፍ ትራንስ ኮርፖሬሽን ማለት የግሎባላይዜሽን ተቀዳሚ ተጠሪ የሆነውን አጥብቀው እንደሚታገሉ አያጠራጥርም።

- በአውስትራሊያና በኒውዝላድ ያሉት ሶሻል አገልግሎቶች ከእስካንድኔቪያ ያልተናነሰ ነው። በእነዚህ አገሮች

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የወግ አጥባቂ ፓርቲዎች ከሶሻል ዴሞክራሲ ፓርቲ ጋር በመወዳደር ለሥልጣን በመብቃታቸው በትግል የተገኙትን አንዳንድ ጥቅሞችን ለመሸራረፍ በመሞከር ላይ ናቸው።

የዓለም አቀፍ ሴቶችና ተራማጅ ሃይሎች የወደፊት ትግል በጣም የተወሳሰበና ዘርፈ ብዙ ችግሮችን የያዘ ነው። በመሆኑም ትግላቸው ከአሁን የበለጠ አንድነት፣ ትብብርና ቅንጅት የሚጠይቅ ትግል መሆን እንዳለበት የሚያመላክት ይመስለናል። ድንበር የለሹ አዲሱ የግሎባላይዜሽን ሥርዓት በትራንስ ኮርፐሬሽን አማካኝነት የምዕራብ አገሮች ሴቶች በትግላቸው ያገኙትን ድሎች ቀስ በቀስ በመቦርቦር ለማጥፋት እየተንቀሳቀሰ ያለ ሃይል ነው። የዓለም አቀፍ ሴቶች ድርጅት ከተራማጅ ሃይሎች ጋር በመተባበር የግሎባላይዜሽን ጎጂው ገጽታውን በመቃወም ለምሳሌ የአየር ብክለትን በተመለከተ ከድበር የለሹ ትራንስ ኮርፐሬሽን ጋር ግብግብ በማድረግ ላይ ናቸው። ማለት ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ፣ ጥናታዊ ጽሁፎች፣ ሴሚናርና ሲምፖዚየም በማድረግ ለሕብረተሰባቸው ንቃተ ህሊና በመስጠት ላይ ይገኛሉ።

<u>*በአገር አቀፍ ደረጃ:*</u>

የሴቶች ጥያቄ መልስ የሚያገኘው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በአገራችን ሲመሰረት ብቻ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከ75 ሚሊዮን በላይ ነው። አምሳ በመቶ በላይ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው። በመሆኑም ያለነሱ ሙሉ ተሳትፎ እኩልነት፣ ነፃነት፣ ዴሞክራሲ፣ ሰላም፣ ልማት፣ እድገት ሊመጣ በፍጹም አይቻልም። እንዲያውም በአንድ እጅ ማጨብጨብ ነው የሚሆነው። ኢትዮጵያ ሴቶች የረጅም ጊዜ የትግል ታሪክ ያላቸው ናቸው። ከእኛ ዘመን ስንነሳ በየካቲት 66 አብዮት በገጠርም በከተማም ከደርግና ከጠባቦች ጋር ታግለዋል፤ አሁንም ከወያኔ አምባገነን ጋርም በአገርና በዓለም አቀፍ ተደራጅተው በትግል ላይ ናቸው።

የኢትዮጵያ ሴቶች በአገራቸው ግንባታም ይሁን በጠላት ወረራ ጊዜም አገርን በመከላከል ከወንዶች ወንድሞቻቸው፣ ባለቤቶቻቸውና፣ ልጆቻቸው ጋር በማበር ትልቅ አስተዋጽዖና መስዋዕትነትን ከፍለዋል። ለማስረጃነት እንዲረዳ እስቲ የኢሕአፓ የካቲት 29 ቀን የዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ የሴቶች ቀን አስመልክቶ ያወጣውን መግለጫ እንመልከት።

*"በኢትዮጵያ በተካሄዱ ትግሎች ሁሉ ሴቶች ወሳኝና የሚደነቅ ሚና ነበራቸው። በአድዋ ጦርነት እቴጌ ጣይቱ ስማቸው ገኖ ቢነሳም ከ30 ሺ ያላነሱ ሴቶች በዘያ ጦርነት ልዩ ልዩ ፈርጅ ተሳትፈዋል። የሙሶሊኒ የጣሊያን ጦር ኢትዮጵያን ሲወርም ብዙ ሺ ሴቶች በአርበኝነት ታግለዋል። የውስጥ አርበኞች ድርጅት ዋና አባላት*

*ሴቶች ነበሩ። ...በአሄው ዘመን ሆነ በዘመነ ደርግ ደግሞ የትግሉ እምብርት በመሆን የቆራጥነት ታሪክ አስመዝግበው ያለፉ እህቶቻችንና እናቶቻችን ጥቂት አይደሉም። በመሆኑም ትግሉ ሊደምቅና ሊጠነክር የሚችልበት ሁኔታ እውን ሆኗል።"*

*የገጠር ሴቶች፡*

ስማንያ በመቶ የሚሆነው ያገራችን ሕዝብ የሚኖረው በገጠር ነው። በገጠር የኢትዮጵያ ሴቶችን ጭቆናና አኗኗር አስመልክቶ የእድሜ ባለፀጋ የሆኑት አባታችን፡ ታጋዩና ደራሲው ኮለኔል አስናቀ እንግዳ "ዘመን ያልሻረው የሴቶች አበሳ" በተሰኘው መጽሐፋቸው ውስጥ በመታሰቢያነት ያሰፈሩትን ቁም ነገሮች ማለት አሁንም በከፋ መልኩ በወያኔ አምባገነን መንግሥት እየተፈፀሙ ያሉ በደሎች በመሆናቸው በአማኝነት እንድናቀርብ ይፈቀድልን።

*አድካሚ የቤት ሥራዎች፡*

- ልጅ አዝለው ሲፈጩ እጆቻቸው ለቆረፈደባቸው የገጠር ሴቶች
- ወንዝ ወርደው ውሃ ሲቀዱ፤ በጀርባቸው አንግተው አቀበት ሲውጡና ቁልቁለት ሲወርዱ ወገባቸው ለጎበጠባቸው እናቶችና እህቶች
- በዱር ውስጥ እንጨት ለቀመው ሲሸከሙ ጀርባቸው ሞረድ በመሆን ለሻከረባቸው
- በራሳቸው ዕቃ ሲሸከሙ ጸጉራቸው ለተመላለጠባቸው
- በጀርባ (በአንቀልባ) የታዘለ ሕፃን ልጅ ሽንት በቂንጃቸው ላይ ለጎረፈባቸው
- ሕፃናትን በማጥባት ጡታቸው ቀረንጨ ለሆነባቸው
- ጥጥ ለፈትሉ በጭንቸው ላይ ያሸከረከሩት እንዝርት ጭናቸውን ላበለዘባቸው
- የቤት ዕቃ ሞስብ፡ ስፌድ፡ እንቅብ፡ ቁና፡ አገልግል፡ ወንፊት ሲሰፉ በወስፌ እጃቸው ለተወጋባቸው
- የእህል መያዣ ጎታ፡ ደንገል፡ ሲሰሩ ብርድ (ኒሞኒያ) መትቷቸው በሳል ለተቃዩ
- እንጀራ ሲጋግሩ፡ ወጥ ሲሠሩ፡ እንኩሮ ሲያነኩሩ ዓይናቸው በጢስ ላሞጨሞጨባቸው፡ ጭናቸውን ብግን ለበላቸው
- በርበሬና ኑግ ሲወግጡ ሽንጣቸው እየተጠማዘዘ በውጋት ለተሰቃዩ

*የግብርና ሥራዎች፡*

- በግብርና ተሰማርተው በዋልካ ውስጥ ሲጎለጉሉ እግራቸው ለተሰነጣጠቀባቸው
- ሲያርሙ እሾህ ለወጋቸውና ጣቶቻቸው ፈለግ ላወጡባቸው
- እህል ተጎንብሰው ሲያጭዱና አውድማ ሲለቀልቁ በድረት ውጋት ለተሰቃዩ

*የሕክምና የመጓጓዣ (transportation) እጦቶች፡*

- በሕክምና እጦት በወሊድ ተሰቃይተው ለሞቱት

- ሙጀሌ የተባለ ተባይ እግሮቻቸውን ላጠመመባቸው
- ያለጫማ ራቅ ወዳለ ገበያ ሲሄዱ እሾህ ለወጋቸው

*በባሕል ተፅኖ የሚደርስ በደሎች*

- በወንድ ማን አህሎኘነት በዱላ ለደቀቁ፣ በአለንጋ ለተገረፉት
- ልጅ አዝለው ተጎንብሰው የባላቸውን እግር ሲያጥቡ ነርቦቻቸው ከወለል ጋር ለተፋተጉባቸው
- በወንድ ቅናዓት አፍንጫቸው ለተፎነነባቸው፣ ከንፈራቸው ለተቆረጠባቸው
- ወንድ ጉንጫቻቸውን በጥፊ እየመታ ማዲያት ላበላቸባቸው
- በዓመፅ ክብረ ንጽሕናቸው ለተደፈረባቸው
- በቁባትና ውሽማ በቅንዓት ለተሰቃዩ
- ወንዶች በሚስት ላይ ሚስት እየደራረቡ በቅንዓት ማዕበል ላለቁ
- በወንድ ንቀት ለተሸማቀቁ ሴቶች

ከላይ በዝርዝር የሰፈሩት ድርብርብ የሴቶች ጭቆናዎች ሊወገዱ የሚችሉት በትግል ማለት ሴቶች በያታ ሉብቻቸው በግል ተደራጅተው ለሙብታቸው በመታገልና በወል (ጋራ) ከፖለቲካ ድርጅቶችና በሲቪክ ማህባራት ጋር በማበር ወይም በቀጥታ በፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ ገብተው ከተራ አባልነት አንስቶ እስከ አመራር ባለው እርከን በመሳተፍ ሥር ነቀል የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚና የሶሻል ለውጥ ማለት የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማምጣት መሳተፍ አለባቸው። ለዚህም የፖለቲካ ድርጅት አባሎች በአርያነት ከመጥፎ ጎጂ ባህል ተላቀው ማለት ከራሳቸውን ጋር ታግለው ነፃ በመውጣት ሴቶች እናቶቻችን፣ ሚስቶቻችን፣ እህቶቻችንና ልጆቻችን እኩልነት ከልባቸው እጃቸውን ዘርግተው ወደ ትግሉን በብዛት እንዲቀላቀሉ ከአሁን የበለጠ ጥረት ማድረግ ይገባናል፤ ይጠበቅብናል።

*የከተማ ሴቶች፥*

ጭቆና ምንም እንኳን በመልኩ ከገጠር ሴቶች የሚለይ ቢመስልም የጭቆና ይዘታቸው አንድና ተመሳሳይ ናቸው። ይህን መሰረተ አሳብ ለማገናዘብ እንዲረዳ የኢሕአፓ ልሳን የሆነውን የዴሞክራሲያ ቅጽ 33 ቁጥር 6 "ሴት ልጅ ከታገለች የድል ቀን ቀረበች" በዋቢነት እንመልከት።

*"የገጠሯን ኢትዮጵያዊት መራራ ህይወት ስንዘክር፣ በከተማ የምትኖረዋ ሴት ህይወት የተሳል ነው ማለት አይደለም። የዚችኛው ኑሮ ደግሞ ለውርድትና ለዘመናዊ ባርነት የተጋለጠ ነው። በከተማ የሥራ ማጣቱን ትንተርሶ ከሚመጣ የኑሮ ውድነት ጋር በተየያዘ ክስተት፣ በከተማ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊት የልብ ጠባሳን ብቻ ሳይሆን የአዕምሮ ስቃያንም ጭምር በሚያስከትል ቀጭት ተዘርዝሮ የማያልቅ ግፍና በደል ይፈፀምባቸዋል። የሚቀምሱት የሚልሱት በማጣታቸው ምክንያት ሳይወዱና ሳይፈቅዱ፣ ኢትዮጵያዊ ባህላቸውን ብቻ ሳይሆን ክብር*

ሰብዕቸናውን ጭምር በሚያዋርድ ተግባር መሰማራታቸው ዓለም ያወቀው አንዱ መለያችን ሆኗል። ዛሬ በከተማ የሚታየውን የህገራችንን ሴቶች ሁኔታ በቅርብ ከሚከታተል ማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር፣ ሀገራችን ኢትዮጵያ የቱን ያህል እንደትዋረደችና ማንነቷም እየጠጋ መሄዱን በቀላሉ ይገነዘባል። ይህ ትውልድ ትኩረቱ፣ በአገር የማዳን ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በማንነት ፍለጋ ላይም ጭምር እንደሆነ መገንዘብ የሚያዳት አይደለም። ዛሬ አንድ ኩሩ ኢትዮጵያዊ አባት፣ ለአቅ ሄዋን ያደረሰችውን ሴት ልጁን፣ “እባክሽ ልጀ ውንድሞችሽና እህቶችሽ በረሃብ ከሚያልቁ እሰቲ ወጣ ብለሽ አንድ ነገር ፈልጊ” ማለት ያልተለመደ እንዳልሆነ ልባቸው የደም እምባ እያደማ የሚፀፀቱ አዛውንቶች ቁጥር በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ይህ በሴቶች ላይ የሚከናወነው ጉድና ብሔራዊ ውርደት ከሀገር ውስጥ አልፎ ተርፎ የዓ ለም አቀፍ መልክናድርጊት እያያዘ ከመጣ አመታት አስቆጥሯል። ዛሬ ሀገራችን የመንግሥት ሥልጣን ጨብጬለሁ በሚለው ወራዳ ዘረኛ ብድን ተባባረነትና ግፊት፣ በአያሌ ሺ የሚቆጠሩ ወጣት ሴቶች ላዘመባዊ ባርነትና ሴተኛ አዳሪነት ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ሀገሮች እንደ ንግድ ሸቀጥ የይለፍ ሰነድ እየተሰጣቸው በመጉረፍ ላይ ናቸው፣ በሌባኖስ ዋና ከተማ በቤይሩት ብቻ ከሃያ አምስት ሺ በላይ የሚሆኑ ወጣት ኢትዮጵያዊት ዜጎች እንደሚገኙ በሰነድ የተረጋገጠ ሃቅ ነው።”

የፖለቲካና የሰብዓዊ መብት እመቃ እንዲሁም ኑሮ አንገፍግፏቸው ወደ ጎረቤት አገሮች ማለት ኬንያ፣ ሱዳን፣ ጅቡቲና ሱማሊያ የሚሰደዱ ከዚያም ወደ ሦስተኛ አገር ማለት ከሱማሊያ ወደ የመን በጀልባ ከብዙ ስቃይ በኋላ ሲደርሱ፤ ቀሪዎች ብዙዎቹ ሴቶች ከነልጆቻቸው ሰምጠዋል። ከሱዳንም ወደ ሊቢያ ለመድረስ በስህራ በርሃ ቀልጠው የቀሩትን እህቶች ቤታቸው ይቁጠራቸው፤ ሊቢያም የደረሱት አሁን እንደምንሰማው የሚደርስባቸው ስቃይ በጣም የሚዘገንን ነው። በደላቸውን ይበልጥ በተጨማሪ ግልጽ ለማድረግ ዴሞ ቅጽ 33 ቁጥር 6 እንጥቅሳለን።

“በዐረብ ባሕረ ሰላጤ ሀገሮችና በዐረቢያ ሳውዲት የተሰደዱት በበርካታ ሺ የሚቆጠሩት ኢትዮጵያዊት ዜጎች የሚደርስባቸው በደልና ግፍ የሚያልቅ አልሆነም። በቤይሩትና ባህሬይን ከተሞች በቤት አግልጋይነት የተሰማሩት ወጣት ኢትዮጵያዊት በአሰረዎቻቸው የሚደርስባቸውን ኢሰብዓዊ ግፍ መሸከም እያቃታቸው ከሰቃዩ ለማገላገል ሲሉ ከፎቅ ላይ እየተፈጠፈጡ ራሳቸውን የሚያጠፉት ቁጥራቸው በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ከአንድ ዓመት በፊት በሳውዲት አረቢያ ከተማ በጀዳ ያለ ተገቢው ህጋዊ ፍርድ በስቅላት የተገደለችው ወጣት ኢትዮጵያዊት የሚዘገንን አፈፃፀም የዓለምን ሕዝብ ህሊና እንደረበሸው የቅርብ ትዝታ ነበር። በጣም የሚያሳዝነውና የሚያስተዛዝበው ደግሞ ይህን አሳዛኝ ግድያ መላው ዓለም ዲያውግዘው፣

*የወያኔ የውጭ ጉዳይ ሰዎች የዲፕሎማቲክ ተቃውሞ እንኳን አለማሰማታቸው ነው።”*

በኢትዮጵያዊት ሴቶች በተለይም በከተሜዎች የሚደርሱትን አንኳር የሆኑትን አበሳና ስቃይ እንመልከት።

- አብዛኛዎቹ የትምህርት እድል የተነፈጋቸው፣ ናቸው። ትምህርት ቤት የገቡትም ከስምንተኛና ከአስረኛ እንዲሁም አስራ ሁለተኛ ያጠናቀቁ ሥራ ፈት እንደወያኔ አባባል ቦዘኔ ሆነዋል።

- ያለፍላጎታቸው እራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ማለት ወላጆቻቸውን ለመርዳት በሴተኛ አዳሪነት መሰማራት፤ በዚህ አድራጎታቸውም ለቀሳፊ በሽታ ማለት ለኤድስ በሽታ በቀላሉ እንዲጋለጡ አድርጓቸል።

- በወያኔ ደላላዎች (sugar daddy) አማካኝነት እራቁታችውን በዳንኪራ ቤቶች እንዲደንሱና የተቀሩትም ወደ መካከለኛ ምስራቅ አረብ አገሮች ስራ እናስቀጥራችኋለን በሚል ለባርነት ተዳርገዋል።

- በግርድና ላይ ለተሰማሩት በቀጣሪዎቻቸው ያለፍላጎታቸው የሚደርስባቸው መደፈር ምክንያት በአጋጣሚም ዲቃላ ከወለዱ ያለአባት ልጅ ማሳደግ ጣጣ ውስጥ እንደሚገቡ ይደረጋሉ።

- እናቶች ልጆቻቸውን በትንሽ ገንዘብ ለውጭ አገር ሰው በጉዲ ፈቻ እንዲሰጡ ይደረጋል። ሕጻናቶቹም የአገራቸውን ባህል፤ ታሪክና ቋንቋዎች ሳይውቁ እንዲያድጉ ይፈረድባቸዋል።

<u>*ማጠቃለያ*</u>

የኢትዮጵያ ሴቶች ከአለባቸው የፆታ ጭቆና በተጨማሪ በአገራችን የፓለቲካ፣ የኤኮኖሚና የሶሻል ትግሎች ውስጥ መሳተፍ አስፈላጊና ወሳኝ መሆኑን ለማስጨበጥ ጥረት አድርገናል ብለን እንገምታለን። የዓለም አቀፍ የሴቶች ድርጅት ማለትም የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በአሉበትና የአምባገነንን ሥርዓት በተንሰራፋባቸው አገሮች ውስጥ ለምሳሌ የኢትዮጵያ ሴቶች በሴትነታቸው ትግላቸውን እንዴት አድርገው ሊያቀናጁና ሊያስተባበሩ ይገባል የሚለውን ለመዳሰስ ሞክረናል። የዓለም አቀፍ የሴቶች ድርጅት የተጋድሎ ታሪክ፣ መቼና እንዴት እንደተጀመረ፤ በትግላቸው ያገኙት ድሎችን እንዴት እንደሚንከባከቡና ወደፊትም የሚመጣባቸውን ችግሮች እንዴት ሊወጡት እንደሚገባ በያመቱ በዓላቸውን ለማክበር በመሰብሰብ ውይይትና፣ ጥናቶች በማድረግ እቅድ እንደሚያወጡ ተገንዝበናል።

ኢትዮጵያዊት ወገኖች ከዓለም አቀፍ የሴቶች ማህበር ተመክሮዎች ምን ሊማሩ ይገባቸዋል የሚለውን በሚቀጥለው በዓላቸው ቢያጠኑትና ቢወያዩበት ጠቀሜታ ይኖረዋል ብለን እንገምታለን።

የአለም አቀፍ የኢትዮጵያ የሴቶች ድርጅት ሁለተኛ አመቱን አስቆጥሯል። በመሆኑም የኢትዮጵያ ሴቶች ተሰባስበው ትግላቸውን በይበልጥ ለማጠናከር በአገር አቀፍ ደረጃ መደራጀታቸውና የዓለም አቀፍ የሴቶች ማህበር አባል መሆናቸው እስየው የሚያሰኝና መበረታት ያለበት ጉዳይ ነው። እህቶቻችን ለዖታ መብታቸው ከመታገል ባሻገር አሁን ከወያኔ አምባገነን መንግሥት ጋር እየተደረገ ባለው የሞትና የሽረት ሁለገብ ትግል ውስጥ በብዛት ገብተው መሳተፍ ትግላቸውና የጋራ ትግላችን ግብን እንዲመታ ያደርጋል።

የዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን የካቲት 29 ቀን (March 8) በመላው ዓለም በድምቀት ተከብሮ ውሎአል። የኛም የኢትዮጵያ ሴቶች የዓለም አቀፍ ድርጅት የማህበሩ አባል እንደመሆናቸው መጠን የዘንድሮው ከአለፈው አመት በበለጠ በዓይነትም በጥራትም ባለው መልክና ዝግጅት በአንክሮት በአገራችን እየደረሰ ያለውን መከራ በሁለንተናዊ መልኩ በመርመር በዓሉን አክብረውታል። የሴቶች ዓለም አቀፍ የበዓል ቀን የካቲት 29 (March 8) በዴሞክራሲያዊና፣ በሶሻል ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቶች ባለባቸው አገሮች ተከብሯል። የእኛም እህቶች ገና የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት በትግል ላይ ስለሆኑ አገራችንን ከጥፋት ለማዳንና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማምጣት ማለት ለአንድነት፣ ለነፃነት፣ ለእኩልነት፣ ለፍትህና ለርትዕ ለማግኘት የሚደረገው ትግል ይበልጥ ለማስተባብርና ለመቀስቀስና ለማቀናጀት ጥረት ያደረጉበት በዓል ነው።

የሴቶች ጥያቄ በሚመለከት ደርግና ወያኔ ሁለቱ ተራማጅና ዴሞክራት ነን ባዮች ስለሆኑ በሕገ መንግሥታቸው ውስጥ የሴቶች መብት መከበር የሚል አንቀጾች አስፍረዋል። በተጨባጭ ግን ሁለቱም አድሃሪና አምባገነን በመሆናቸው ያስፈሩት ሕግ የወረቀት ነብር ከመሆን ያላለፈ ነው። አንድና ሁለት ሴቶች ያውም ዘረኛ ወያኔ የሆኑትን በምኒስቴርነት መሾም ለሴቶች ጭቆና መልስ ሊሆን ከቶ አይችልም። ምናልባት ለፈረንጆች መሸንገያነት ሊያገለግል ይችል ይሆናል።

የኢትዮጵያ ሴቶች በነፃ በዖታቸው መደራጀታቸውን በበጎና በጤናማ መልክ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው። ሴቶች እህቶቻችን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማምጣት ከሚታገሉ ድርጅቶች ውስጥ በብዛት ገብተው ከአመራር እስከ ተራ አባል መሳተፍ እንደሚገባቸውና ታጋይ ወንዶችም ከራሳቸው ጋር ታግለው ከወንድ ማንያህሎኝነት ነፃ በመውጣት የሴቶች ተሳትፎ እንዲጠናከር ሁኔታዎችን የማመቻቸት የአላፊነትና ግዴታ አለባቸው። በመሆኑም ተራማጅ

ወንዶች የሴቶች ተሳትፎ ስንል ትግላቸውን በተጨባጭ በቃልና በተግባር አጋርነታችን ማሳየትና መርዳት ማለት ነው። ኢትዮጵያዊያን ሴቶች በያታ ተደራጅታችሁ ለመብታችሁ ከመታገል በተጨማሪ ለጠቅላላው ቤተሰብና ለአገራችሁ ለአባቶቻችሁ፣ ለወንድማችሁ፣ ለትዳር ጓደኞቻቹሁ ባሎቻችሁና ለልጆቻችሁ ስትሉ በጋራ ለችግሮች ሁሉ መፍትሔዎች አመላካች የሚሆነውን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማምጣት ያላሰለሰ ጥረት በህብረት ማድረግ ለሁሉም ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው።

የአገራችንን ህልውና ለማስጠበቅና የዴሞክራሲያ ሥርዓት ለማምጣት ትግላችን ግቡን እንዲመታ ከተፈለገ የሴቶች ተሳትፎና የጋራ ብሄራዊ አጀንዳ ማለት ከአንድነት ጎራ ባሉ ድርጅቶችና ሲቪክ ማህበራትን ያካተተ የትግል ታክቲክና እስትራቴጂ መንደፍና በተግባር ላይ በቁርጠኛነት ማዋል አማራጭ የሌለው ነው። ይህ ብቻ ሲሆን ነው አቸናፊ መሆን የምንችለው። ታዲያ አሁን ያለውን የኢትዮጵያ የፓለቲካ ተጨባጭ ሁኔታዎችን ስንገመግም በዚህ ትግል ውስጥ ሁሉም ሴቶች ተሳታፊ ይሆናሉ ብለን አንገምትም። እንድያውም በተቃራኒው በአጥፊነት ለመስማራት አቀብቁበው ይገኛሉ። እነኝህ ሴቶች የወያኔ ተላላኪና ቅጥረኞች ለመሆን ያስፈሰፋ አንጃኞች፣ በታኞችና ከፋፋዮች በዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት ላይ ለመዝመት ሌላ የሴቶች ድርጅት እናቋቁማለን ብለው ወዲያ ወዲህ በመሯሯጥ ላይ መሆናቸውን እያስተዋልን ነው። የሚያደርጉትን ተንኮልና የሚነዙትን ውጅምብር ነቅተን እንደ አመጣጣቸው ልንታገላቸው ይገባል። በምንም ዓይነት መንገድ በትግላችን ላይ ቀዝቃዛ ውሃ እንዲከልሱበት ልንፈቅድላቸው አይገባም። ሁለተኛ ዓመቱን ያስቆጠረው ለጋው የዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበር ከበታኝና ከፋፋይ አንጃኞች ድርጅታቸውን በማጽዳት ህልውናውን መጠበቅ ሀላፊነትና ግዴታ አለባቸው። እኛም የትግል ወንድሞቻቸው የሚቻለን በመርዳት ከጎናቸው መቆም ግዴታችን ነው።

የኢትዮጵያ ሴቶች ጭቆናን በተለይም የኋላቀርና ጎጂ ባህል አስመልክቶ እኛ በደረስንበት ዘመን ማለት በከፊል ፊውዳልና በከፊል ካፒታሊስት ዘመን የነበረውን ምስክርነት ለመስጠት ይፈቀድልን። በዚያን ዘመን ግለሰቦች ሲጣሉና ሲሰዳደቡ አንተ/አንቺ "የሴት ልጅ" ሲባባሉ እንዲሁም ሲፈቃቀሩ ደግሞ አንተ/አንቺ "ጀግና የወንድ ልጅ" ነህ ወይም ነሽ ብለው ሲሞጋገሱ እየሰማን ነው ያደግነው። ይህ የሚያመለክተን በሕብረተሰባችን ውስጥ ምን ያህል ስር የሰደደ ጎጂ ባህል ማለት ሴትን በሆነው ባልሆነው ማጥላላት ትክክል አለመሆኑን ተገንዝበን፤ ኋላቀር የሆኑ ባህሎቻችን አጥብቀን መታገል ያለብን መሆኑን ነው። ለዚህም በመጀመሪያ ደረጃ ወንዶች ከራሳችን ጋር ታግለን የሴቶች እኩልነት ከልብ አምነን ለመቀበል መቻልና አጋርነታችን በተጨባጭ ማሳየት እንዳለብን ነው።

የባህል ነገር ከተነሳ በሁሉም አገሮች መልካምና ጎጂ ባህሎች አላቸው። ቁም ነገሩ መጥፎውን በመተውና መልካሙን በማዳበሩ ላይ ነው። የሚገርመው ያንዳንድ አገር ባህሎች ብዙ ግራ የሚያጋቡ አስተሳስብና ባህሪያት ያሉዋቸው መሆናቸው ነው። ለምሳሌ ሩስያዎች ስለአገራቸው ሲያስቡ ማለት በጦርነት ጊዜ እንደ አንደኛውና ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሕዝባቸውን ለጦርነት የሚቀስቅሱትና ያስባስቡበት መፈክር "ያባት አገር" ተደፈረ የሚለውን ነበር። በተቃራኒው የእኛ አገር የተጠቀመችበት "እናት አገር" ተወረረች የሚለውን ነው። ከዚህም ጠለቅ ብለውን ስንመለክት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታለች" ማለት የሴትነትን ትልቅነትን የሚያመለክት ሆኖ እናገኛዋለን። ይህ እንግዲህ እራሱን የቻለ ጥናት የሚያስፈልገው ጉዳይ ቢሆንም እንዲያው በደፈናው ጥሩ ባህሎችን መንከባከብና መጠበቅ፤ ጎጂውን መተው እንዳለብን እንረዳለን። እናት ልጆቿን በጣም ስለምትወድ፣ በተፈጥሮዋ ደግ፣ ርህሩህና ልበስፊ በመሆኗ "እናት" አገራችን የሚለው አባባል መልካምና አግባብነት ያለው ጥሩ ባህል ስለሆነ መጠበቅና መቀጠል ያለበት ነው። እዚህ ላይ ለኢትዮጵያ ሴቶች ማለት እናቶች የመጀመሪያ የልጆቻቸው አስተማሪ እንደመሆናቸው መጠን ባህሎቻችን፣ ቋንቋዎቻችንና ታሪካችንን ከማስተማር እንዳይቦዝኑ አደራ እንላለን። ለማጠቃለል እናቶቻችን ድርብርብ ጭቆናዎችን እንደተሸከሙ ከውጭ ወራሪ ጠላት ጋር በቆራጥነት በመዋጋት ህልውናችንንና ብሄራዊ ነፃነታችን እንዳስጠበቁልንና እንዳቆዩልን ሁሉ እኛም የበኩላችን ተጋድሎ አድርገን ለተተኪው ትውልድ የማስረከብ ሀላፊነት እንዳለብን ለአንድ አፍታ እንኳን ሳንዘነጋ አገራችንን ከጥፋት ለማዳንና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማምጣት ተግተን መታገል አለብን።

በሴቶች ሙሉ ተሳትፎ ትግላችን ግብን ይመታል!!! እናቸንፋለን!!!

*ዋቢዎች*


1. የኢሕአፓ የዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት የበዓል ቀን አስመልክቶ ያውጣው መግለጫ የካቲት 29 ቀን 2000 ዓ.ም.
2. www.IEWO.COM ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት፣ አላማዎችና ግቦች
3. Documentary Film, A Walk to Beautiful: View the Trailer, Engel Entertainment Production
4. ዴሞክራሲያ ቅጽ 33 ቁጥር 6 *"ሴት ልጅ ከታገለች የድል ቀን ቀርበች"*
5. በኮለኔል አስናቀ ዕንግዳ፣ ዘመን ያልሻረው የሴቶች አበሳ፣ ቨርጂኒያ፣ ስሜን አሜሪካ፣ 1996
6. http://www.SOCEPP.de/ የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ
7. www.wic.org/misc/history.htm, Women's History in America Presented by Women's International Center
8. www.un.org/ecosocdev/geninfo/women/women97.htm, International Women's Day